ጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪና አራቱ ተከታዮቹ በፕሮቶኮል አስተናባሪዎች አማካይነት ከመሰብሰቢያው አዳራሽ ገብተው፣ መሐል መሐሉን እየተራመዱ፣ ከመጨረሻው ጥግ ወደተያዘላቸው ሥፍራ ሲያመሩ በግራና በቀኝ ለሚገኙት መልዕክተኞች የፈገግታ ሰላምታ ለመስጠት መሞከራቸው አልቀረም:: ነገር ግን ከአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች እንዲሁም ከሆላንድና ከብራዚል መልዕክተኞች በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ የተመለከቷቸው በተከሳተረ ገጽታና በቀጣ በደፈረስ ዓይን ነበር:: የሲኞር ደጋስፐሪን ፀረ ፋሽስትነት የሚያደንቀው የሆላንዱ መልዕክተኛ መጀመሪያ በጭብጨባ ለመቀበል፣ ቀጥሎ በትህትና ሰላምታ ለመስጠት ሲዳዳው አይተው፣ ብዙዎቹ መልዕክተኞች በዓይናቸው ሲገላምጡት፣ ሎሬንሶ ታዕዛዝ እጅግ ተበሳጩ:: ወዲያው ከሆላንዱ አጠገብ በመሄድ ወዳጅ የሚያነጋግሩ መስለው፣ « ..... ድል የሆነ ጠላት ቅጣቱን ፈጽሞ ምሕረት እስከሚቀበል፣ ሰላምታና ክብር አይገባውም:: ስለዚህ እርፈህ ተቀመጥ .... » የሚል ቃል አሰሙት:: የሆላንዱም መልዕክተኛ ይህ ቃል የተሰጠው ለዛቻ ይሁን ለምክር፣ ነገሩ በትክክል ሳይገባው ደንግጦ፣ በደፈናው «እሺ አመሰግናለሁ» አላቸው:: ይህንን ትርኢት አይቶ እጅግ የተገረመው ከደጋስፐሪ ተከታዮች አንዱ የነበረው፣ በዚያን ዘመን የጣልያን የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር ጁሴፔ ብሩዛስካ ነው:: (GIUSSEPE BRUSASCA)

# የጣልያን ይቅርታ

« ..... የጣልያን ሕዝብ « የቀድሞ ጠላት » ሊባል የማይገባውና እውነትም የቀድሞ ጠላት ያልነበረ ነው:: ..... »

አልቺዴ ደጋስፐሪ

ቅዳሜ ነሐሴ 10 ቀን 1946 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ በአሥር ሰዓት፣ የሠላም ጉባኤው ሊቀመንበር ፈረንሣዩ ዦርዥ ቢዶ « ..... አሁን የአዲሲቷ ጣልያን መንግሥት መሪ የሚያደርገውን ንግግር እናዳምጣለን ... » ብሎ የሊቀመንበሩን ደወል ባስማ ጊዜ፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ሲኞር አልቺዴ ደጋስፐሪ ከአዳራሹ በስተጫፍ ከተሰጠው ወንበር ተነስቶ በአንድ የፕሮቶኮል ረዳት እየተመራ መሐል መሀሉን እየተራመደ ወደ መናገሪያው ስገኑት ሲያመራ፣ እጅግ የተከዘ መንፈስ ይታይበት ነበር:: ነገር ግን ዲስኩሩን ሲጀምር፣ ገና ከመጀመሪያው የሚያሳየው፣ ጣልያን የዓለም ሠላም ጠላት ተብሎ በተከሰሰበት ወንጀል ጥፋተኛነቱን አምኖ ምሕረት ለመጠየቅ ወይም ለመለማመጥ አለመዘጋጀቱን ነበር::

ቀጥሎም የሂትለር ግብረአበር የሆነውን የሙሶሊንን መንግሥት የጣልያን ሕዝብ መደምሰሱን እና ከተባበሩት የቃል ኪዳን የጦር ኃይሎች ጋር ተሠልፎ ናዚስቶችን በመውጋት ያደረገው መስዋዕትነት እንዲታወቅለት፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪ ትልቅ ጥረት ሆነ:: አስተያየቱን ከዚሁ ጋር በማያያዝ፣ ..... ከአገሩ ውስጥ ፋሽስቶችን ከውጭ ናዚስቶችን በመውጋት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረገው የጣልያን ሕዝብ፣ ዛሬ ሠላም ሲመሠረት እንደ ቀድሞ ጠላት ተቆጥሮ የጠነከረ የቅጣት ውል እንዲፈርም መገደዱ ትክክለኛ ፍርድ ይሆን ?..... » በሚል ጥያቄ ከጉባኤው አስተዛዛኝ አስተያየት ለማግኘት ከሞከረ በኋላ ፣ ወደ ቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ ተሻገረ::

በሲኞር ደጋስፐሪ አስተያየት፤ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች የሆኑት፤ ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሊ፣ ከፋሽስት ጥፋት ጋር የሚያያዝ ጉዳይ ስለሌላቸው፤ በቀጥታ ለአዲሲቷ ሬፑብሊክ መንግሥት መመለስ ይገባቸዋል። ባለፈው ግንቦት ወር እነዚህን ሶስት ቅኝ ግዛቶች የአዲሲቷ ሬፑብሊክ መንግሥት በሞግዚትነት ተቀብሎ እንዲያስተዳድራቸው፣ ከፈረንሣይና ከሶቪየት ሕብረት ቀርቦ የነበረውን ሀሳብ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በምሥጋና ካስታወሰ በኋላ፣ ጉባኤው እንደገና ይህንን ሀሳብ በጥልቅ ቢመለከተው የተዛባ ፍርድ ከመስጠት ይድናል አለ። ከዚህም ጋር አያይዞ በጦርነቱ ጊዜ ከእነዚሁ ኮሎኒዎች የተባረሩት የጣልያን ዜጎች፣ በተለይ በኬንያ እና በሮዴሽያ ያሉት ከፍ ባለ ሥቃይ ላይ ስለሚገኙ፤ ወደ ቤታቸውና ወደ ንብረታቸው እንዲመለሱ፤ እንደዚሁም ለየቅኝ ግዛቶቹ የአስተዳደር ኃላፊነት የነበራቸው ጣልያኖች፣ ወደ ቀድሞ ምድብ ሥራቸው ተመልሰው አሁን ባለው በታላቋ ብሪታንያ ወታደራዊ አስተዳደር የበላይ ተቆጣጣሪነት እንዲያገለግሉ ቢደረግ፣ ለየአገሩ ሕዝብ ማለት ለሊቢያ፣ ለኤርትራ እና ለሱማሌ እጅግ ጠቃሚ ይሆናሉ የሚል ሀሳብ አቀረበ። በደጋስፐሪ አስተያየት የኮሎኒያል አድሚኒስትራተሮችና የፋሽስት ባለሥልጣኖች የነበሩት ሁሉ በየቀድሞ ቦታቸው ተመልሰው፣ ግፍና ጭቆና የተሞላበት ሞያቸውን እንዲቀጥሉ ያስፈልጋል ማለት ነው።

የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ለእነዚህ ሶስት ቅኝ አገሮች የወደፊት ዕድል ለመወሰን አራቱ ኃያላን መንግሥታቶች የአንድ ዓመት ጊዜ እንዲጨመርላቸው የጠየቁትን አልተቃወመም። ነገር ግን ጉባኤው ይህን ሀሳብ በሚያጸድቅበት ጊዜ፣ ለጣልያን በተዘጋጀው የዕርቅ ውል ላይ፤ «<u>ጣልያን የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቿን ለመልቀቅ ተስማምታለች</u>» የሚለው ቃል እንዲሠረዝለት አስፈላጊ መሆኑን አመልክቷል። ሲኞር ደጋስፐሪ በዲስኩሩ ማክተሚያ ላይ የተናገረው ቃል የተለየ መልክ ነበረው።

« የቀድሞው የጠላት አገር እንደራሴ፣ የሚል ስም ተሰጥቶኝ ዛሬ ከፊታችሁ ስቀርብ ደጋግሜ ሳረጋግጥላችሁ የምፈልገው፤ የጣልያን ሕዝብ « <u>የቀድሞ ጠላት</u> » ሊባል የማይገባው እና በእውነተኛውም « <u>የቀድሞ ጠላት</u> » ያልነበረ መሆኑን እንድትገነዘቡልኝ ነው። ...... የታላቋ ብሪታንያ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበረው ዊንስተን ቸርችል እንደተናገረው፤ የፋሽስት ጦር በዓለም ላይ የዘመተው፤ በአንድ ሰው ውሳኔ፣ በአንድ ሰው ፍላጎት፣ መሆኑ እንዲታወቅ መሻው የጣልያን ሕዝብ ለዓለም ታዛቢዎች ያመለክታል። ..... በጣልያንነቴ እና ፀረ ፋሽስት በሆነው መሠረታዊ አቋሜ፤ የነ ጁሴፔ ማዚኒን (GIUSEPPE MAZZINI) ሰብዓዊ መንፈስ በሚከተለው ዓላማዬ፣ ዩኒቨርሳል በሆነው ክርስቲያናዊ እምነቴ፣ የምጠይቃችሁ አንድ ነገር ብቻ ነው። ይኸውም፤ ሠላምን በእውነተኛ ሠላም ላይ ለመመሥረት አርባ ሰባት ሚሊዮን (47) ለሆነው ለአገሬ ሕዝብ፤ ትክክለኛ የሆነ መብቱን እንዳትነሱት፣ ተገቢውንም ፍርድ እንዳትነፍጉት ብቻ ነው » በሚል አቤቱታ ንግግሩን ደመደመ።

የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር በዚህ አነጋገሩ፣ አለአግባብ የተፈረደበት አጋር የሌለው ይግባኝ ጠያቂ መስሎ ቢታይም፤ ቀደም ሲል በሰፊው ዲስኩሩ የተነተናቸው ታሪኮችና የገለጻቸው አስተያየቶች፣ ከእውነተኛው መስመር የወጡ መሆናቸውን ሊሸፍንለት አልቻለም። የደጋስፐሪ ንግግር በጣልያን ላይ እንኳንስ ቂም በቀል ያላቸውን አገሮች ይቅርና፤ እንዳንድ መልካም መንፈስ ሊያሳዩት የሚሹትንም ቢሆን፣ የሚያበሳጭ እንጂ የሚያስታግስ አልነበረም። ከሰኔ 10 ቀን 1940 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሐምሌ 20 ቀን 1943 ዓ.ም ድረስ፤ የጣልያን ጦር

ከናዚስቶች ጋር ሆኖ ለሶስት ዓመታት ያለማቋረጥ በመላው አውሮፓ እና በሰሜን አፍሪካ ባደረገው ውጊያ፣ ደጋስፐሪ እንደሚለው የጣልያን ሕዝብ ተካፋይ አልነበረም ሊባል አይቻልም። በጠቅላይ ሚኒስትሩ ዲስኩር ብዙ ድርጊቶች ሳይገለጡ ታልፈዋል።

- ሐምሌ 20 ቀን 1943 ዓ.ም ሙሶሊኒ ከሥልጣን የወረደው፣ የእንግሊዝና የአሜሪካ ጦር ኃይሎች በደቡብ ጣልያን በሲሲሊያ በኩል ገብተው፣ የጣልያንን ወገብ ካነቁ በኋላ መሆኑ አልተነገረም።

- የጣልያን ንጉሥ ቪክቶር አማኑኤል ሳልሳዊና የፋሽስት ጦር አዛዥ የነበረው ማርሻል ባዶግሊዮ፣ (MARSHALLO BADOGLIO) ሐምሌ 20 ቀን 1943 ዓ.ም ሙሶሊኒን አሥረው አዲስ መንግሥት ሲያቋቁሙ፣ የጣልያን አዲሱ አስተዳደር ከናዚ ጋር የተደረገውን ስምምነት አክብሮ ጦርነቱን እንደሚቀጥል በማረጋገጥ መሆኑ አልተጠቀሰም።

- የጣልያን ጦር ከናዚ ጋር የነበረውን ሠልፍ አቋርጦ፣ የመሣሪያውን አፈሙዝ ወደ ጀርመን እንዲቀለብስ የተገደደው፣የእንግሊዝና የአሜሪካ ጦር ኃይል ድል እያደረገ መጥቶ የማርሻል ባዶግሊዮም መንግሥት ጄኔራል አይዘንሐወር ተንበርክኮ መስከረም 8ቀን 1943 ዓ.ም የተሸናፊነቱን ስምምነት ከፈረመ በኋላ መሆኑ አልተገለጸም።

ፀረ ፋሽስትነቱንና ሠላም ወዳድነቱን በመሀላ አረጋግጣለሁ የሚለው አልቺዴ ደጋስፐሪ፣ በ 1936 ዓ.ም በጋዝና በመርዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ በማቃጠል ፋሽስት የፈጸመውን የጭካኔ ሥራ፣ ማውገዝ ተገቢ መሆኑን አላመነበትም። እንደዚሁም የፋሽስት ጥቃት የደረሰባቸውን እንደ ዩጉዝላቪያ እና እንደ ግሪክ የመሳሰሉትን አገሮች ማስታወስ አስፈላጊ ሆኖ አልታየውም። በጠቅላላው የሲኞር ደጋስፐሪ ዲስኩር እሱ እንደተመጻደቀው የሰብዓዊነትን እና የክርስቲያንነትን ሀቅ ያልተመረኮዘ ስለሆነ፣ የጉባኤው ተካፋይ ከሆኑት ከሀያ አንድ አገሮች መካከል አንዳችም የሀዘኔታ አስተያየት ማግኘት አልቻለም።

ከጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ንግግር በኋላ፣ የብዙዎች አገሮች መልዕክተኞች መልስ እንደሚሰጡ የሚጠበቅ ነበር። በፋሽስት ጦር በመጀመሪያ የተጠቃችውና ከዚሁ ከፋሽስት ቀንበር ደግሞ ነፃነት በማስመለስ የመጀመሪያዋ የሆነችው ኢትዮጵያ፣ ለጣልያን መሪ ንግግር ከመልስ ሰጭዎቹ የመጀመሪያዋ ሆና ተመዘገበች። በዚያ በአምስቱ ዓመት የጠላት ዘመን በእንግሊዝ አገር ከንጉሠ ነገሥቱ ሳይለዩ፣ ከፍተኛ የፖለቲካና የዲፕሎማሲ አገልግሎት የሰጡት፣ ኋላም ነፃነት ሲመለስ የመጀመሪያው የጃንሆይ ካቢኔ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩት ብላቴን ጌታ ሎሬንሶ ታዕዛዝ፣ ለጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ንግግር መልስ እንዲሰጡ ተደረገ።

ሎሬንሶ ታዕዛዝ ከመናገሪያው ሠገነት ላይ ወጥተው የኢትዮጵያን አስተያየት ለመግለጽ ሲጀምሩ፣ « ..... የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ሲናገር በማዳምጥበት ጊዜ፣ ብዙ አሳዛኝ ሁኔታዎች እየታወሱኝ፣ በተለይ ስሜቴን ለመቆጣጠር የታገልኩበት አንድ ትዝታ አለኝ ...... » አሉ። ይኸውም ..... የዛሬ አሥር ዓመት በጄኔቭ የመንግሥታት ማህበር ስብሰባ ላይ፣ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት በአገራቸውና በሕዝባቸው ላይ የሙሶሊኒ ጦር የሚፈጽመውን ግፍ ሲያመለክቱ፣ በአዳራሹ የተሰገሰጉት የፋሽስት መልዕክተኞች ንጉሠ ነገሥቱን

አላናግር ብለው፣ የሚያሰሙት የብልግና ጩኸትና ፉጨት፣ ከአዕምሮዬ እየተደቀነ ነው:: ...... ይህ አሳዛኝ ሁኔታ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ላይ ሲፈጸም፤ በተለይ የታላላቅ መንግሥታት እንደራሴዎች ሕገ ወጡን ሥራ ያዘጋጀው የፋሽስቱ መልዕክተኛ መሪ መሆኑን እያወቁ፤ አንድ ዓይነት እርምጃ እንዲወሰድበት ወይም በጉባኤው እንዲወገዝ አለመፈለጋቸው ምንጊዜም ከአዕምሮዬ ሊጠፋ አይችልም:: ..... በዚያን ጊዜ የፋሽስት መንግሥት ከጀርመን ናዚ ጋር ተደርቦ የአውሮፓ ደህንነትና ሠላም እንዳይደፈርስ ፍራቻ ስለነበረ፤ ለኢትዮጵያ ስቃይ ማሰብ አስፈላጊ አልሆነም:: ይሁን እንጂ፣ ያ እንደዚያ ብዙ መንከባከብ የተደረገለት ሠላም፣ ብዙ መቆየት ስለአልቻለ፤ በኢትዮጵያ ላይ ከባዱ መከራ በወደቀ በሶስት ዓመቱ፣ ዓለም በጦርነት እሳት ውስጥ ገብቶ ፈተናውን ተቀበለ .... » ካሉ በኋላ፣ በሲኞር ደጋስፐሪ ዲስኩር ውስጥ ኢትዮጵያን በቀጥታ በሚመለከተው ጉዳይ ሎሬንሶ ታዕዛዝ የገለጹት አስተያየት የሚከተለው ነበር::

« ...... የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ከጣልያን መንግሥት መሪ የሰሙት ንግግር፣ በሙሶሊኒ የፋሽስት ዘመን ከነበረው አስተያየት የተለየ ሆኖ አለማግኘታቸውን ለጉባኤው የሚገልጹት እጅግ እያዘኑ ነው:: ...... ጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪ ያለ አንዳች እፍረት ባቀረበው ሀሳብ፣ የጣልያን ቅኝ የነበሩት አገሮች በሙሉ ለጣልያን እንዲመለሱ የመብት ጥያቄ አድርጉ አቅርቦታል:: ከዚህም ጋር አያይዞ በሊቢያ፣ በኤርትራና በሱማሌ ሕዝቦች ላይ፣ ለብዙ ዘመናት ግፍ ሲፈጽሙ የኖሩት የፋሽስት ባለሥልጣኖች በቀድሞ ምድብ ቦታቸው መመለስ አለባቸው ብሏል:: ይህንን በመሰለ ሀሳብ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች ሀዘናቸውን እና ትዝብታቸውን ቢገልጡ፤ የተገባ መሆኑን የተከበራችሁ መልዕክተኞች እንደምታምኑበት እርግጠኛ ነኝ:: ..... የጣልያን መንግሥት በተለይ ኤርትራንና ሱማሌን ለመውሰድ የሚጥረው፣ ከዚህ ቀደም ደጋግሞ እንደፈጸመው ሁሉ፣ አሁንም በእነዚህ አገሮች ላይ የጦር ኃይሎቹን ማስፈሪያና ማሽጋገሪያ አድርጉ ለአራተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ለመውጋት ነው:: ስለዚህ ኤርትራና ሱማሌ ለጣልያን እንዲመለሱ ቢደረግ፣ ኢትዮጵያ በነፃነቷ ላይ አደጋው እንዳይደርስባት ለመከላከል በቅድሚያ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ የምትገደድ መሆኑ እንዲታወቅላት ትፈልጋለች .... » በሚል ቃል የሎሬንሶ ታዕዛዝ ንግግር ተፈጸመ::

ከኢትዮጵያ ቀጥሎ በጣልያን ዲስኩር ላይ ከፍ ያለ ትችት የሰጠው፣ የመስኮብ መልዕክተኞች መሪ ሙሴ ሞሎቶቭ ነበር:: የሶቪየት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በመስከረም 1945 ዓ.ም በሎንዶን በተደረገው የአራቱ ኃያላኖች የውጭ ጉዳይ ምክር ቤት ስብሰባ ላይ፣ ጣልያን ከቅኝ ግዛቶቿ መነቀል ይገባታል ብሎ መፍረዱ ይታወሳል:: ከስምንት ወራት በኋላ ደግሞ ይኸው ስብሰባ ፓሪስ ላይ ሲደረግ፤ ግንቦት 10 ቀን 1946 ዓ.ም የማርሻል ስታሊን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፤ ከፈረንሣይ ጋር ተደርቦ ለጣልያን ሶስቱም ቅኝ ግዛቶቿ እንዲመለሱላት ያልተጠበቀ አዲስ አስተያየት አቀረበ:: ይህ ከሆኗ ከሁለት ወር በኋላ፣ ጣልያን ቅኝ ግዛቶቿን በፈቃዷ መልቀቋን በውሉ ላይ እንድትፈርም እንግሊዞችና አሜሪካኖች ያቀረቡትን ሀሳብ የመስኮብ ዲፕሎማሲ መሪ ሐምሌ 12 ቀን 1946 ዓ.ም መስማማቱ ተነገረ:: አሁን ደግሞ በዚህ በሠላሙ ጉባኤ ላይ ሙሴ ሞሎቶቭ ለመናገር በቀረበ ጊዜ፣ ምን አዲስ ጣጣ ይፈጥር ይሆን ? ተብሎ ሲጠበቅ፣ የጣልያን ጠቅላይ ሚኒስትር ያደረገውን ዲስኩር ነጥብ በነጥብ እየመነጠረ የከረረ ነቀፋ በስፊው ሲያወርድበት፣ ለኢትዮጵያ መልዕክተኞች ትልቅ ደስታ ሆነ::

« ...... አሁን የሰማነው የጣልያን የመንግሥት መሪ ንግግር፣ አራቱ ኃያላን መንግሥታት ያረቀቁትን የዕርቅ ውል የሚቃወም ከመሆኑ በስተቀር፣ አዲሲቷ የተባለችው ጣልያን ስለአሳት መሠረታዊ አቋም፣ የዓለም ሕዝብ ለሚያቀርበው ጥያቄ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት አልፈለገም:: ...... ብዙ መብራራት የሚገባቸውን ቁም ነገሮች ሸፋፍኖ አልፏቸዋል:: ለምሳሌም ያህል የሙሶሊኒ ጣልያን፣ በኢትዮጵያና በአልባኒያ፣ በዩጐዝላቪያና በግሪክ አገሮች ላይ የፈጸመውን በደል በማውገዝ ፋንታ መሸሽን መርጧል:: ..... አዲሱ የጣልያን መንግሥት ፀረ ፋሽስትነቱን ለማሳመን ካለመቻሉም በቀር፣ እንዲያውም ይግረማችሁ ብሎ ቀደም ሲል በኮሎኒያሊስት ዘመን የተጀመረውን እና ፋሽስቱ ሙሶሊኒ የቀጠለውን የግዛት ማስፋፋት ፖሊሲ የሚከተል መሆኑን አሳይቶናል:: ... » በማለት ቅሬታውን በስፊው ገለጸ:: ቀጥሎም <u>የጣልያን ሕዝብ ፋሽስትን የደመሰሰና ከተባበሩት የቃል ኪዳን የጦር ኃይሎች ጋር ተሰልፎ ለዓለም ሠላም ደሙን ያፈሰሰ ነው</u> ሲል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የፎለለበትን ዲስኩር፣ ሙሴ ሞሎቶቭ እውነተኛውን ታሪክ እየገለጠ አስተካከለለት::

የፋሽስት መንግሥት የተባረረው፣ ናዚስቶች በስታሊንግራድ ከተዋረዱና ከደቀቁ በኋላ፣ የእንግሊዝና የአሜሪካ ጦር በሰሜን አፍሪካ የፋሽስትን ጦር አስለቅቀው፣ በሲሲሊያ በኩል ተሻግረው፣ ደቡብ ጣልያንን በእጃቸው ሲይዙ መሆኑን ሲኞር ደጋስፐሪ እንዲገነዘበው፤ ሙሴ ሞሎቶቭ የታሪኩን ሂደት ደህና አድርጎ አብራራለት:: አዲሲቷ ዴሞክራቲክ የተባለችው ጣልያን ዛሬ የምታሳየው መልክ እጅግ የሚያሳስብ መሆኑን ከገለጸ በኋላ፣ የሶቪየት ሕብረት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ንግግሩን ሲፈጽም፤ « ...... የአሁኖቹ የጣልያን መሪዎች ከፋሽስት ወጥመድ ተላቀዋል፣ ብሎ ለማመን አይቻልም ..... » ብሏል::

ሲኞር አልቺዴ ደጋስፐሪ ያደረገው የተቀናጣ ዲስኩር፣ የጣልያንን ቅጣት የሚያጠነክርበት እንጂ እሱ እንደሚመኘው ፍርዱን ለማላላት የሚረዳው ሊሆን አልቻለም:: በቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ የጣልያን ደጋፊነቱን በግልጽ ያሳየው፣ የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዦርዥ ቢዶ እንኳን ባደረገው ንግግር፣ « ..... የፋሽስት ጦር በዓለም ላይ ለፈጸመው ወንጀል፤ የጣልያን ሕዝብ ተጠያቂ አይደለም ማለት አይቻልም ...... » ብሏል:: የታላቋ ብሪታንያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም አስተያየቱን ሲገልጽ፣ አራቱ ኃያላኖች ባረቀቁት ውል፣ ጣልያን እንድትጐዳ ያደረጉት ነገር አለመኖሩን ከጠቀሰ በኋላ፣ « ..... የቀድሞዎቹ ጠላቶቻችን (እንደ ጣልያን የመሳሰሉት) የተዘጋጀላቸውን ውል ከመፈረማቸው በፊት፣ ሀሳባቸውን ቀርበው እንዲያስረዱ መፍቀዳችን ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ነው:: ..... » ብሏል::

ኤርነስት ቤቨን እንደተናገረው አራቱ ኃያላን መንግሥታቶች ለጣልያን የሰጡትን ዕድል ሌሎቹ የዓለም ጠላቶች አላገኙትም:: የሂትለር ጀርመን ግንቦት 8 ቀን 1945 ዓ.ም፤ ጃፓን ነሐሴ 15 ቀን 1945 ዓ.ም፣ ድል መሆናቸውን ተቀብለው የሠላም ውል ሲፈርሙ፣ እንኳንስ ይህ መለወጥ አለበት፣ ይህ ተገቢ አይደለም እያሉ በዲስኩር ለመተቸት ይቅርና፣ አንዳንድ መጠነኛ ጥያቄዎች እንኳን ለማቅረብ አልተፈቀደላቸውም:: የተሸናፊዎቹ ግዳጅ አሸናፊዎቹ በወሰኑት መሠረት የተጻፈውንና የቀረበላቸውን ዶኩሜንት ያለአንዳች ማንገራገር መፈረም ብቻ ነበር:: ሲኞር ደጋስፐሪ ያለፈውን ማስታወስ ባለመፈለጉ ነው እንጂ፣ የማርሻል ባዶግሊዮ መንግሥት መስከረም 8 ቀን 1943 ዓ.ም ጣልያን ወንጀለኛነቷንና ድል መሆንዋን አረጋግጦ፣ ከአንድ የአሜሪካ የጦር ዤኔራል ጋር <u>የፈረመው ጊዜያዊ ውል</u>፣ ኋላ

ለጀርመኖችና ለጃፓኖች ከተዘጋጀው የተለየ አልነበረም። ደግነቱ ያ ጊዜያዊው ውል ጊዜያዊ ሆኖ መቅረቱ ነው እንጂ፣ ዛሬ በዚያው መልክ ቀጥሎ ቢሆን ኖሮ ጣልያን የደም እንባ ታለቅስ ነበር።

ሐምሌ 25 ቀን 1943 ዓ.ም ሙሶሊኒ ከሥልጣን ወርዶ አዲሱን መንግሥት ያቋቋመው የማሬሻል ፒየትሮ ባዶግሊዮ (PIETRO BADOGLIO) ዋና ምኞት፤ በሰሜን ጣልያን ከሠፈሩት የጀርመን ናዚስቶች እና በደቡብ ጣልያን ኃይላቸውን ካከማቹት የተባበሩት የቃል ኪዳን አገሮች መካከል ሆኖ፣ ለነዚያም ለነዚህም አብሬአችሁ ነኝ እያለ፣ ለመቆየት ነበር። ነገር ግን የዚህ ዓይነቱ ማጭበርበር ሳይታወቅበት ከአንድ ወር የበለጠ ዕድሜ ሊያገኝ አልቻለም። የቃል ኪዳን አገሮች የጦር አዛዥ የሆነው ጄኔራል አይዘንህወር ተቆጥቶ፤ ማርሻል በዶግሊዮ በአስቸኳይ ውሉን እንዲፈርምና፣ ወታደሮቹንም ከተባበሩት የጦር ኃይሎች ጋር አሠልፎ፣ በሰሜን ጣልያን ከሠፈሩት ናዚስቶች ጋር እንዲዋጋ ወሰነበት። በዚህ ጊዜ በድንገት ሽሚዛቸውን ገልብጠው ፀረ ሙሶሊኒ በሆኑት በእነ ቪክቶር አማኑኤል ሣልሣዊና፣ በእነ ማርሻል ባዶግሊዮ ላይ ትልቅ ጉድ ፈላ። በሰሜን ጣልያን በኩል የጀርመን ጦር እሳት ጉርሶ እሳት ለብሶ ወደ ሮም ጉዞ ጀመረ። በደቡብ በኩል ደግሞ የተባበሩት የቃል ኪዳን አገሮች ኃይል እየገፋ መጣ። በዚህ ሁኔታ የማርሻል ባዶግሊዮ መንግሥት ከላይም ከታችም እሳት እየነደደበት ሮም ላይ «ድፎ ዳቦ» ሆኖ ለመጋገር ምቹ ሆነ። ወዲያው ሮምን በሩጫ ለቅቆ ብሪንዲሲ "BRINDISI" ከምትባል አንዲት በደቡብ ጣልያን በአድሪያቲክ የባሕር አካባቢ የምትገኝ ከተማ ላይ ከሠፈረ በኋላ፣ በፀረ ፋሽስትነትና በፀረ ናዚስትነት ውጊያውን የሚቀጥል መሆኑን ስለአስታወቀ፤ የተባበሩት ኃያላን ጦር እርዳታ ሰጥተው በናዚ ከመጨፍለቅ አዳኑት።

እንግዲህ ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ አራቱ ኃያላን መንግሥታቶች በጣልያን ላይ የወሰኑት ቅጣት ከጀርመንና ከጃፓን እጅግ የተለየና በጣም የተሻለ የሆነበት ምክንያት፣ ከመስከረም 1943 ዓ.ም ጀምሮ በማርሻል ባዶግሊዮ የተመራው መንግሥት ከተባበሩት የቃል ኪዳን አገሮች ጋር ነኝ ብሎ የአቅሙን ተፍጨርጭሯል በሚል አስተያየት ነበር። አዲሶቹ መሪዎች እነ ደጋስፐሪ ግን፣ ይህን ሁሉ ከውለታ ሳይቆጥሩ፣ በጠቅላላው የጣልያን ሕዝብ የፋሽስቱ መሪ ሙሶሊኒ ባደረሰው ጥፋት ተጠያቂ አይደለም፤ የሚል ሙግት ለመክፈት ያደረጉትን ዲስኩር የሚያዳምጥላቸው ሳያገኙ ቀሩ።

ለጣልያን በተዘጋጀው የዕርቅ ውል ላይ፤ ከሚደረደሩት አንቀጾች ለውሳኔ ጊዜ የፈጁት ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ነበሩ። እነዚህም፣ የመጀመሪያው ቀድሞ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች የነበሩትን የሊቢያን፣ የኤርትራንና የሱማሌን የወደፊት ዕድል መወሰን ሲሆን፤ ሁለተኛው፤ በጣልያንና በዩጉዝላቪያ መካከል የከረረ ጠብ የፈጠረው «ትሪየስቴ» የተባለው አውራጃ ጉዳይ ነበር። የሠላሙ ዋና ጉባኤ እነዚህን ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ሰፋ ባለ መንገድ አጥንቶ ሀሳብ እንዲያቀርብ፣ የፖለቲካና የግዛቶች ጉዳይ ኮሚሲዮን አቋቋመ። በመሠረቱ የዚህ ኮሚሲዮን መቋቋም የተለየ ሀሳብ ያመነጫል ተብሎ ሳይሆን፣ በጉዳዮቹ ላይ ሰፊ ጥናቶች መከናወናቸውን ለማሳየት ያህል ነበር። ከዚህ ቀደም እንደተነገረው፣ በአራቱ ታላላቆች የተረቀቀውን ለመለወጥ አይቻልም። የሠላም ጉባኤው ለወጉ የዕርቅ ውሉቹን አጸደቀ ተብሎ የሚወራለት፣ እራቱ ኃያላኖች በቅድሚያ የተስማሙባቸውን ጉዳዮች መሆኑ የተረጋገጠ ነው።

በቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ የየራሳቸውን አቋም ይዘው ለመሟገት የቀረቡት፣ ኢትዮጵያና ጣልያን ሲሆኑ፤ በድንገት ግብፅም ከኤርትራ ግዛት ውስጥ የምፅዋ የባሕር በር፣ የእኔ ይዞታ የነበረ ነው የሚል ዲስኩር አዘጋጅታ ስለመጣች፣ ሶስተኛዋ የመብት ጠያቂ ሆና ተመዘገበች:: ኮሚሲዮኑ ሥራውን ሲጀምር በመጀመሪያ ያዳመጠው የኢትዮጵያን መግለጫ ነበር::

«...... ከቀድሞዎቹ ጠላቶቻችን ጋር የምናደርገውን የዕርቅ ውል ለማዘጋጀት በተከፈተው በዚህ በሠላም ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ የተካፈለችው ከልብ በመነጨ መልካም ስሜት ነው:: ... በዚህ አስቸጋሪ በሆነ ዓለም ውስጥ ነፃነቷን አላስነካም በማለት ብዙ መከራዎች ሲፈራረቁባት ለኖረች ኢትዮጵያ፣ የነፃነት ዋጋው እና የሠላም ጥቅሙ ምን እንደሆነ፣ ከማንም ያላነሰ፣ ሲሆን በበለጠ፣ በጥልቅ የተረዳች ነች ብዬ ብናገር፣ አበዛው ብላችሁ እንደማትወቅሱኝ ተስፋ አደርጋለሁ::

...... ይህ የሠላም ጉባኤ በክፍለ ዘመናችን ታሪክ ውስጥ እንድ የተለየ ምዕራፍ ይዞ ሲጠቀስ የሚኖር ነው ብላ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ግምት ትሰጠዋለች::

...... ይህ የሠላም ጉባኤ ለዓለም ሠላም እና ደህንነት ዋስትና ለመስጠት እንዲችል፣ እያንዳንዳችን የኃላፊነት ድርሻችንን ማቅረብ እንደሚያስፈልገን ኢትዮጵያ በጥልቅ ታምናለች::

...... ይህን አስተያየት ሁላችንም የምንቀበለው ቢሆን፣ ለጉባኤው ሥራ የተደቀኑትና የተወሳሰቡት የዓለም ፕሮብሌሞች ሁሉ፣ ዘላቂ የሆነ መፍትሔ እንደሚያገኙ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ተስፋ ታደርጋለች:: በዚህ መሠረት ኢትዮጵያ ድርሻዋን ለማበርከት በምታቀርበው ሀሳብ፣ ይህ የሠላም ጉባኤ በፖለቲካና በኤኮኖሚ ጥቅም ከተበረዘ አስተያየት በመራቅ፣ በትክክለኛ ፍርድ ላይ ብቻ ተመርኩዞ፣ የሚጠበቅበትን ግዳጅ እንዲፈጽም አጥብቃ ትጠይቃለች:: .....

...... ይህ የሠላም ኃላፊነት የወደቀበት ከፍተኛ ጉባኤ የሚሰጠውን ፍርድ ለመስማት፣ የዓለም ሕዝብ ፊቱን ወደ ፓሪስ መልሶ በናፍቆት ስለሚጠብቅ፣ በውጤቱ እንዳያዝንና ተስፋውን እንዳይቆርጥ ኢትዮጵያ ልባዊና ጽኑ ምኞቷን ታቀርባለች ..... » ካሉ በኋላ፣ የመልዕክተኞች መሪ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ኢትዮጵያ በበኩልዋ ከዚህ የሠላም ጉባኤ ትክክለኛ ፍርድ ለማግኘት የምታመለክተውን ሲያቀርቡ እንዲህ አሉ::

<u>ትክክለኛ ፍርድ ለኤርትራና ለሱማሌ ሕዝቦች !</u> ያለውዴታቸው በግዴታ በኮሎኒያሊስት ጣልያን በጭቆና አስተዳደር ሲሰቃዩ የኖሩ በመሆናቸው፣ ዛሬ በዓለም ላይ የተዘረጋው የሕዝቦች የነፃነት ብርሃን ውጋጋን በእነሱም ላይ ፈንጥቆ ከእናት አገራቸው ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀሉ፤

<u>ትክክለኛ ፍርድ ለራሷ ለኢትዮጵያ !</u> ከሎኒያሊስት ጣልያን ነጥቆ በወሰደባት ግዛቶቿ ላይ፣ የጦር ማከማቻና ማሸጋገሪያ እያደረገ፣ በአንድ የትውልድ ዘመን ውስጥ ሶስት ጊዜ አከታትሎ ያደረሰባት ጥቃት፣ ለአራተኛ ጊዜ እንዳይደገም፤

ትክክለኛ ፍርድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ! የባሕር በሩ እና መገናኛዎቹ ተዘግተውበት፣ ጠላት የሚያደርስበትን ጥቃት እየተቀበለ ከኖረበት የመከራ ዓለም ለመላቀቅ እንዲችል፣ በኮሎኒያሊስት ጣልያን የተወሰዱበት የሰሜንና የደቡብ አገሮቹ እንዲመለሱለት፣ ይህ የሠላም ጉባኤ በዳኝነት ተመልክቶ እንዲፈርድ ጥያቄዎቹ ቀርበውለታል:: የተከበራችሁ መልዕክተኞች ! ይህ የሠላም ጉባኤ የሚሰጠው ፍርድ፣ ያሳለፍነውን ጥቁር የመከራ ዓለም ለታሪክ አስረክቦ፣ አዲሱን የተስፋ ዓለም ለመረከብ የሚያስችለን ይሆናል ብለን እንጠብቃለን:: እንደዚሁም፣ የቀድሞ ጠላቶች የነበሩት የዛሬ ወዳጆች ሆነው፣ ለአገሮች ሠላም እና ነፃነት፣ ለሕዝቦች ብልፅግና እና ደህንነት፣ ፍሬያማ ጥረት የሚያደርጉበት ዓለም እንዲሆን ኢትዮጵያ ሙሉ ተስፋ ታደርጋለች:: ...... »

የአቶ አክሊሉ መግለጫ ሲፈጸም፣ የካናዳ፣ የቻይና እና የዩጐዝላቪያ መልዕክተኞች በየተራ እየተነሱ፣ የኢትዮጵያ ጥያቄ ተገቢ ነው በማለት ድጋፍ መስጠት ጀመሩ:: የስብሰባው ሊቀመንበር ፈረንሣይ በመሆኑ፣ እንደ ካናዳ እና እንደ ቻይና የመሳሰሉት አገሮች የሚሰጡት ድጋፍ እየጨመረ ከሄደ፣ ለወዳጁ ለጣልያን አደገኛ መሆኑ ስለተሰማው፣ ቶሎ ብሎ ለጣልያን መንግሥት መልዕክተኛ የመናገሪያ መድረኩን ሰጠ ::

የፋሽስት መንግሥት በዓለም ላይ ባደረሰው ጥፋት ምክንያት በጉዳዩ እንግዳ የሆነው የጣልያን ሕዝብ፣ ብዙ መስዋዕት አድርጐ ያቀናቸውን ግዛቶቹን በገዛ ፈቃዱ እንዲለቅ መገደዱ ተገቢ አለመሆኑን፣ የጣልያን መልዕክተኛ በስፊው ከተቸ በኋላ፣ ፊቱን ወደ ኢትዮጵያ መልዕክተኞች መልሶ « .... በዚህ በሠላም ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ ተካፋይ መሆኗ ትክክል አይደለም:: ...... » አለ:: ሲኞር በኖሚ (BONOMI) ምክንያቱን ሲያብራራ፣ « .... የዚህ የሠላም ጉባኤ ዋና ዓላማ፣ ሙሶሊኒ ከሂትለር ጐን ሆኖ ጦርነቱ ውስጥ ከተካፈለበት ከ 1940 ዓ.ም ወዲህ ከፋሽስት ጦር ጋር በያለበት ከተዋጉት አገሮች አዲሲቷ ጣልያን የምታደርገውን የዕርቅ ውል ለማዘጋጀት ነው ተብሏል:: በፋሽስት መንግሥትና በኢትዮጵያ መካከል የተደረገው ግጭት በግንቦት 1936 ዓ.ም ተፈጽሞ፣ ኢትዮጵያ የጣልያን ቅኝ ግዛት ስለሆነች፣ ዛሬ ከጣልያን ጋር የምታደርገው የዕርቅ ድርድር የለም:: ...... » አለ::

ይህ የጣልያን መልዕክተኛ የሰጠው መግለጫ ምናልባት ትክክለኛ ጥያቄ ሳይሆን አይቀርም በማለት ብዙዎቹ መልዕክተኞች ተደናግጠው የጉባኤውን የውስጥ ደንብ ሲያገላብጡ ታዩ:: የስብሰባውም ሊቀመንበር የጣልያን ጥያቄ ትክክል መሆን አለመሆኑን ለይቶ በማስረዳት ፋንታ፣ ሲያመነታ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ መልሱን ይዘውለት ቀረቡ::

« ..... በኢትዮጵያና በጣልያን መካከል ጥቅምት 3 ቀን 1935 ዓ.ም የተጀመረው ጦርነት የቆመው፣ ከስልሣ ሰባት ወራት በኋላ በግንቦት 5 ቀን 1941 ዓም ኢትዮጵያ ጣልያንን ድል አድርጋ ከግዛቷ ውስጥ ካበረረች በኋላ ነው:: .... በ 1941 ዓ.ም በታላቋ ብሪታንያ ከፍተኛ እርዳታ የጣልያንን ጦር ከደመሰሰች በኋላ፣ ከተባበሩት የቃል ኪዳን አገሮች ጐን ሆና እንኳንስ በቀጥታ ስትዋጋ ከኖረችው ከፋሽስት መንግሥት ቀርቶ፣ ለሌሎቹም የዓለም አጥፊዎች ለሆኑት ለጀርመንና ለጃፓን ዲክታተሮች ጦር ያወጀች መሆንዋን ታላላቅ መንግሥታቶች ይመሰክሩላታል:: ከዚህም በቀር፣ በኢትዮጵያና በጣልያን መካከል በ 1935 ዓ.ም የተጀመረው ጦርነት በ 1941 ዓ.ም በኢትዮጵያ ድል አድራጊነት ቆሟል ቢባልም፣

ኢትዮጵያ ከባለጋራዋ ከጣልያን ጋር እንዳችም የጦር ማቆሚያ ወይም የዕርቅ ውል ያልተፈራረመች መሆኗ መታወቅ አለበት ..... » ካሉ በኋላ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የጣልያን መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ ያቀረበው የጠላትነት ክስ መዘዙ ምን እንደሚሆን ለጉባኤው ያስረዱት እንደሚከተለው ነበር።

« ..... ኢትዮጵያ በዚህ የሠላም ጉባኤ ላይ እንድትገኝ በክብር የተጠራችው፣ ከፋሽስት ጋር ለብዙ ዓመታት ያለማቋረጥ የተዋጋች እና በመጨረሻም ድል አድርጋ ነፃነቷን ስለመለሰች፤ ከቀድሞው ጠላት ጋር በሚደረገው የዕርቅ ውል ተካፋይነቷ አጅግ አስፈላጊ መሆኑን የአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች አምነውበት ነው። ነገር ግን «የቀድሞው» እየተባለ የሚጠራው ጠላት፣ ዛሬም ጠላታችን ስለሆነ፣ በዚህ በተከበረው የሠላም ጉባኤ ላይ የጣልያን መልዕክተኛ በሰጠው መግለጫ ከኢትዮጵያ ጋር ዕርቅ የማይፈልግ መሆኑን አስምቶናል። ጣልያን ሠላም አለመፈለጉን ሲነግረን፣ ኢትዮጵያ ዕርቅ ይሻላል ብላ አትለምንም። ስለዚህ በዛሬው ዕለት ከፍ ላሉት ገዢዎ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በማስተላልፈው ቴሌግራም፣ ጣልያን ከኢትዮጵያ ጋር ዕርቅ አለመፈለጉን ስለገለጸልን፣ የታወቁት አርበኞችና ወታደሮቻችን ለማናቸውም ጉዳይ ዝግጅት እንዲያደርጉ እጠይቃለሁ። በዚህ በሠላም ጉባኤ ላይ ተካፋይ የሆናችሁት የተከበራችሁ መልዕክተኞች፣ በተለይም የአራቱ ኃያላን መንግሥታት ወኪሎች እንድትረዱልኝ የምፈልገው፣ በዚህ በጣልያን መንግሥት ቀስቃሽነት ኢትዮጵያ በምትወስደው እርምጃ በአገራችን ለሚኖሩት በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩት የጣልያን ተወላጆች ለደህንነታቸው ዋስትና መስጠት የማይቻል መሆኑን ነው ...... » በማለት የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ማስጠንቀቂያቸውን ሲወረውሩ፣ የእንግሊዝ መልዕክተኛ ጣልቃ ገብቶ የአቶ አክሊሉ ንግግር እንዲቆምና ስብሰባው ለግማሽ ሰዓት ሥራውን እንዲያቋርጥ ጠየቀ። ወዲያውም የእንግሊዝ፣ የአሜሪካና የፈረንሣይ መልዕክተኞች በኢትዮጵያና በጣልያን መልዕክተኞች መካከል ድርድር ጀመሩ። ይኸውም፣ የጣልያን መልዕክተኛ የዘባረቀውን አርሞ ይቅርታ እንዲጠይቅ፣ ኢትዮጵያም የወረወረችውን ዛቻ ከይቅርታ ጋር እንድትሰርዝ ነበር።

አቶ አክሊሉ በበኩላቸው ይቅርታ የሚያስጠይቅ ምክንያት የለኝም አሉ። ኢትዮጵያ በሚደረገው የዕርቅ ስምምነት ተካፋይ ለመሆን መገኘት አልነበረባትም ብሎ በቀጥታ ነቀፌታውን ያቀረበው የጣልያን መልዕክተኛ ነው። በዚህ ሁኔታ ጣልያን ከኢትዮጵያ ጋር ዕርቅ አያስፈልገኝም ያለው ያለጥርጥር እንደልማዱ ተንኮል አስቦብን ይሆናል በማለት፣ ኢትዮጵያ መዘጋጀት ያስፈልጋታል ብዬ መናገሬ በዛቻ ሊተረጐም አይገባም። ይቅርታ መጠየቅ ያለበት የጣልያን መልዕክተኛ ነው ብለው ተከራከሩ። በመሠረቱ የሶስቱ ኃያላን መንግሥታት ወኪሎች ጥፋተኛ ነው ብለው የፈረዱት በጣልያን መልዕክተኛ ላይ ነበር። ይልቁንም የእንግሊዝ መልዕክተኛ « ..... ኢትዮጵያውያኖች በጣልያን ላይ ያላቸው ጥላቻ ምን ያህል ሥር የሰደደ መሆኑን ታውቃለህ ወይ ? ....... በኢትዮጵያ ያሉትን ከሠላሣ ሺህ በላይ የሆኑትን የጣልያን ዜጐች የኢትዮጵያ አርበኞች በደም ፍላት አርደው ለአውሬ እንደሚሰጧቸው አይታይህም ወይ ? ..... » በማለት የጣልያኑን መልዕክተኛ አስደንግጦታል። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ የሰጡት መግለጫ ዛቻ አይደለም በማለት አቋማቸውን ሲያጠነክሩ፣ የጣልያን መልዕክተኛ ጥፋተኛው እሱ ብቻ ነው ተብሎ በይፋ ይቅርታ እንዲጠይቅ ምዕራባውያኖች ማስገደድ አልፈለጉም። በመጨረሻው በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው አስታራቂ መንገድ በመፈለግ፣



*« ...... ያለ ውዴታቸዉ በግዴታ፣ በኮሎኒያሊስት ጣልያን ተገንጥለው የተወሰዱት የኤርትራና የሱማሌ ሕዝቦች፣ ወደ እናት አገራቸው ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ፤ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የዓለምን ፍርድ ይጠይቃል ...... »*

አክሊሉ ሀብተወልድ

(ሐምሌ 1946 ፓሪስ)

1ኛ. የጣልያን መልዕክተኛ ስለ ኢትዮጵያ ተካፋይነት ያቀረበው ጥያቄ ትክክል አለመሆኑን እና ኢትዮጵያ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት መጠራቷ ተገቢ ነው በማለት የጉባኤው ሊቀመንበር ለስብሰባው እንዲያስረዳ፣

2ኛ. ኢትዮጵያ ከዚህ ቀደም ደጋግማ ባቀረበችው ሀሳብ መሠረት የፋሽስት መንግሥት በዓለም ላይ ሕገወጥ ጦርነት የጀመረው በጥቅምት 3 ቀን 1935 ዓ.ም ኢትዮጵያን በወጋ ጊዜ መሆኑ፣ ከጣልያን ጋር በሚፈረመው የዕርቅ ውል አንቀጽ 38 ላይ፣ "እንዲመዘገብ ስምምነት ተደርጐ፣ ለጊዜው ተቋርጦ የነበረው ስብሰባ እንዲቀጥል ተደረገ።

አቶ አክሊሉ፣ ምንም እንኳ እንደተመኙት፣ የሮማ መንግሥት ያደረገውን ስህተት አምኖ ራሱ ይቅርታ እንዲጠይቅ ባይደረግም፣ በሚዘጋጀው የዕርቅ ውል ጣልያን በዓለም ላይ የጫረው ጦርነት መነሻው፣ ኢትዮጵያን በወጋበት ቀን ጥቅምት 3 ቀን 1935 ዓ.ም እንዲሆን በመወሰኑ እጅግ ተደስተዋል።

# የግብፅ ጥያቄ

በኤርትራ ውስጥ በሀይማኖት በኩል ከክርስቲያኑ ይልቅ እስላሙ በቁጥር ይበልጣል እያሉ፣ ጣልያኖች በዓረብ አገሮች የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ ቀስ በቀስ በግብፅ የንጉሥ ፋሩክን መንግሥት ማንቃት ጀመረ። የጣልያን ፕሮፓጋንዳ ዋና ግቡ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ እስላሞች ስለሚጨቆኑ፣ አብዛኛው እስላም የሆነው የኤርትራ ሕዝብ በኃይለሥላሴ መንግሥት የተበደለ ነው በማለት የዓረብ አገሮች በሕብረት እንዲቃወሙ ነበር።

የግብፅ መንግሥት የራሱ ዜጋ በሆነው በዓረብ ሊግ ዋና ጸሐፊ በአብደል ራህማን አዛም (ABDEL - RAHMAN AZZAM) በኩል ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች ጉዳይ ሲከታተል፣ በመስከረም 1945 ዓ.ም ሎንዶን ላይ ለሚከፈተው የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ፣ ኤርትራና ሱማሌ ይመለሱልኝ ብላ ኢትዮጵያ ማመልከቻ ማቅረቧን ሰማ። ወዲያውም አብዱልራህማን አዛም ለአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ምክር ቤት በላከው ደብዳቤ፣ ሊቢያና ኤርትራ ነፃነት እንዲሰጣቸው የዓረብ ሊግ የሚደግፍ መሆኑን እና፣ እንዲሁም ይህ ሀሣብ እስከሚፈጸምበት ጊዜ ድረስ እነዚህ አገሮች በዓረብ መንግሥታት የሞግዚት አስተዳደር ለመቆየት እንደሚችሉ አስታወቀ። ይህ የዓረብ ሊግ ዋና ጸሐፊ ደብዳቤ ሎንዶን ደርሶ በምክር ቤቱ ሲታይ፣ የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ሊጉን የሚመለከተው አይደለም በማለት፣ ከስብሰባው አጀንዳ ላይ እንዳይመዘገብ ተደረገ።

የግብፅ መንግሥት ግን በበኩሉ፣ ከኤርትራ ግዛት ውስጥ የምፅዋ የባሕር በር የኔ ይዞታ የነበረ ነው በማለት፣ ለአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ደጋግሞ ስለአመለከተ፣ ፓሪስ በሚደረገው የሠላም ጉባኤ፣ ስለ ቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ ንግግር በሚደረግበት ጊዜ መልዕክተኛ ልኮ ሀሣቡን እንዲያመለክት ፈቀዱለት።

የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ምክር ቤት ይህንን ውሳኔ ለግብፅ መስጠቱን ኢትዮጵያ አላወቀችም ነበር። በዚያን ጊዜ በካይሮ የሚገኙት የኢትዮጵያ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ብላቴን ጌታ በላቸው ያደቴ እና፣ ከእሳቸውም ቀጥሎ

የሌጋሲዮኑ ጉዳይ ፈጻሚ የነበሩት አቶ ጋሻው ዘለቀ፣ ግብፅ ከኤርትራ ግዛት ምፅዋ የኔ ነው ብላ ፓሪስ እንደምትመጣ አልሰሙም።

በመስከረም 1946 ዓ.ም. ለኮሎኒዎችና ለግዛቶች ጉዳይ የሠላሙ ጉባኤ ባቋቋመው የፖለቲካ ኮሚሲዮን ላይ፤ የንጉሥ ፋሩክ ልዩ መልዕክተኛ መጥቶ « .... ምፅዋ የግብፅ ይዞታ የነበረ ግዛት ስለሆነ ለባለማብቱ ለግብፅ ማመለስ አለበት። ..... » የሚል ጥያቄ ሲያቀርብ፣ ለኢትዮጵያ መልዕክተኞች ያልተጠበቀ አዲስ ነገር ነበር። የንጉሥ ፋሩክ መልዕክተኛ መሠረታዊ ታሪኩን ለስብሰባው ሲያስረዳ፣ « ..... ይህ ምፅዋ የተባለው ወደብና አካባቢው፣ በጥንታዊው ዘመን የቱርክ ግዛት ሆኖ ለብዙ መቶ ዓመታት ከቆየ በኋላ ከ 1825 ዓ.ም እስከ 1885 ዓ.ም ድረስ፣ የግብፅ መንግሥት ይዞታ ሆኖ ሲተዳደር የነበረ ነው። .... ጣልያኖችም በ 1885 ዓ.ም በዚሁ በምፅዋ ወደብ በግብፆች ቦታ ተተክተው ሲሰፍሩ፣ ባለቤትነቱ የግብፅ መንግሥት መሆኑን አውቀው ነው። .... ከዚህም በላይ የምፅዋ አካባቢ ሕዝብ በሙሉ፣ በዘሩ፣ በሀይማኖቱና በባሕሉ፣ ከግብፆች የሚመሳሰልና የሚቀራረብ ነው እንጂ ከኢትዮጵያ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። .... » ካለ በኋላ፣ የተከበረው መልዕክተኛ ምፅዋ የግብፅ ሙብት ስለሆነ ለግብፅ እንዲመለስ የንጉሥ ፋሩክ ብርቱ ጥያቄ መሆኑን በጥብቅ አሳሰበ።

በኤርትራ ጉዳይ ግብፅም እንደ ጣልያን እውነተኛውን ታሪክ ሸፋፍኖ በፈጠራ ታሪክ በመተካት፣ ጉባኤውን ለማምታታት ስለሞከረች፤ ተገቢውን መልስ በቶሎ ማቅረብ የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ግዴታ ነበር።

« ..... የግብፅ መልዕክተኛ እንደጠቀሰው፣ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ከግራኝ መሐመድ ወረራ በኋላ ቱርኮች በምፅዋ የባሕር በር ጦር አስፍረው መቆየታቸውን የኢትዮጵያ መንግሥት ሀሰት ነው አይልም። እንዲሁም ከአሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ቱርኮች ምፅዋን ሲለቁ፣ ግብፆች ተተክተው ለጥቂት ዓመታት እንደከረሙ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አይክድም። ነገር ግን ቱርኮቹም ሆኑ ግብፆች በምፅዋ ሰፍረው በኖሩበት ዘመን የባሕር ወደቡ ለኢትዮጵያ የሚሰጠው አገልግሎትና የወደቡ አስተዳዳሪዎችም ለኢትዮጵያ መንግሥት የሚከፍሉት ታክስ ተቋርጦ የማያውቅ መሆኑን፣ የተከበረው መልዕክተኛ ሳይጠቅሰው ሸፋፍኖ በማለፉ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች እጅግ ተገርመዋል። ከዚህም በላይ ቱርኮቹም ሆኑ ግብፆቹ በተለያዩ ጊዜያቶች ከሰፈሩበት ከምፅዋ በር እየተነሱ የኤርትራን ደጋማ አውራጃዎች ለመያዝ ያደረጓቸውን ሙከራዎች፤ የኢትዮጵያ ነገሥታቶች በጦር ድል እያደረጉ ያባረሯቸው መሆኑን የተከበረው መልዕክተኛ መናገር አለመፈለጉ ግልጽ ነው። ቱርኮች በ 1589 ዓ.ም በአፄ ሠርጸ ድንግል ጊዜ፣ ግብፆች በ 1875 እና በ 1876 ዓ.ም በአፄ ዮሐንስ አራተኛ ዘመን፣ ድል መሆናቸው መታወቅ አለበት።

...... በኢትዮጵያ፣ በእንግሊዝና በግብፅ መንግሥታት መካከል ስፊ ድርድር ተደርጐ፣ ሰኔ 3 ቀን 1884 ዓ.ም አድዋ ከተማ ላይ በተፈረመው ውል፣ ምፅዋ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የባሕር በር መሆኑ ተረጋግጧል። ይህ የአድዋ ውል ከተፈረመ ከጥቂት ወራት በኋላ፣ የኮሎኒያሊስት ጣልያን ጦር ሲመጣባቸው፣ የግብፅ ወታደሮች በመካከል ፋንታ ፈርጥጠው በመልቀቃቸው፤ በስምምነቱ መሠረት ግብፆች ምፅዋን ለባለቤቷ ለኢትዮጵያ ለማስረከብ የገቡበትን ግዴታ ሳይፈጽሙ ቀርተዋል።

እንግዲህ ግብፅ በምፅዋ ላይ መብት አለኝ ብላ የቀረበችው በምን አግባብ ነው ? ..... በማለት፤ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ፤ ታሪኩን ለፍርድ በሚያመች መልክ ስለአቀረቡት፣ በስብሰባው ላይ የጠነከረ ክርክር ሳይደረግ፣ የቀረበው ማመልከቻ ተገቢ አይደለም ተብሎ የግብፅ ንጉሥ የግርማዊ ፋሩክ ልዩ መልዕክተኛ ባዶ እጁን በሰላም ወደ አገሩ ተመለሰ። ከፓሪሱ የሠላም ጉባኤ በኋላ፣ የኤርትራ ጉዳይ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ሲጠና፣ ቀጥሎም ጉዳዩ ወደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተዛውሮ በሚታይበት ጊዜ፣ የግብፅ መንግሥት በምፅዋ ላይ መብት አለኝ የሚለውን ጥያቄ ደግሞ ለማቅረብ አልሞከረም።

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰዉ፤ የግርማዊ ንጉሥ ፋሩክ መንግስት በኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያን ጥያቄ ለማሰናከል፣ በፓሪስ የሠላም ጉባኤ ላይ ይህን የመሰለዉን ማመልከቻ ያቀርባል ብሎ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግስት አልጠበቀም ነበር።

# የሠላም ጉባኤው ፍጻሜ

የአዶልፍ ሂትለር ግብረ አበር ለሆኑት አምስት የፋሽስት አገሮች፣ (ጣልያን፣ ሁንጋሪያ እና ቡልጋሪያ፤ ሩማንያ እና ፊንላንድ) የተዘጋጁትን የዕርቅ ስምምነቶች ለማጽደቅ፤ የሀያ አንድ (21) አገሮች መልዕክተኞች ለሁለት ወር ከአሥራ አምስት ቀን በፓሪስ ታሥረው መቆየት ግዴታ ሆነባቸው።

ይህ የሠላም ጉባኤ ረዥም ጊዜ የወሰደበት ዋናው ምክንያት በአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች መካከል፣ ምዕራባውያኖች በአንድ በኩል ሆነው፣ ሶቪየት ሕብረት በሌላ በኩል አፈንግጠ፣ ለየጥቅማቸው በማሰብ ሲነታረኩ በመቆየታቸው ነው እንጂ፤ የሚዘጋጁት የዕርቅ ውሎች ይህን ያህል የተወሳሰቡና አስቸጋሪዎች ሆነው አልነበረም። ከአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች ሌላ የጉባኤው ተካፋይ ከሆኑት አሥራ ሰባት (17) አገሮች መካከል፣ አሥራ ሁለቱ (12) የምዕራባውያን ደጋፊዎች ሲሆኑ፣ ቀሪዎቹ አምስቱ አገሮች የመስኮብ ተከታዮች ናቸው። ጉባኤው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ማናቸውም ጉዳይ በሁለት ሶስተኛ የድምፅ ብልጫ እንዲወሰን በአራቱ ኃያላኖች መካከል በተደረገው ስምምነት መሠረት፣ ሂሣቡ ሲታይ ምዕራባውያኖች አሥራ አምስት ድምፅ ሲያከማቹ፣ (15) ሶቪየት ሕብረት ከስድስት (6) የበለጠ ሊኖረው አልቻለም። በዚህ አሠራር ምዕራባውያኖቹ ሁልጊዜ የሚፈልጉትን ለማስፈጸም በቂ ድጋፍ አላቸው ማለት ነው።

የስታሊን መንግሥት የዓለምን አቋም ከለዋወጠው፣ ከ «ያልታ» ስብሰባ ጀምሮ፤ በምዕራባውያኖች ላይ የጠነከረ አቋም በመውሰድ በብዙ ረገድ የጠቀመው ስለሆነ፣ የበለጠ ለማግኘት ማስፈራራቱን መቀጠል አስፈላጊ መስሎ ታየው። በዚህ በሠላም ጉባኤ ላይ ማናቸውም ውሳኔ የሚጸድቀው በሁለት ሶስተኛው የድምጽ ብልጫ ነው ቢባልም፣ ዞሮ ዞሮ ተካፋይ ከሆኑት አገሮች መካከል አብዛኛዎቹ የምዕራብ ወገኖች በመሆናቸው፣ ሶቪየት ሕብረት ምንም ኃይል እንደሌለው ሙሴ ሞሎቶቭ ስለተረዳው፤ ለዚህ አንድ አፍራሽ መንገድ መፍጠር አለብኝ ብሎ ተነሣ። ይኸውም፣ ማናቸውም ጉዳይ በጉባኤው የሚወሰነው በሁለት ሶስተኛው የድምፅ ብልጫ መሆኑ ሳይለወጥ፣ ወሳኝ በሆነው በሁለት ሶስተኛው የድጋፍ ወይም የተቃውሞ ቁጥር ውስጥ፣ የሶቪየት ሕብረት ድምፅ ከሌለበት ሊጸድቅ አይችልም

የሚል ነበር:: ይህ ምን ማለት ነው ? በሌላ አነጋገር፤ ለምሣሌ ጣልያን ለሶቪየት ሕብረት የምትከፍለው የጦር ካሣ መጠኑ መቀነስ አለበት የሚል ሀሳብ ለጉባኤው ቀርቦ አሥራ አምስት አገሮች ቢደግፉትና ስድስቱ ቢቃወሙት፤ የሶቪየት ሕብረት ድምፅ ከደጋፊዎቹ መካከል ካልተገኘ አንቀጹ አይጸድቅም ማለት ነው::

በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ በልማድ እንደሚታወቀው፣ አንዳንድ ጊዜ ተጋበኛ ፋከራውን ከመጠን በላይ ሲያንዛዛ፤ ፈሪውም ቢሆን ሆሞቱ ይቆርጥለት እና የመጣው ይምጣ ብሎ ሲመክት፣ ባልጠበቀው መንገድ አሸናፊ ይሆናል:: ዩናይትድ ስቴትስና ታላቋ ብሪታንያም፣ የሙሲ ሞሎቶቭን አይጥ የበጣጠሰው ጠባይ ማስታመም ስለሰለቻቸው፤ በድምፅ ብልጫ የሚደረገውን ውሳኔ ካልተቀበልክ ደህና ሁን ብለው ለማሰናበት የቀረጡ መሆናቸውን አሳዩት:: የስታሊን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርም በጀመረው ማስፈራራት ለመቀጠል እንደማይችል ሲያውቀው፤ አፈግፍጉ እሺ በማለት ፋንታ፣ ለምክር ሞስኮ ተጠርቻለሁ ብሎ ጉባኤውን አቋርጦ በድንገት ሄደ:: በዚህ ጊዜ ብዙዎቹ መልዕክተኞች፤ ሙሲ ኒየት ወደ አገሩ የሄደው ያለ ጥርጥር አባ ነብሮ ስታሊን ተቆጥቶ ስለሆነ፤ የሠላም ጉባኤው ከሁለት ወር ድካም በኋላ መፍረሱ ነው በማለት ተጨንቀው ነበር:: ምዕራባውያኖችም በበኩላቸው መስኮብ በዕርቁ ስምምነቶች ላይ አልካፈልም ካለ፣ በቀረጠ መንፈስ የሚወስዱትን እርምጃ ሲያቀነባብሩ፣ አሁንም በድንገት ሙሲ ሞሎቶቭ ከሞስኮ ተመልሶ በስብሰባው አዳራሽ ወንበሩን ያዘ:: ብዙ ሀተታ ሳያበዛ ለአምስቱ አገሮች የተዘጋጁት ውሎች በሁለት ሰስተኛው የድምፅ ብልጫ እንዲጸድቁ መስማማቱን ገልጾ፣ ጉባኤው ሥራውን እንዲያፋጥንና ከአንድ ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲጨርስ ሀሳብ አቀረበ:: እንደተባለውም ሙሲ ኒየት ወደ አገሩ ሄዶ በአባ ነብሮ ተባርኮ ከተመለሰ በኋላ፣ በሰባት ቀናት ውስጥ ለአምስት የቀድሞ የፋሽስት አገሮች የተዘገጁትን ሁለት መቶ ሀያ ሰስት (223) አንቀጾችና ሠላሣ ሰስት (33) አባሪዎች፣ ጉባኤው ያለ አንዳች እንቅፋት በድምፅ ብልጫ ማጽደቅ ቻለ::

ሐምሌ 29 ቀን 1946 ዓ.ም የተከፈተው ይህ የሠላም ጉባኤ፣ ከሰባ አምስት ቀናቶች በኋላ ጥቅምት 15 ቀን 1946 ዓ.ም ሥራውን ሲፈጽም፣ ባለመታደል በዓለም የታወቁት የዜና ማሠራጫ ድርጅቶችና ጋዜጦች እንደሚጠበቀው ሊያጅቡትና ሲያሚሙቁለት ሳይችሉ ቀሩ:: ምክንያቱም በኑረምበርግ (NUREMBERG) የተቋቋመው የአራቱ ኃያላን ፍርድ ቤት የሙት በቃ የፈረደባቸው አሥራ አንዱ የናዚ ባለሥልጣኖች፤ ቅጣታቸው በስቅላት የተፈጸመው ጥቅምት 15 ቀን ሲነጋጋ ስለሆነ፤ የዓለም ሕዝብ ጆሮ ወደ ኑረምበርግ ስለአመራ ነበር::

በኑረምበርግ ከተሰቀሉት አሥሩ ከፍተኛ የናዚ መንግሥት ባለሥልጣኖች መካከል፤ የጀርመንን ድል መሆን አስታውቆ የጦርነት ማቆሚያ ስምምነቱን የፈረመው ማርሻል ዊልሄልም ከይተል፣ (WILHELM KEITEL) የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበረውና በ 1939 ዓ.ም አውሮፓ በጦርነት እሣት ውስጥ ስትጠልቅ፣ ከሙሲ ሞሎቶቭ ጋር የወዳጅነት ጤና ጽዋ የተለዋወጠው ቮን ሪበንትሮፕ፣ (VON RIBBENTROP) የናዚ አይዲዎሎጂ ፈላስፋ የነበረው አልፍሬድ ሮዘንበርግ (ALFRED ROSENBERG) ይገኙበታል:: የኑረምበርግ ፍርድ ቤት ዳኝነት አፈጻጸምና የስቅላቱ ታሪክ የየጋዜጦቹን ዋና አምዶች ስለአጥለቀለቀት፤ ሁለት ወር ተኩል የፈጀው የሠላም ጉባኤ ውጤት በሁለተኛው ደረጃ ዜና ከመቅረብ የበለጠ ዕድል ሲያገኝ አልቻለም:: የፓሪሱ ስብሰባ እስከዚህ የተጓተተውና ሲፈጸምም የጋለ

ፕሮፓጋንዳ ለማግኘት ያልታደለው፣ በሙሴ ኒየት ቆጭባራነትና ወልጋዳነት መሆኑን፣ በመጨረሻው የየአገሩ መልዕክተኞች በሙሉ አምነውበታል።

የጉባኤው ውጤት በብዙ ረገድ ሲመዘን ለኢትዮጵያ የሚበቃ ደስታ ሰጥቶ፣ አዲሲቷ ሬፐብሊክ ለተባለችው ጣልያን፣ ከፍ ያለ ብስጭትና ሀዘን ያስከተለ ሆነ። በተዘጋጀው የዕርቅ ውል ላይ፣ 1ኛ. « የቀድሞ ጠላት » ተብሎ መጠራቱ እንዲቀርለት፤ (ጣልያን የዓለም ሕዝብ ጠላት ስላልሆነ) 2ኛ. ሶስቱም « የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቹን በገዛ ፈቃዱ መልቀቁን አረጋግጧል» የሚለው ቃል እንዲሰረዝለት፣ 3ኛ. የቲቶ ዩጉዝላቪያ ባላንጣ ሆኖ የቀረበበት የትሪየስቴ ግዛት እንዳይነካበት፣ 4ኛ. በጦር ካሣ ክፍያ ጉዳይ፣ ለአንዳንድ አገሮች ለምሣሌ እንደ ኢትዮጵያ ለመሣሰሉት መክፈል እንዳይኖርበት፣ ለሌሎቹም ቢሆን አቅሙ የሚፈቅደውን አጥንቶ እስኪያቀርብ ድረስ ያልሆነ ተመን እንዳይከነዳበት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ደጋስፐሪ ብዙ ጩኸት አሰምቶ ነበር።

በአራቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ምክር ቤት የተረቀቀውን ውል፣ የጉባኤው ተካፋዮች እያንዳንዱ አንቀጽ እየተነጠሉቸው በድምጽ ብልጫ ሲያጸድቁ፣ የጣልያን መንግሥት እንዲሻሻልለት ወይም እንዲለወጥለት ያቀረበላቸውን አቤቱታዎች አላስታወሱለትም።

በስምምነቱ መግቢያ ላይ «የቀድሞ ጠላት» ተብሎ ለጣልያን የተሰጠው የመጠሪያ ማዕረግ አልተነካም። ሶስቱንም የቀድሞ ቅኝ ግዛቶቹን በገዛ ፈቃዱ መልቀቁን የሚያረጋግጠው አልተለወጠም። በጦር ካሣም ጉዳይ ጣልያን ግፍ ለፈጸመባቸው አገሮች (ኢትዮጵያ ጭምር) እንዲከፍል የተተመነው ሶስት መቶ ስልሣ ሚሊዮን ($360,000,000) የአሜሪካን ዶላር አልተቀነሰም ወይም አልተሻሻለም። በትሪየስቴም ጉዳይ ምንም እንኳን በወዳጁ በፈረንሣይ ብርታት ለጊዜው ከተማው በኢንተርናሽናል አስተዳደር እንዲቆይ ቢደረግም፤ ቬኔሲያ ጁሊያ (VENEZIA GIULIA) ከተባለው የሰሜን ጣልያን አውራጃ ግዛት፣ ግማሹ ተቆርጦ ለዩጉዝላቪያ እንዲሰጥ፣ የተወሰነውን ማስቀረት አልተቻለም።

ሌላው ደግሞ ሲኞር ደጋስፐሪን እና መልዕክተኞቹን እጅግ አድርጐ ያበሳጫቸው፤ ኢትዮጵያ የሠላም ጉባኤ ተካፋይ መሆኗ ብቻ ሳይሆን፣ በስብሰባው ላይ በየጉዳዩ ጣልቃ እየገባች የጣልያንን መንግሥት ለማጥቃት የምታደርገው ዲስኩር ነበር። « ..... አሁን እፊታችን የቀረበው የደጋስፐሪ መንግሥት ፀረ ፋሽስት ይሁን ኔዎ ፋሽስት፤ ራዲካል ይሁን ሶሲያሊስት፣ ጣልያን የዓለም ጠላትና ብዙ ግፍ የፈጸመ ወንጀለኛ አገር መሆኑን አይለውጠውም ... » እያለ፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኛ አክሊሉ ሀብተወልድ፣ ሕገ ወጥ በሆነ ቋንቋ ሲሳደብ ጉባኤው ዝም ብሎ ማዳመጡ እጅግ አሳዛኝ ነው ብለዋል። በእነ ደጋስፐሪ አስተያየት ይህ የሠላም ጉባኤ ሲሰናዳ ከተደረጉት መሠረታዊ ስህተቶች አንዱ፣ ከ1936 ዓ.ም ጀምሮ የጣልያን ኮሎኒ መሆኗ በኦፊሲየል የታወቀላት ኢትዮጵያ፣ በ1940 ዓ.ም በዓለም ጦርነት ውስጥ ከተዋጉት አገሮች መካከል ተቆጥራ የዕርቁ ውል ፈራሚ እንድትሆን መደረጉ ነው። ከዚህ አልፎ ደግሞ ሀያ አምስት ሚሊዮን ($25,000,000) የአሜሪካን ዶላር የጦር ካሣ እንዲከፈላት ጉባኤው ያደረገው ውሳኔ ጨርሶ የሚገባት አልነበረም። ምንም እንኳን የፋሽስት መንግሥት ኢትዮጵያን ለመያዝ ያደረገውን ጦርነት ባንደግፍም፤ አገሩ በኮሎኒ አስተዳደር በቆየበት በአምስቱ ዓመታት ውስጥ፣ ጣልያኖች የፈጸሙትን ከፍ ያለ የልማት ሥራ መርሣት አንችልም። የአገሪቱ አውራጃዎች ከዋናው ከተማ ጋር በአውራ ጎዳና

መንገዶች የተገናኙት፣ መሸጋገሪያ ድልድዮች የተዘረጉት፤ ሆስፒታሎችና ሕንፃዎች በብዛት የተሰሩት፣ የኢንዱስትሪ ልማቶች የተቋቋሙት፤ በጣልያኖች ሞያ መሆኑን፤ ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያውያኖች ራሳቸው ሊክዱት አይችሉም:: የኢትዮጵያ ጉዳይ የጦር ካሣ በማግኘት ብቻ አይቆምም:: አሁን ደግሞ ኤርትራና ሱማሌ የኔ ስለሆኑ እንዲመለሱልኝ ብላ ጩኸቷን በያለበት ማሰማት ይዛለች:: ይህንን ሁኔታ አዲስቷ ሪፑብሊክ በቸልታ መመልከት አይገባትም:: በሚል የቅሬታና የሀዘን እንጉርጉሮ እነ ሲኞር ደጋስፐሪ ወደ ሮም ተመለሱ::

ኢትዮጵያ ግን በዚህ ጉባኤ ላይ ተካፋይ ለመሆን ያደረገችው ጥረት ተሳክቶላት በመገኘቷ በውጤቱ ብዙ ተጠቅማለች::

*መጀመሪያ፡-*

ጣልያንን ወግተው ድል ካደረጉት አገሮች ጋር ተሠልፋ፣ የዕርቁን ውል ፈራሚ በመሆኗ ከፍ ያለ ክብርና ደስታ ሰጥቷታል::

ሁለተኛ፡-

የቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች ተመልሰው ለጣልያን እንዳይሰጡ ለመከራከርና፣ የጥንት አካሎቿ የሆኑት ኤርትራና ሱማሌ እንዲመለሱላት የታሪክ ማስረጃዎቿን በማቅረብ ለመከራከር አስችሏታል::

ሶስተኛ፡-

ባልተጠበቀ ሰዓት፤ ከኤርትራ ግዛት የምፅዋ ባለቤት እኔ ነኝ፡ ብሎ የመጣውን የግብፅ መልዕክተኛ፣ ጥያቄው መሠረት የሌለው መሆኑን በማስረዳቷ፣ ጉባኤው የቀረበውን ማመልከቻ ሠርዞላታል::

አራተኛ፡-

ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ ለፈጸመው ግፍ ሀያ አምስት ሚሊዮን(25,000.000) የአሜሪካ ዶላር የጦር ካሣ እንዲከፍላትና፣ ከአገሯ ዘርፎ የወሰዳቸውንም ታላላቅ የታሪክ ቅርሶችና ንብረቶች በሙሉ እንዲመልስ፣ በዕርቁ ውል ላይ ተመዝግቦላታል:: *

እንደ እውነቱ ከሆነ ኢትዮጵያ በዚህ በሠላም ጉባኤ ላይ ባትካፈል ኖሮ፤ ከጣልያን ጋር የዕርቅ ስምምነት ለመፈራረም ቀጥታ የሆነ ድርድር ማድረግ ስለምትገደድ፤ ብዙ ችግር ይገጥማት ነበር:: ንግግሩም በሁለቱ አገሮች መካከል በሚደረግበት ጊዜ ፈረሱ ላይ የሚወጣው ጣልያን ስለሆነ፣ ኢትዮጵያ ብቻዋን መብቷን የምታስከብርበት አቅም እንደማይኖራት የታወቀ ነው:: አዲሶቹ የጣልያን መሪዎችም፣ የፋሽስት ሸሚዛቸውን ለይስሙላ የለወጡት በቅርቡ ስለሆነ፣ ለኢትዮጵያ የጦር ካሣ ለመክፈልና የዘረፉትንም የታሪክ ቅርስ የሆኑ ንብረቶች ለመመለስ ጨርሶ አይስማሙም ነበር:: ኢትዮጵያን በብዙ ረገድ የጠቀማት በዚህ የሠላም ጉባኤ ላይ ተካፋይ መሆኗ ነው::

* (የጦር ካሣ ለዩጉዝላቪያ 125 ሚሊዮን ለግሪክ መቶ አምስት ሚሊዮን ለመስኮብ መቶ ሚሊዮን ለኢትዮጵያ ሀያ አምስት ሚሊዮን ለአልባኒያ አምስት ሚሊዮን)

# የአራቱ ኃያላን መርማሪ ኮሚሽን በኤርትራ

በፓሪሱ የሠላም ጉባኤ ውሳኔ መሠረት፣ የካቲት 15 ቀን 1947 ዓ.ም የጣልያን የዕርቅ ስምምነት በሀያ አንድ አገሮች (ኢትዮጵያ ጭምር) ከተፈረመ በኋላ፣ ውሉ ጸድቆ በሥራ ላይ መዋል የሚጀምረው ከመስከረም 15 ቀን 1947 ዓ.ም ጀምሮ ነው::

~

የአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች ከመስከረም 15 ቀን 1947 ዓ.ም እስከ መስከረም 15 ቀን 1948 ድረስ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ለነበሩት አገሮች የወደፊት አስተዳደር አንድ መፍትሔ መስጠት ካልቻሉ፤ ጉዳዩን ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አቅርበው እንዲያስወስኑ የፓሪሱ የሠላም ጉባኤ ጠይቋቸዋል:: በዚህ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የኤርትራን፣ የሊቢያንና የሱማሌን ጉዳይ መወሰን እንዲቻል፣ በነዚህ አገሮች እየተዘዋወረ የሕዝቡን ፍላጐት አጣርቶ ሀሳብ የሚያቀርብላቸው፣ አንድ የመርማሪ ኮሚሽን ቡድን ለማቋቋም የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ተስማሙ::

እንደሚታወቀው፤ አራቱ ታላላቅ መንግሥታቶች በጦርነቱ ዘመን በመካከላቸው የተመሠረተው መግባባትና መተባበር፤ የሠላሙ ዘመን ሲጀምር ሊቀጥል አልቻለም:: አሜሪካ፣ እንግሊዝና ፈረንሣይ በሊበራሊዝም ዕምነታቸው ማርክሲዝምን እና ሌኒንዝምን ሲቃወሙ፣ ሶቪየት ሕብረትና ተከታዮቹ የምዕራብን ካፒታሊዝም አስተዳደር በግልጽ ማውገዝ ጀመሩ:: በተለይ በ 1947 ዓ.ም የነበረው የዓለም ስዕል እንደሚያሳየው፤ ምዕራባውያኖችም ሆኑ ኮሚኒስቶቹ በታናናሽ አገሮች ላይ የሚኖራቸውን ተሰሚነትና ኃይል ለማዳበር በመሽቀዳደም ላይ ነበሩ:: የሂትለር ግብረ አበር ከሆነው ከጣልያን ጋር የሚደረገው የሠላም ውል ሳይፈረም ረዥም ጊዜ የወሰደው፤ በዚሁ በአራቱ ታላላቅ መንግሥታቶች መካከል በተፈጠረው መለያየትና መቃቃር ምክንያት ነበር:: አሁንም የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ተገቢውን መፍትሔ በቶሎ ከማግኘት የሚዘገየው፤ በእነዚሁ በአራቱ ኃያላኖች አለመግባባት መሆኑን በየጊዜው የሚፈጸሙት ድርጊቶች ያስረዳሉ::

ከአሜሪካ፣ ከእንግሊዝ፣ ከፈረንሣይና ከመስኮብ የተሰየሙት የመርማሪ ኮሚሽን አባሎች ሥራቸውን የሚጀምሩት በኤርትራ እንዲሆን ሲወሰን፤ ተግባራቸውን የሚያከናውኑት በምን አኳኋን እንደሆነ፣ በዝርዝር የተጠና ፕሮግራም አልነበራቸውም:: በኤርትራ የሚገኘው የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ወታደራዊ አስተዳደር፣ የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን አሥመራ የሚደርሰው ያለ አንዳች ፕሮግራም ባዶ እጁን መሆኑን ስለአወቀ፣ በራሱ ፈቃድ እርምጃ ወስዶ፣ የኤርትራን ሕዝብ አስተያየት ለማዳመጥ የሚቻልበትን ዕቅድ አዘጋጀ:: ይኸውም በመላ ኤርትራ ከቀበሌ እስከ አውራጃ ድረስ ነዋሪው ሕዝብ እንደራሴዎቹን እንዲመርጥና፣ ተመራጮቹም ለኮሚሽኑ እየቀረቡ የሕዝቡን ፍላጐት እንዲገልጡ ማድረግ ነበር:: በመሠረቱ በጣልያን የኮሎኒ አስተዳደር ዘመን ይህን የመሰለውን የሕዝብ ወኪሎች መምረጥና መላክ ኤርትራውያኖች የሚያውቁት ስለነበረ፣ ከእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር የተጠየቁትን ለመፈጸም እንግዳ ነገር አልሆነባቸውም::

ህዳር 8 ቀን 1947 ዓ.ም የአራቱ ኃያላን መርማሪ ኮሚሽን አባሎች አሥመራ ሲደርሱ፤ የእንግሊዝ አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ቁጥራቸው ከሶስት ሺህ

በላይ የሆኑ የሕዝብ ወኪሎችን አስመርጦ፤ በኤርትራም ያሉትን ልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በቅደም ተከተል መዝግቦ ጠበቃቸው:: በዚህ በተደረገው ዝግጅት የአሜሪካ እና የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኞች ደስታቸውንና ምሥጋናቸውን ሲገልጡ፤ የፈረንሣይና የመስኮብ ወኪሎች እጅግ ቅር ተሰኙ:: እንደሚታወቀው የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች፣ በሊቢያ ውስጥ በፈረንሣይ ከሚተዳደረው « ፌዘን » ከተባለው አውራጃ በስተቀር፣ ሌሎቹ ትሪፖሊታንያ እና ሲረናይከ፣ በምሥራቅ አፍሪካ ኤርትራ እና ሱማሌ፣ የተያዙት በታላቋ ብሪታንያ ወታደራዊ አድሚኒስትሬሽን ነው:: የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን ከሉንዶን ከመነሳቱ በፊት፣ በየአገሩ የህዝብ እንደራሴዎች ተመርጠው፣ የልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ቅደም ተከተል ይዘው ይጠብቃሉ ተብሎ ሲነገር፣ እንግሊዞች በተንኮለኛው ጥበባቸው ይህንን ያዘጋጁት ኮሚሲዮኑን አወናብደው የራሳቸውን ፍላጐት ለማስፈጸም ነው፤ በማለት ፈረንሣይና መስኮብ ሥጋት አደረባቸው::

የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን ገና ከጠዋቱ ሥራውን ሲጀምር፣ መልዕክተኞቹ ሁለት ቦታ ተከፍለው ያሳዩት የሀሣብ ልዩነት፣ በመሠረቱ በአራቱም ታላላቆች መካከል በቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ መግባባት አለመኖሩን ወይም ሊኖር እንደማይችል የሚያመለክት ሆነ:: ይህ በቡድኑ መካከል የተፈጠረው መለያየት፣ ዓለምን በሁለት በስነጠቀው በትልቁ ጉዳይ፣ በካፒታሊዝምና በኮሙኒዝም አይዲዎሎጂ ምክንያት ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ ፈረንሣይ ከአንግሎ አሜሪካ ግሩፕ ተገንጥላ ከመስኮብ ጋር አትቆምም ነበር:: ነገር ግን በቅኝ ግዛቶቹ ጉዳይ፤ መልዕክተኞቹ ከየመንግሥቶቻቸው የተሰጣቸው ልዩ መምሪያ፣ ዳኝነታቸውን ለየአገራቸው የፖለቲካ ጥቅም እንዲያውሉት ስለሆነ፣ በዚያን ሰዓት መስኮብና ፈረንሣይ የአንግሎ አሜሪካኖችን ሕብረት አብረው የሚቃወሙበት ተመሣሣይ ምክንያት አግኝተዋል:: የሶቪየት ሕብረት መልዕክተኛ፣ የሕዝብ ነፃነት ከሚከበርበ ትና ዲሞክራሲ ከሰፈነበት ዓለም የመጣ ይመስል፤ የተደረገው የሕዝብ ወኪሎች ምርጫ የዲሞክራሲን ሥርዓት የተከተለ አይደለም በማለት <u>ከፍተኛ ጩኸቱን አሰማ::</u> የፈረንሣዩም መልዕክተኛ በበኩሉ ምንም እንኳን አነጋገሩ የዲፕሎማሲን ወዝ የተከተለ ቢሆንም፤ «የአራቱ ኃያላን መንግሥታት እንደራሴዎች በታዛቢነት ያልተገኙበት የሕዝብ ወኪሎች ምርጫ መጠናቀቁ ትክክል አይደለም » አለ::

ፈረንሣይና መስኮብ የሚፈልጉት ምንድን ነው ? ..... በኤርትራም ሆነ በሌላው አገር እያንዳንዱ ሕዝብ በቀጥታ ሀሳቡን የሚገልጥበት የሬፈራንዶም ሥርዓት ማከናወን የሚቻል ቢሆን ኖሮ፣ መርማሪ ኮሚሽን የሚባል ቡድን ማቋቋም አያስፈልግም ነበር:: እነዚህ በጣልያን የኮሉኒ አስተዳደር ተጨቁነው የኖሩ ሕዝቦች፣ የምዕራብን የዲሞክራሲ ሥርዓት ተቀብለው በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመፈጸም አቅም እንደሌላቸው ለማንም የተሰወረ አይደለም:: ስለዚህ፤ ከዚህ ቀደም በልማድ ሲሠራበት እንደነበረው በየቀበሌው ያለው ነዋሪ ሕዝብ፣ ወኪሎቹን እንዲመርጥና በነዚህም ያገር ሽማግሌዎችና የሕዝብ ተጠሪዎች አማካኝነት፣ መርማሪው ኮሚሽን ተግባሩን እንዲፈጽም ተዘጋጅቶ ጠብቆታል:: እንደ ደንቡ ከሆነ፣ ቡድኑ የተሰጠውን ኃላፊነት ሲቀበል፣ በምን አኳኋን እንደሚፈጽም ፕላኑን በቅድሚያ አዘጋጅቶ ማስታወቅ ነበረበት:: ይህ ሳይደረግ በመቅረቱ በኮሚሲዮኑ ሥራ ላይ ችግር እንዳይፈጠር አስበው፤ የአስተዳደሩ ባለሥልጣኖች ማናቸውንም ጉዳይ አሰናድተው በመጠበቃቸው፣ ነቀፌታ ለማቅረብ የሚደረገው ጥረት ምን ለማሻሻል ? ወይም ምን ጉድሎ ምን ለመጨመር ነው ? .... በማለት፤ የአሜሪካና የእንግሊዝ ወኪሎች አምርረው ስለተቆጡ፣ ፈረንሣይና መስኮብ ዝግጅቱን አሜን ብለው መቀበል ግዴታ ሆነባቸው::

እነዚህ የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ተብለው የተመደቡት ሰዎች፣ የእያንዳንዳቸው የሕይወት ታሪክ ሲታይ፣ ይህን ለመሰለው የኃላፊነት ተግባር አብዛኞዎቹ ጨርሶ ብቁ አለመሆናቸውን ለመገንዘብ አያስቸግርም::

1. የአሜሪካው መልዕክተኛ ሚስተር ጆን ኡተር (JOHN UTTER) የባንክ ሥራ ልምድ ያለው ሲሆን፤ ለጥቂት ጊዜ በሰሜን አፍሪካ፣ ጉዞ አድርጐ ነበር ይባላል::

2. ፈረንሣዊ ሙሴ ኤቲየን ደ- ሮዚዬ፤ (ETIENNE DE-ROSIERS) በዲፕሎማሲ ሥራ በምዕራብ አውሮፓ የቆየ ቢሆንም፣ አፍሪካን በተለይም የምሥራቁን ክፍል አይቶ አያውቅም::

3. የሞስኮቡ ሚስተር አርተሚ ፌዎዶሮቭ (ARTEMY FEODOROV) ከሁሉም የባሰ ነው:: ሞያውና እስካሁንም የሠራው በውትድርና ብቻ ሲሆን፣ አፍሪካ የሚባለውን አህጉር ጨርሶ አይቶ አያውቅም::

4. የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኛ ፍራንክ ስታፎርድ (FRANK STAFFORD) የእንግሊዝ የኮሎኒ ሚኒስቴር ባልደረባ የነበረ እና፣ በጦርነቱም ዘመን በኢትዮጵያና በኤርትራ ተመድቦ ያገለገለ ኦፊሰር ነው:: የኢትዮጵያ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ፤ ሚስተር ስታፎርድ የገንዘብ ሚኒስትር የአቶ ይልማ ዴሬሣ አማካሪ ሆኖ ለሁለት ዓመት የሠራ በመሆኑ፤ ስለአገራችን ያለው ኤክስፔሪያንስ ከሌሎቹ ጓደኞቹ ጋር ሲመዘን እጅግ የላቀ ሆኖ ይገኛል::

የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን የኤርትራን ሕዝብ ፍላጐትና ስሜት ለመረዳት የሚችለው የታላቋ ብሪታንያ ወታደራዊ አስተዳደር ባዘጋጀለት ፕሮግራም መሠረት ብቻ ስለሆነ፤ የቡድኑ የመጀመሪያው ሥራ በአሥመራ ከተማ፣ የልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችን በየተራ እንዲያነጋግር ተወሰነ:: እነዚህም፤

- የማህበረ ፍቅሪ ሀገር (የአንድነት የአገር ፍቅር ማህበር)
- የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ (የእስላም ሊግ)
- የሊበራል ፕሮግሬሲስት
- የፕሮ ኢጣልያ (የጣልያን አፍቃሪዎች)
- የምዕዋ የእስላም ሊግ ማህበር፤ ናቸው::

በትግሪኛ ቋንቋ «ማህበረ ፍቅሪ ሀገር» የተባለው የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝቦች አንድነት ማህበር የተቋቋመው፣ ኢትዮጵያ ከፋሽስት እንደተላቀቀች ወዲያውኑ፤ በሚያዝያ 1941 ዓ.ም ስለሆነ፣ በአገሩ ውስጥ ከተፈጠሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ፣ የመጀመሪያውና እጅግ የታወቀው ትልቁ ድርጅት ነው:: የአንድነት ማህበር ሲቋቋም፤ ዓላማው ያለ አንዳች ገደብ ከእናት አገራችን



በአዲስ አበባ ነዋሪ የሆኑት የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ማህበር አባሎች

(1941- 1952 ዓ.ም)

ከኢትዮጵያ ጋር እንዋሀድ በሚል ጽኑ ሀሳብ የተመሠረተ ሲሆን፣ በዚያን ጊዜ የመላው ኤርትራን ሕዝብ ድጋፍ እንዳገኘ የሚቆጠር መሆኑን የሚክድ የለም።

« ማህበረ ፍቅሪ ሀገር » ክርስቲያኖቹንና እስላሞቹን በማስተባበር፣ ከዓላማውና ከግቡ ለመድረስ የሚያስችለው ትልቅ ኃይል የያዘ መሆኑ ሲታያቸው፣ የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳዳሪዎች ከፍ ያለ ሥጋት አደረባቸው። በ 1946 ዓ.ም በፓሪስ የተካሔደው የሠላም ጉባኤ በሰጠው ውሳኔ መሠረት፣ የአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች፣ የኤርትራንና የሌሎቹንም የጣልያን ቅኝ ግዛት ሕዝቦች ፍላጐታቸውን የሚያጠና መርማሪ ኮሚሽን ከመላካቸው በፊት፣ «ማህበረ ፍቅሪን» ለማዳከም እንግሊዞች ልዩ ልዩ የተንኮል ዘዴዎችን አዘጋጁ።

በመጀመሪያ « የማህበረ ፍቅሪ ሀገር » አባል ሆነው ሲታገሉ ከነበሩት እስላሞች መካከል፣ እንደ እነ ኢብራሂም ሡልጣን የመሳሰሉትን በጥቅም ደልለው፣ የኢትዮጵያ አንድነት ተቃዋሚዎች እንዲሆኑ እርዳታ አደረጉላቸው።

በኤርትራ፣ በከሠላና በተስነይ ያለው የካትሚያ ማህበረሰብ መሥራች ልጅ የሆኑት፣ በኃይማኖት መሪነታቸው እጅግ በታወቁት፣ <u>በሰይድ አቡበከር ኤል ሞርጋኒ ሊቀመንበርነት፣</u> በጥር ወር 1947 ዓ.ም በከረን ከተማ እጅግ ከፍ ያለ የእስላሞች ስብሰባ ተደርጐ « የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ » የፖለቲካ ፓርቲ ተቋቋመ። ዓላማውም፣

> መጀመሪያ፣ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ዓይነት የዘር፣ የባሕልና፣ የታሪክ ግንኙነት የሌላት መሆኑን ለዓለም ለማሳወቅ፤
>
> ሁለተኛ፣ ኤርትራ ለተወሰነ ዘመን በታላቋ ብሪታንያ፣ ይህም ካልተቻለ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሞግዚት አስተዳደር ከቆየች በኋላ ነፃነቷ እንዲሰጣት፤ የሚል ነበር።

በዚሁ ስብሰባ ላይ ቀድሞ የ «ማህበረ ፍቅሪ ሀገር» አባል የነበረው ኢብራሂም ሡልጣን አዲስ ለተመሠረተው የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ ፓርቲ፤ ዋና ጸሐፊ ሆኖ ተመደበ።

« የሞርጋኒ » ቤተሰቦች በኤርትራ የእስልምና ሐዋርያ በመሆን ዝናን ያተረፉ በመሆናቸው በዚህ ከረን ላይ በተመሠረተው ፓርቲ አማካይነት የመላውን የኤርትራን የእስልምና ተከታዮች በአንድ አቋም ላይ ለማስተባበር ይቻላል፣ የሚል ተስፋ እና እምነት አድሮባቸው ነበር። ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ ውጤቱ እንደታየው፤ እነ « ኤል ሞርጋኒ » የተመኙት አልተፈጸመላቸውም። የቤን አሞር ጐሣ መሪ ደግለል፣ የኢምቤሬኒው ሼክ አል አሚን፤ የሀባብ ባላባት ከንቲባ አስማን ሀዳድ፣ የአድሼክ ጐሣ መሪ መሐመድ አማር ፓሻ እና ሌሎችም ታላላቅ እስላሞች የማህበረ ፍቅሪ ሀገር አባል መሆናቸውንአላቋረጡም። እንደዚሁም የኤርትራንና የኢትዮጵያን አንድነት እምነት አልለወጡም። በኢብራሂም ሡልጣን ዋና ጸሐፊነት እንዲመራ የተመሠረተው፤ ይህ የእስላም ሊግ ድርጅት ጉዞውን የቀጠለው በመጀመሪያው ደረጃ፣ የኢትዮጵያና እንዲሁም የጣልያን ተቃዋሚ ሆኖ፣ ከእንግሊዞች ጋር ወዳጅነቱን በመግለጽ ነበር። ያለ እንዳች ገደብ « ኢትዮጵያ ወይም ሞት » ብሎ የተነሣውን ያገር ፍቅር አንድነት ማህበርን ለማዳከም፤ እንግሊዞች ይህንን የእስላም ሊግ ድርጅት በማቋቋም ብቻ አልተወሰኑም።

ክርስቲያኖቹም መካከል የሀሳብ ልዩነት እንዲፈጠር በጣም አስፈላጊ መሆኑን ስለአመኑበት፣ « .... ኤርትራ በሸዋ ዘውድ ሥልጣን እጅ መውደቅ የለባትም:: እኛ የኤርትራ ሕዝቦች ከኢትዮጵያ ጋር እንድንቀላቀል የሚያስፈልገን ከሆነ፣ መብታችንን የሚያስከብርልን የተለየ ውል ያስፈልገናል ... » እያሉ ሲፎልሉ የነበሩትን የነ ደጃች ተሰማ አስበሮምን ቤተሰቦች በመቀስቀስና በማበረታታት፣«ሊበራል ፕሮግሬስስት» የተባለው የፖለቲካ ፓርቲ እንዲቋቋም አደረጉ:: በአካለ ጉዛይ አውራጃ የታወቁትን እነዚህን በኢትዮጵያ ላይ የሚያንገራግሩ ቤተሰቦች መሣሪያ ለማድረግ፣ በታላቋ ብሪታንያ ንጉሥ መልካም ፈቃድ ደጃች ተሰማ አስበሮም የራስነት ማዕረግ ሲቀበሉ፣ ለልጃቸውም ለፊታውራሪ አብርሃ ተሰማ ደግሞ ደጃዝማችነት ተሰጠ::

ራስ ተሰማ እና ልጃቸው ደጃዝማች አብርሃ በኢትዮጵያ ሥርዓት እጅግ የተከበረውን የመጠሪያ ማዕረግ፤ ከእንግሊዝ አስተዳዳሪዎች እጅ ነስተው የተቀበሉት በጋለ ደስታ እንደነበረ ይነገርላቸዋል:: በዚህ አኳኋን የኢትዮጵያን ወገና ባሕል በአንድ በኩል እያጠበቁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያዊ መሆንን እንፈልግም እያሉ እደባባይ ለመውጣት፣ ለራስ ተሰማ አስበሮምና ለቤተሰቦቻቸው ምን ያህል አሣፋሪ መሆኑ ግልጽ ነበር:: በመሠረቱ የተሰማ አስበሮም ቤተሰቦች ገርገር፣ ለኤርትራ የወደፊት ዕድል ምን እንደሚሻል ሕዝብ የሚከተለው መሠረት የጨበጠ ፕላን አልነበራቸውም:: በመጀመሪያ ደረጃ ያሳዩት ተቃውሞ፣ ያለአንዳች ገደብ ከኢትዮጵያ ጋር አንዋሀድ የሚለውን የማህበረ ፍቅሪ ሀገርን ሀሳብ ነበር:: ቀጥሎ ደግሞ፣ እንግሊዞች ሲያቀርቧቸውና ሲረዷቸው፣ ኤርትራ በታላቋ ብሪታንያ ሞግዚትነት አሥር ዓመት ከተዳደረች በኋላ ነፃነቷን ማግኘት ትችላለች የሚል አቋጣጫ ያዙ:: የነ ራስ ተሰማ ሀሳብ በዚህ ብቻ አልቆመም:: በዘር በቋንቋና በባሕል የሚመሳሰለው የትግራይ ሕዝብ ከኤርትራ ጋር ተቀላቅሎ « ትልቁ ትግራይ » የሚባል አገር ለመመሥረት ይቻላል የሚለውን የእንግሊዞችን ዕቅድ ለመከተል ተነስተናል አሉ::

የነ ራስ ተሰማ ንቅናቄ ይሀን በመሳሰለ በተምታታ ሀሳብ በሚዋዥቅበት ሰዓት፣ የመምህርነትና የጋዜጠኝነት ሞያ ልምድ ያላቸው አቶ ወልደአብ ወልደማርያም፣ ከአገር ፍቅር እንድነት ማህበር የእባልነት ቦታቸውን ለቅቀው ወደ እነ ራስ ተሰማ አስበሮም ቤተሰቦች ሲዛወሩ፣ «ሊበራል ፕሮግሬሲስት» የተባለው ፓርቲ ኤርትራ ለኤርትራውያን በሚል መፈክር አንድ ዓይነት መልክ ይዞ መታየት ጀመረ:: የወልደአብ ወልደማርያም ከነ አስበሮሞች ጋር መሰለፍ፣ «ሊበራል ፕሮግሬሲስት» የተባለውን ፓርቲ መፍጠር ብቻ ሳይሆን፣ ለዓላማውና ለግቡ መሳካት የእንግሊዞችን ሙሉ ድጋፍና ትብብር ማግኘት ችሏል:: አቶ ወልደአብ ቀደም ሲል በአሥመራ የብሪቲሽ ኢንፎርሜሽን ሰርቪስ በየሣምንቱ ለሚያወጣው ጋዜጣ አዘጋጅ የነበሩ በመሆናቸው፣ ከእንግሊዞች ጋር በመግባባት ለፓርቲው ከፍ ያለ ፕሮፓጋንዳ ለማሠራጨት አልተቸገሩም::

እንግዲህ ከ 1941 ዓ.ም ጀምሮ የአብዛኛውን የኤርትራ ሕዝብ ድጋፍ ይዞ ከኢትዮጵያ ጋር ለመዋሀድ ሲታገል የቆየውን «ማህበረ ፍቅሪ ሀገርን» ለመቃወም በእንግሊዞች እርዳታ የተቋቋሙት እነዚህ ሁለቱ የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ እና የሊበራል ፕሮግሬሲስት ፓርቲዎች ሲሆኑ፤ ሌሎች ደግሞ ኢትዮጵያን እንፈልግም የሚል ጩኸት እንዲያሰሙ፣ በጣልያን ገንዘብ በፍጥነት የተፈጠሩ ጥቃቅን ቡድኖች ተመዝግበው ቀረቡ:: ከነዚህም አንዱ «ፕሮ ኢታሊያ» የተባለው የጣልያንን ስሜት ይዞ ለጣልያን የቆመ ድርጅት ነው:: ይህ ፓርቲ በኤርትራ

ውስጥ የሚኖሩትን ጣሊያኖችና ከእነሱም የተወለዱትን ክልሶች፣ እንዲሁም በውትድርና ኮሎኒያሊስት ጣልያንን ያገለገሉትን ጡረተኞች በጠቅላላውም ሹምባሾችንና ሙንጣዞችን የሚሰበስብ ነው:: « ፕሮ ኢታልያ » ስሙ እንደሚያስረዳው፣ ኤርትራን የፈጠረ እና የወደፊት ዕድሏንም ማዘጋጀት የሚችለው ጣልያን ስለሆነ፣ ኤርትራ ከኮሎኒያሊስት ጣልያን መለየት የለባትም ብሎ የጌታውን ባንዲራ ያነገበ ነው:: በእንግሊዞችና በጣልያኖች እርዳታ የተቋቋሙት እነዚህ ልዩ ልዩ ፓርቲዎች፣ ለአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን፤ ዓላማቸውንና ግባቸውን ለማለጽ የተሰናዱት፣ ምንም እንኳን በሞግዚት ስለሚያስተዳድራቸው ኮሎኒያሊስት የእያንዳንዳቸው ምርጫ የተለያየ ቢሆንም፤ « የማህበረ ፍቅሪ ሀገርን » ድርጅት ለመቃወም ሁሉም በአንድነት የተሰለፉ ናቸው::

ጣልያኖች በቀጥታ፣ እንግሊዞች በሥውር ጉዳና የሚያደርጉት ጥረት፣ በመጀመሪያ ደረጃ ማህበረ ፍቅሪ ሀገርን በመጨቆን፣ ብዙዎቹ ኤርትራውያኖች ለመርማሪው ኮሚሽን የሚገልጹትን አስተያየት በየጥቅማቸው መስከ ለማሠማራት ይቻላል ብለው ነበር:: ይሁን እንጂ ምንም እንኳን በብዙ አቅጣጫ የሚወረወርባቸው ጥቃት ቢበዛባቸው፣ የአንድነት ማህበር አባሎች እስከ መጨረሻው በቆራጥነት መቋቋምን እንጂ፣ ተዳክመው መታየትን አልፈለጉም::

# የኤርትራ የፖለቲካ መሪዎች ከመርማሪው ኮሚሽን ጋር

## <u>ሀ/ የአገር ፍቅር አንድነት ማህበር፤</u>

ህዳር 17 ቀን 1947 ዓ.ም፤ የአራቱ ኃያላን መርማሪ ኮሚሽን ቡድን፣ በኤርትራ የሚንቀሳቀሱትን የልዩ ልዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀሳብ የሚያዳምጥበት ቀን ስለሆነ፣ <u>የመጀመሪያው ፕሮግራም ለአገር ፍቅር አንድነት ማህበር እንዲሰጥ ተወሰነ::</u>

| | |
|---|---|
| ደጃዝማች በየነ ባራኪ | ፕሬዚዳንት |
| አቶ ተድላ ባይሩ | ዋና ጸሐፊ |
| ፊታውራሪ ፀሐይ አደም | ገንዘብ ያዥ፤ |
| ሼህ ሱሌማን ኤልዲን አህመድ | አባል |
| ሠይድ አህመድ ሁሴን አዮቲ | አባል |

ሠልፋቸውን አሳምረው በሥርዓትና በወግ በተጠሩበት ሰዓት ቀረቡ::

የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን የዕለቱ ሊቀመንበር የሆነው የመስከቡ ወኪል ሙሴ አርተሚ ፌዎዶሮቭ (ARTEMY FEODOROV) አንድነቶችን ሲቀበል ባደረገው የመክፈቻ ንግግር፤ « .... ወደ እኛ ዘንድ እንድትመጡ የተደረገው ሀሳባችሁን በግልጽና ፍጹም በሆነ ነፃ መንፈስ እንድትናገሩ ነው:: ..... ፍጹም ነፃ በሆነ




የኤርትራና የኢትዮጵያ አንድነት ማህበር አባሎች ለመርማሪው ኮሚሽን ስሜታቸውን ሲገልጹ::
(ኅዳር 1947)

መንፈስ በምትገልጡት ሀሳብ፤ ከአስተዳደሩ (ከእንግሊዞች) በኩል ምንም ዓይነት ጥቃት እንደማይደርስባችሁ እናረጋግጥላችኋለን ...... » አለ:: የመስኩቡ ወኪል ይህን የተናገረው፣ እንግሊዞችን ለመንካት በግል ሀሳቡ ተመርቶ ነው እንጂ፤ ከሚሲዮኑ የተስማማበት መግለጫ አልነበረም::

የአንድነቶች ድርጅት ፕሬዚዳንት፣ ደጃዝማች በየነ ባራኪ በነጭ ያገር ልብስ አሸብርቀው፣ የኢትዮጵያን ባንዲራ አንግተው፣ ከፍ ያለ ግርማ ሞገስ ባለው አቀራረብ በሰጡት መልስ፤ « ... ለተነሳንበት ለኢትዮጵያዊነት ዓላማችን በምናደርገው ጥረት፤ ከአስተዳደሩ በኩል ምንም ዓይነት ችግር አይደርስባችሁም የሚል የዋስትና ቃል ስለነገራችሁን እናመሰግናችኋለን:: ..... እኛም የአስተዳደሩ ክፍል ችግር ይፈጥርብናል ወይም ያጠቃናል ብለን የማንሰጋ መሆናችንን እናረጋግጥላችኋለን:: ከአስተዳደሩም ሆነ ከየትኛውም አቅጣጫ ችግርና እንቅፋት ቢገጥመንም ባይገጥመንም፣ ነፃ በሆነው መንፈሳችን ላይ ፍርሃት ሳናስገባ፣ ደካማነት ሳይሰማን፣ በዛሬው ዕለት ለእናንተ ለኃያላን መንግሥታት እንደራሴዎች ለማስገንዘብ የምንፈልገው፤ ሳንወድ በግድ በኮሎኒያሊስት ጣልያን የተነጠቅነው ኢትዮጵያዊነታችን እንዲመለስልን እስከ ሞት የቆረጥንበት መሆኑን ብቻ ነው:: ...» ካሉ በኋላ፤ ዋናው ጸሐፊ አቶ ተድላ ባይሩ ዝርዝሩን መግለጫ እንዲያቀርቡ ጠየቁ:: ተድላ ባይሩ በሰጡት መግለጫ፤ የመርማሪው ኮሚሽን አባሎች የኤርትራን የወደፊት ዕድል ለመወሰን በሚያደርጉት ጥናት፣ ከዚህ የሚከተሉትን ዋና ዋና ጉዳዮች በቅድሚያ እንዲገነዘቡት አመለከቱ::

1. የኤርትራ ሕዝብ ትውልዱንና ታሪኩን መሠረት አድርጐ የጠየቀውን ኢትዮጵያዊነት ለማስፈጸም፣ ይህ የአገር ፍቅር አንድነት ድርጅት የተቋቋመው፣ ጣልያን ከመላ ኢትዮጵያ በተባረረ ማግሥት በግንቦት 1941 ዓ.ም ነው::

2. ያገር ፍቅር አንድነት ድርጅታችን፤ ከ 1941 ዓ.ም ጀምሮ ዓላማውን ከግቡ ለማድረስ የሚያደርገውን ጥረት ለመቃወም፣ ዛሬ ከእናንተ ፊት የሚቀርቡት የእስላም ሊግና ሊበራል ፕሮግሬሲስት የተባሉት ፓርቲዎች የተቋቋሙት፣ የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ወደ ኤርትራ መምጣቱ ከታወቀ በኋላ ነው::

3. በተለይ « ፕሮ ኢጣልያ » ተብሎ በሮማ መንግሥት በጀት የሚመራው፣ ማህበር በድንገት ብቅ ያለው፣ የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን ከሎንዶን ተነስቶ ወደ አሥመራ ጉዞውን ሲጀምር ነው::

« ፕሮ ኢጣልያ » ስሙ እንደሚያመለክተው ኤርትራ ከኮሎኒያሊስት ጣልያን እጅ መውጣት የለባትም የሚል ነው::

4. የራቢጣ ኤል ኢስላሚያ የተባለው የእስላም ሊግ፤ አንድ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በውጭ መንግሥት እርዳታ በተቋቋመ ጊዜ፣ ከምዕራባዊው ቆላ ሕዝብ አብዛኛው አባል ሆኖ የተመዘገበው፣ የድርጅቱ ዋና ዓላማ የእስልምና ሀይማኖትን ለማስፋፋትና በተለይ ክርስቲያኖች በሚበዙበት ክፍለ ሀገር እስላሞች እንዳይበደሉ ይከላከላል የሚል ፕሮፓጋንዳ ስለተነዛ ነው:: እንደ እውነቱ ከሆነም የምዕራባዊው ቆላ ኤርትራዊ ሕዝብ፤ ፕሮፓጋንዳ ስለበዛበት የሀይማኖት ጭቆና ይደርስብኝ ይሆን ? ብሎ በጥርጣሬ ከመስጋቱም በስተቀር፣ ኢትዮጵያዊነቱን አይክድም:: የዚህ የእስላም ሊግ መሪዎችም ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለንም፤ ኢትዮጵያንም አንፈልግም ብለው የሚጮሁት፤ በ1941 ዓ.ም

የአንድነት ማህበራችን ሲቋቋም መሥራች አባሎች ሆነው ብዙ አገልግሎት የሰጡን ናቸው:: የኃያላን መንግሥታት ወኪሎች እንደምታውቁት፣ የአንድነት ድርጅታችን «ኤርትራን ጣልያን ተመልሶ ይግዛት ወይም የዛሬ ስድስት ዓመት የተጀመረው የእንግሊዝ አስተዳደር ይቀጥል አይልም» የድርጅቱ ዓላማ በዚህ አቋሙ ህብት ካላቸው ከውጭ መንግሥታት አንዳች እርዳታ አያገኝም:: ቢቀርብለትም አይቀበልም:: የእስላም ሊግና የሊበራል ፓርቲዎች ግን፣ ኢትዮጵያን ስንቃወም የውጭ እርዳታ እናገኛለን በማለት፣ ስለ ኤርትራ የወደፊት ዕድል የሚያቀርቡት ሀሳብ ሁሉ ለግላቸው ከሚያልሙት ጥቅም ጋር የተያያዘ መሆኑን እናንተ ክቡራን ዳኞች እንደምትረዱት ሙሉ ተስፋችን ነው::

5. የአራቱ ኃያላን መንግሥታት ዳኞች ለኤርትራ የወደፊት ዕድል ትክክለኛ ውሳኔ መስጠት የሚችሉት፣ የአብዛኛው የኤርትራ ሕዝብ ጥያቄና ጽኑ ፍላጎት ምን መሆኑን በትክክል ሲያውቁት ብቻ ነው:: ይህ ሕዝብ በመከራውም ሆነ በሠላሙ ዘመን፣ የኢትዮጵያዊነት ስሜቱን ጠብቆ የቆየ፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሆነውን ሰንደቅ ዓላማ ለብሶ የኖረ ነው:: ይህ ሕዝብ በዘሩና በታሪኩ፣ በባሕሉና በኢኮኖሚ ሕይወቱ፣ ከመሠረት አገሩ ከኢትዮጵያ ተለይቶ መኖር እንደማይችል፣ ክቡራን ዳኞች እንደምትረዱት አንጠራጠርም .... »

ከዚህ መግለጫ በኋላ፣ የኮሚሽኑ አባሎች ልዩ ልዩ መስቀለኛ ጥያቄዎች በማቅረብ ፋታ ባይሰጧቸውም፣ አቶ ተድላ ጨዋ በሆነ አቀራረብ ስሜታቸውን ለመቆጣጠርና በረጋ መንፈስ አስፈላጊ መስሎ የታያቸውን ሁሉ መልስ ከመስጠት አልተዳከሙም:: ሆኖም ከአሜሪካኑ መልዕክተኛ የቀረበላቸውን አንድ ከባድ ጥያቄ ወቶሎ ለመመለስ ለአቶ ተድላ ባይሩ ቀላል አልነበረም::

ጥያቄው፣ « .... ኤርትራ ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ በኮሎኒያሊስት ጣልያን በጦር ኃይል ተነጥቃ የተወሰደች ነች እያለ፣ የአንድነት ፓርቲያችሁ ሰፊው ይናገራል:: ይህ እውነት ከሆነ በ 1896 ዓ.ም ከአድዋ ድል በኋላ የኢትዮጵያ እና በጣልያን መካከል በተፈረመው የሠላም ውል፣ ንጉሥ ምኒልክ በአሸናፊ ደረጃ ላይ መገኘታቸውን እያወቁ፣ ኤርትራ የጣልያን ግዛት መሆኗን ለምን ሲሉ በፊርማቸው አጸደቁ? ..... » የሚለው ጥያቄ ነበር:: እንደሚታወቀው አብዛኛዎቹ የኤርትራ ተወላጆች አፄ ምኒልክ ሸጡን ለወጡን በሚል መንፈስ የደጉ በመሆናቸው፣ ትክክለኛውን ምክንያት ተመራምሮ ለማወቅ ጥረት አላደረጉም:: አቶ ተድላም በግል አስተያየታቸው ምኒልክን መጥላታቸው የታወቀ ቢሆንም፣ ለአሜሪካኑ ጥያቄ በሰጡት መልስ የግል ዕምነታቸውን ሸፋፍነው ለማምለጥ ሞክረዋል:: « ..... ኮሎኒያሊስት ጣልያን በጦር ኃይል ተዘጋጅቶ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ላይ ገንጥሎ ለመውሰዱና ቅኝ ግዛቱ ለማድረጉ የተረጋገጠ ታሪክ ስለሆነ የተለየ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም:: ...... ይህም የተፈጸመው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ ዮሐንስ ኳራተኛ፣ በሌላው ግዛታቸው በኩል ከውጭ ከመጣባቸው ጦር ጋር ሲዋጉ በጦር ሜዳ በሞቱበትና፣ የንጉሠ ነገሥቱ ወራሽ ማን መሆናቸው ታውቆ አገሩ ባልተረጋጋበት ጊዜ ነው:: ከአፄ ዮሐንስ በኋላ ኢትዮጵያን የያዙት ንጉሥ ምኒልክ የ 1896 ዓ.ም ውል ያደረጉት ኮሎኒያሊስት ጣልያን ኤርትራን ቅኝ ግዛቱ አድርጐ ከያዘ ከአሥር ዓመታት በኋላ መሆኑ መታወቅ አለበት ..... » ሲሉ የማህበረ ፍቅረ ሀገር ዋና ጸሐፊ የሰጡትን መልስ የአሜሪካው መልዕክተኛ በጥሞና ሲያዳምጥ፣ የፈረንሣዩ ያሾፍ እንደነበረ አንድ የምዕራብ ጋዜጠኛ ጠቅሶታል:: የፈረንሣዩ መልዕክተኛ ያቀረባቸው አምስት ጥያቄዎች፣ አንዳቸውም ክብደት ያላቸው ወይም ዓይነተኛ ግምት የሚሰጣቸው

አልነበሩም:: ለምሣሌ ያህል አንዱ ጥያቄ « ...... የአንድነት ማህበር አባል ሆነው የተመዘገቡት ሁሉ፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር እንድትቀላቀል የሚያምኑ ናቸው ወይ ? .... » የሚል ነበር:: በዚህ ጥያቄ ፕሬዚዳንቱ ደጃዝማች በየነ ባራኪ ተናደው በሰጡት መልስ፤ « .... በኢትዮጵያዊነቱ የሚያምንና የቆረጠ ካልሆነ በስተቀር፣ ሌላ ሀሳብ ካለው በምን ምክንያት የአንድነት ማህበራችን አባል ሆኖ ይመዘገባል ? ..... » ብለው መልሱን ሰጥተውታል::

በጠቅላላው ህዳር 17 ቀን 1947 ዓ.ም ከመርማሪው ኮሚሽን ጋር በተደረገው ስፊ ውይይት፣ የአንድነት መሪዎች በሚያምኑበት ዓላማ እስከ መጨረሻው ለመዝለቅ ያሳዩት የቆራጥነት መንፈስ፤ በዳኞቹ ላይ አንድ ዓይነት ከፍተኛ ግምት አሳድሮባቸዋል::

<u>ለ/ የሊበራል ፕሬግሬሲስት ፓርቲ</u>

ጥቅምት 18 ቀን 1947 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በፊት፤

| | |
|---|---|
| 1. ራስ ተሰማ አስበሮም | ፕሬዚዳንት |
| 2. ግራዝማች ሥዩም ማሾ | ዋና ጸሐፊ |
| 3. ደጃዝማች አብርሃ ተሰማ | አባል |
| 4. ደጃዝማች ስብሐቱ ዮሐንስ | አባል |
| 5. አዝማች ካሱ መልኬ | አባል |
| 6. ግራዝማች በየነ ካህሣይ | አባል ቀርበዋል:: |

የፓርቲው ፕሬዚዳንት ራስ ተሰማ አስበሮም ለኮሚሽኑ ከሰጡት ስፊ መግለጫ ውስጥ፤ ቁም ነገሮቹ የሚከተሉት ነበሩ::

« .... በአፄ ዮሐንስ ዘመን የባዕድ መንግሥት ከውጪ መጥቶ ከኢትዮጵያ ላይ ቆርሶ የወሰደው አገር የለም:: ጣልያን ኤርትራን ቅኝ ግዛቱ ያደረገው፣ አፄ ዮሐንስ ከሞቱ በኋላ የኢትዮጵያን ሥልጣን የተረከቡት ንጉሥ ምኒልክ በገንዘብ ስለሸጡለት ነው:: ..... እንደሚታወቀው የተሸጠ ዕቃ በማናቸውም መንገድ እንደማይመለስ ሁሉ፣ ዛሬም የኢትዮጵያ መንግሥት ከሃምሣ ዓመት በፊት የሸጥኩት አገር ይመለስልኝ ማለት አይችልም:: ..... የኢትዮጵያ መንግሥት ኤርትራን በግዴታ ካልወሰድኩ ብሎ የሚታገል መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው:: ይህ መንግሥት በትግራይ ወንድሞቻችን ላይ የመሠረተው የግፍ አስተዳደር በጣም የሚያሳዝን ስለሆነ፤ ይህ አስከፊ ዕድል በኛም በኤርትራውያኖች ላይ እንዲደርስብን አንፈልግም:: ..... የትግራይ ሕዝብ ጤናው አይጠበቅለትም፣ ትምህርት አያገኝም፣ ኑሮው እንዲሻሻል አይታሰብለትም:: ስለዚህ እኛ ኤርትራውያን የሸዋ አስተዳደር ከሚወድቅብን፤ ቀይ ባሕራችን ውስጥ ተዘፍቀን ሕይወታችን ቢያልፍ እንመርጣለን:: ..... የኤርትራና የትግራይ ሕዝቦች አንድ ዓይነት ዘርና አንድ ዓይነት ባሕል ያላቸው፤ አንድ ዓይነት ቋንቋ የሚናገሩ ስለሆኑ፣ በአንድነት ተዋህደው ነፃ መንግሥት ለማቋቋም እንዲወስንላቸው አጥብቀን እንፈልጋለን::



የኤርትራ ኢትዮጵያ አንድነት ያገር ፍቅር ማህበር ፕሬዚዳንት ሆነው ብዙ የታገሉት ደጃዝማች በየነ ባራኪ። (ኋላ ራስ)

«...... ለዓለም መንግሥታት ማስገንዘብ የምንፈልገው፣ በኮሎኒያሊስት ጣልያን የተነጠቅነው ኢትዮጵያዊነታችን እንዲመለስልን እስከ ሞት የቆረጥንበት ጉዳይ መሆኑን ብቻ ነው ...... »

(በየነ ባራኪ ኅዳር 1947 ዓ.ም)

የሁለቱ ሕዝቦች መዋሀድ የማይቻል ነው ከተባለ፣ ኤርትራ ለብቻዋ ነፃነቷን አግኝታ ከአውሮፓ አገሮች እርዳታ እያገኘች ለመኖር እንዲፈቀድላት እንጠይቃለን:: ...... »

ከዚህ በላይ እንደሚታየው ራስ ተሰማ አስበሮም ለመርማሪው ኮሚሽን በሰጡት መግለጫ፣ የኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀል የሚቃወሙት፣ በዘመኑ የነበረውን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንግሥት አስተዳደር አንቀበልም በማለት ይመስላል:: የሊበራል ፓርቲ ግን ለኮሚሽኑ ባቀረበው የጽሑፍ አቤቱታ፣ ኢትዮጵያና ኤርትራ በዘርም ሆነ በቋንቋ፣ የተለያዩ ሕዝቦች መሆናቸውንና አብረውም ለመኖር የሚችሉበት መንገድ አለመኖሩን በሰፊው ገልጿል:: ኤርትራን የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ከተረከበበት ካለፉት ስድስት ዓመታት ወዲህ፣ ለሕዝቡ ሕይወት መሻሻል ብዙ እርምጃዎች መወሰዳቸውን፣ ፓርቲው ባቀረበው ጽሑፍ ስለተናገረ፣ እነዚህ የተፈጸሙት መልካም ሥራዎች ምንና ምን መሆናቸውን ራስ ተሰማ ባጭሩ እንዲያስረዱት የአሜሪካው መልዕክተኛ ጠየቃቸው::

ኤርትራውያኖች በትምህርት እንዲያድጉ፣ በአስተዳደር ሥርዓት እንዲሰለጥኑ፣ ለኃላፊነት ደረጃ ብቁ እንዲሆኑ፣ ትክክለኛ ፍርድ እንዲያገኙ፣ የእንግሊዝ ባለሥልጣኖች የወሰዱት እርምጃ ከፍ ያለ መሆኑን ከዘረዘሩ በኋላ፣ « ...... እኛ ኤርትራውያኖች በነፃነት መተዳደር ብቁ እስከምንሆንበት ጊዜ ድረስ፣ አሁን ያለው የእንግሊዝ አስተዳደር ቢቀጥልልን ደስታችን ከፍ ያለ ይሆናል:: ...... » ሲሉ ከታላቋ ብሪታንያ የራስነት ማዕረግ የተሰጣቸው ተሰማ አስበሮም ወደ መሬት ዝቅ ብለው ትሁት ልመናቸውን አቀረቡ:: በመጨረሻው የፈረንሣዩ መልዕክተኛ ለራስ ተሰማ ልጅ ለደጃዝማች አብርሃ ተሰማ አንድ የተለየ ጥያቄ አቀረበላቸው:: ይኸውም፣ « ..... ኤርትራን ጣልያን በሚገዛበት ጊዜ የናንተ ቤተሰብ በሙሉ፣ በጥሩ ምቾት ይኖር እንደነበረ ለምተናል:: ይህ እውነት ከሆነ፣ ዛሬ ለወደፊቱ አስተዳደር የሚሻላችሁን እንድትመርጡ ስትጠየቁ፣ በምን ምክንያት ጣልያን እንዲመለስላችሁ አላመለከታችሁም ? ... » የሚል ነበር::

የእንግሊዝ ደጃዝማች፣ የጣልያን ፊታውራሪ የሆኑት አብርሃ ተሰማ መልሱን ሲሰጡ፣ « .... በዓለም ጋዜጣ የሰማነው፣ ጣልያን ቅኝ ግዛቶቿን በሙሉ በግዴታ እንድትለቅ የተፈረደባትና የተባበሩት መንግሥታትም አባል እንዳትሆን የተከለከለች ስለሆነ፣ ወደ ኤርትራ የመመለስ ዕድል አይኖራትም ብለን ነው ...... » አሉ::

በእነዚህ በአካለ ጉዛይ ፊውዳል መኳንንቶች የሚመራው ሊበራል ፕሮግሬሲስት የተባለው ፓርቲ፣ ስሙና ግቡ አብሮ አለመሄዱን፣ የፕሬዚዳንቱ የራስ ተሰማና የልጃቸው የደጃች አብርሃ መግለጫዎች ያስረዳሉ:: የተሰማ አስበሮምና የቤተሰቦቻቸው ትልቁ ጥረት፣ ከኤርትራ ይልቅ በመጀመሪያ የራሳቸውን ጥቅም ማባረር ስለሆነ፣ የሊበራልን ፓርቲ በመሠረቱት በነ ወልደአብ ወልደማርያም አስተያየት አልተመሩም:: ጣልያን ተመልሶ ይግዛችሁ ቢባል፣ ወይም ደግሞ እንግሊዞች እንደጀመሩት ይቀጥሉ ተብሎ ቢወሰን፣ የአካለ ጉዛይ መኳንንቶች በእልልታ እንደሚቀበሉ የተረጋገጠ ነበር::

ሐ/ የእስሥላም ሊግ፤

ጥቅምት 18 ቀን ከእኩለ ቀን በኋላ፤

1. ኢብራሂም ሡልጣን አሊ የሊጉ ዋና ጸሐፊ
2. ከብሪ አብደልቃድር የአሥመራ ወኪል
3. ሰይድ እስማን ሆጥ የምፅዋ ወኪል
4. ቃዲ ሙሣ አደም የከረን ወኪል
5. ሐጂ ሱሌማን አህመድ አባል
6. ደጃዝማች ሐሰን ዓሊ አባል ቀርበዋል።

በ 1941 ዓ.ም ያገር ፍቅር አንድነት ማህበር ሲመሠረት፣ ከመጀመሪያዎቹ አባሎች አንዱ የነበረው ኢብራሂም ሡልጣን፣ ዛሬ በእስላም ሊግ ስም ሆኖ ባደረገው ንግግር፣ የገለጻቸው ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ነበሩ።

1. « ..... የኤርትራ ሕዝብ ሁለት ሶስተኛው እስላም ነው። የክርስቲያኑ ክፍል እጅግ ቢበዛ አንድ ሶስተኛው ቢሆን ነው። ስለዚህ ለአገሪቱ የወደፊት ዕድል የአብዛኛውን ሕዝብ ሀሳብ ይዞ የቀረበው የእስላም ሊግ ፓርቲያችን ስለሆነ፤ ለመላው የኤርትራ ሕዝብ ተጠሪነቱንና በሕዝቡም ስም ለመናገር የሚችል መሆኑን፤ የአራቱ ኃያላን መንግሥታት እንዲያውቁልን እንጠይቃለን።

2. ..... ያገር ፍቅር አንድነት እየተባለ ከሚጠራው ድርጅት አባሎች መካከል፣ አብዛኛዎቹ ኤርትራውያኖች ያልሆኑ፣ ከውጭ የመጡ የኢትዮጵያ ተወላጆች መሆናቸውን ኮሚሽኑ እንዲገነዘብልን እንፈልጋለን።

3. ...... የእስላም ሊግ ፓርቲ የተመሠረተው ለኤርትራ ሕዝብ ነፃነትን ለመጠየቅ ነው። ነገር ግን ታላላቅ መንግሥታቶች ኤርትራ ነፃ መንግሥት ሆና ለመተዳደር አልደረሰችም ካሉ፤ ለተወሰነ ዘመን በእንግሊዝ ሞግዚትነት እንድትቆይ የእስላም ሊግ ፓርቲያችን ይስማማል። .... »

የእስላም ሊግ ዋና ጸሐፊ የመግቢያ ንግግሩን ከፈጸመ በኋላ፣ በአንዳንድ የኮሚሽኑ አባሎች የቀረቡት ዋና ዋና ጥያቄዎችና ከኢብራሂም ሡልጣን የተሰጡት መልሶች የሚከተሉት ናቸው።

የአሜሪካ መልዕክተኛ፣
የእስላም ሊግ በሰጠው መግለጫ ለኤርትራ ሞግዚትነት እንግሊዝን እመርጣለሁ ብሏል። ጣልያን ያልተፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው?

ኢብራሂም ሡልጣን፣
እኛ ኤርትራውያኖች እስካሁን ካየነው ሁሉ የተሻለ ሆኖ ያገኘነው፤ የእንግሊዝን አስተዳደር ነው። ለምሣሌ ታላቋ ብሪታንያ ጐረቤታችንን ሱዳንን ለሃምሣ ዓመታት ስታስተዳድር፣ ሕዝቡን አስተምራ ለኃላፊነት ደረጃ ብቁ እንዲሆን አድርሳዋለች። ጣልያኖች ግን ኤርትራን ለሃምሣ ዓመታት ሲገዙ፣ ሕዝቡን አላስተማሩም።

<u>የአሜሪካ መልዕክተኛ፤</u>

ኢብራሂም ሡልጣን! የእስላም ሊግ ዋና ፀሐፊ ከመሆንህ በፊት የአንድነት ማህበር አባል እንደነበርክ ሰምተናል።ለምን ሀሳብህን ለውጠህተቃዋሚው ሆንክ? .....

<u>ኢብራሂም ሡልጣን፤</u>

በእርግጥ ቀደም ሲል ለጥቂት ጊዜ ያገር ፍቅር ማህበር አባል ነበርኩ። አባል የሆንኩትም ለአገር ፍቅር ጉዳይ እንጂ፣ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ እንሁን በሚለው ሀሣብ ተስማምቼ አይደለም።በመጨረሻም ከማህበሩ የወጣሁት፣ የኢትዮጵያ መንግሥት እጅ ስለገባበትና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ብላታ ሎሬንሶ ታዕዛዝ ከአቶ ዘካርያስ ኃይሌ ጋር ሆነው፤ ከንጉሥ ኃይለሥላሴ ለማህበሩ መርጃ የተላከውን ሶስት ሺህ ፓውንድ ሲሰጡ አይቼ ነው።

<u>የመስኮብ መልዕክተኛ፤</u>

የአንድነት ፓርቲ ከኢትዮጵያ መንግሥት በሚሰጠው የፊናንስ እርዳታ የሚመራ ለመሆኑ፤ ማስረጃ ሊቀርብበት ይችላል ወይ ? .....

<u>ኢብራሂም ሡልጣን፤</u>

የኢትዮጵያ መንግሥት ለአንድነት ማህበር ሥራ ማስኬጃ በየወሩ የሚልከውን ገንዘብ ለማወቅ የባርክሌይን ባንክ መጠየቅ ነው። .....

<u>የእንግሊዝ መልዕክተኛ፤</u>

የእስላም ሊግ ባወጣው ዶኩመንት ውስጥ፣ ክርስቲያን የሆነው የኤርትራ ሕዝብ የሊበራል ፕሮግሬሲስት አባል እንጂ የአንድነት ፓርቲ ደጋፊ አይደለም ይላል። በሌላ በኩል ክርስቲያን የሆኑት ኤርትራውያኖች ቁጥራቸው አምስት መቶ ሺህ ነው ተብሎ ይነገራል። የሊበራል ፓርቲ በሰጠው መግለጫ ደግሞ፤ የክርስቲያኖቹ አባሎች ቁጥር ሃምሣ ሺህ ብቻ ስለሆኑ፣ ሌሎቹ የማን ወገኖች ናቸው ?

<u>ኢብራሂም ሡልጣን፤</u>

በኤርትራ የክርስቲያኖቹ ቁጥር አምስት መቶ ሺህ አይደለም። እጅግ ቢበዙ ሶስት መቶ ሺህ ቢሆኑ ነው።

<u>የእንግሊዝ መልዕክተኛ፤</u>

ሶስት መቶ ሺህ ቢሆኑም፣ የሊበራል አባሎች ሃምሣ ሺህ ብቻ ከሆኑ ሌሎቹ የማን ደጋፊዎች ናቸው ?

<u>ኢብራሂም ሡልጣን፤</u>

እኛ ባቀረብነው ዶክመንት የተገለጸው፤ የሊበራል ፓርቲ በስጠን ኢንፎርሜሽን መሠረት ስለሆነ፤ ትክክለኛውን ቁጥር መናገር ያለባቸው ሊበራሎች ናቸው። በእኛ በኩል ማስገንዘብ የምንፈልገው፣ የፓርቲያችን አባሎች ከሰባት መቶ እስከ ዘጠኝ መቶ ሺህ መድረሳቸውን ነው።



ከመሀል ራስ ተሰማ ከግራ ልጃቸዉ ደጃች አብርሃ

ኤርትራ ወደ ኢትዮጵያ ከምትመለስ፣ በእንግሊዝ ወይም በጣልያን የሞግዚት አስተዳደር እንድትቆይ ብዙ የለፉት፣ ራስ ተሰማ አስበሮምና ልጃቸው ደጃዝማች አብርሃ ተሰማ።

እነዚህ ተቀዋሚ የነበሩት ራስ ተሰማና ቤተሰቦቻቸው፣ ጃንሆይ በጥቅምት 1952 ዓ.ም ኤርትራን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲጐበኙ፣ ከደቀመሐሪ ተነስተው ማዕረባ እስኪደርሱ፣ ቀጤማ ጐዝጕዘው ስጋጃ አንጥፈው ከፍ ያለ የክብር አቀባበል አድርገውላቸዋል።

(Photo AAU)

የፈረንሣይ መልዕክተኛ፣
አሁን በኢትዮጵያ መንግሥት ውስጥ የሚኒስትርነትና የከፍተኛ ሥልጣን ቦታ የያዙት ብዙዎቹ ኤርትራውያኖች ናቸው ብላችኋል። እነዚህ ታላላቅ ሰዎች የት አገር የተማሩ ናቸው?

ኢብራሂም ሡልጣን፣
አብዛኛዎቹ እዚሁ አገር ውስጥ የተማሩ ሲሆኑ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ ወደ ውጭ አገር ተልከው ዩኒቨርሲቲ የጨረሱ ናቸው።

የፈረንሣይ መልዕክተኛ፣
መጀመሪያ በሰጣችሁት መግለጫ በጣልያን አስተዳደር ዘመን ኤርትራውያኖች አልተማሩም እንዲያውም ይጨቆኑ ነበር ብላችኋል። እንደዚህ ከሆነ ለኢትዮጵያ ሚኒስትርነት የበቁት ሰዎች በአገር ውስጥ እስከ ምን ደረጃ ተማሩ ? በውጭ አገርም የት ዩኒቨርሲቲ ነበሩ ? የላካቸውስ ማነው ?

ኢብራሂም ሡልጣን፣
በጣልያን ጊዜ የኤርትራ ሕዝብ በትምህርት የተበደለ መሆኑ የታወቀ ነው። ብዙዎቹ ኤርትራውያኖች በአገር ውስጥ መማር የቻሉት በሰዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ነው። ወደ ውጭ አገርሄደው ከፍተኛ ትምህርት የተማሩትም በታላቋ ብሪታንያ እርዳታ ሱዳን ውስጥ ባሉት ታላላቅ ዩኒቨርሲቲዎች ነው።

ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ያስተማሯቸው የኤርትራ ልጆች እነ ሎሬንሶ ታዕዛዝ እነ አምባዬ ወልደማርያም፣ ...... የታወቀው የፈረንሣይ የሞንት ፐሊዬ (MONTPELIER) ዩኒቨርሲቲ ምሩቆች መሆናቸው ቀርቶ፣ ቀጣፊው ኢብራሂም ሡልጣን፣ የሱዳን አገር ተማሪዎች አድርጐ አቀረባቸው። የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መዋሀድ ለመቃወምና በእንግሊዞች ድጋፍ ለመኖር የእስላም ሊግ ዋና ጸሐፊ ምን ያህል እንደቀላመደ ለመረዳት ከዚህ በላይ የተገለጸው በቂ ይሆናል። ኢብራሂም ሡልጣን በኮሚሽኑ ለቀረቡለት ጥያቄዎች የሰጠው መልስ፣ ለኤርትራ የወደፊት ዕድል የሚናገረው ሁሉ ያልበሰለና መሠረት ያልጨበጠ መሆኑን በሚገባ አስመስክሯል። በኤርትራ ሕዝብ ስም ሆኖ ለመናገር፣ ከእስላም ሊግ በስተቀር ሌላ ድርጅት ወይም ፓርቲ የለም ካለ በኋላ፣ እሱ ራሱ የአንድነት ማህበር አባል ሆኖ ለብዙ ጊዜ የሠራው፣ ለአገር ፍቅር ዓላማ እንጂ፤ ግቡ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል መሆኑን አልስማሁም ነበር ብሎ ሲክድ፣ ኢብራሂም ሡልጣን አላፈረም። በኢትዮጵያና በክርስቲያኑ የኤርትራ ሕዝብ ላይ ያለውን ከፍተኛ ጥላቻ በማሳየት፣ የአንድነት ማህበሩ በኤርትራ ሕዝብ ዘንድ ያለውን ከፍተኛ ሥፍራ በማራከስ፣ የቀድሞ ጌቶቹ የነበሩትን ጣልያኖች በማውገዝ፤ ለአዲሶቹ ገዥዎቹ ለእንግሊዞች በመስገድ፤ ኢብራሂም ሡልጣን ከሚመኘው ግብ ለመድረስ የሚቻል መስሎታል። የሰጣቸው የተምታቱ መግለጫዎች ሁሉ፤ በኮሚሽኑ አባሎች ዘንድ በእንግሊዙ መልዕክተኛ ጭምር፣ ምን ያህል ትዝብት እንደፈጠረበት አልተረዳም። ለማናቸውም ጉዳይ፣ በዚህ ዓለም በሀሰት መቀባጠርና ማጭበርበር ብዙ ጊዜ ውጤት የሚሰጥ ስለመሰለው፣ በዚህ ሞያ የተካነው ሡልጣን አሊ፣ እስከ መጨረሻው እንደቀጠለበት ወደፊት እናያለን። በዚህ በሀዳር 18 ቀን 1947 ዓ.ም ከእኩለ ቀን በኋላ የታየው የእስላም ሊግ አቋም፣ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ውህደት

ተቃዋሚነቱና በእንግሊዝ ገዥነት ለመቆየት ፈቃደኛነቱ በኮሚሽኑ ተመዝግቦለታል::

በኤርትራ የእንግሊዝ ወታደራዊ አስተዳደር ባዘጋጀው ፕሮግራም መሠረት ሕዝቡን በመወከል፣ በስፋትም ሆነ በድርጅት የታወቁት እነዚህ ሶስት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢሆኑም፣ መርማሪው ኮሚሽን አሥመራ ሊደርስ አቅራቢያ የተፈጠሩት እንደ « ፕሮ ኢጣሊያ » የመሳሰሉት ጥቃቅን ማህበሮችም፣ በመጨረሻው ሀሳባቸውን እንዲገልጹ ተፈቅዶላቸዋል:: በአሥመራ ከተማ ከየፓርቲዎቹ ጋር የሚደረገው ንግግር ከተፈጸመ በኋላ፣ መርማሪው ኮሚሽን በአገሩ ውስጥ እየተዘዋወረ፣ ከልዩ ልዩ የወረዳና የቀበሌ ነዋሪ ሕዝብ ወኪሎች፣ ከገበሬዎችና ከጥቃቅን ኢንዱስትሪ ሠራተኞች ጋር በቀጥታ በመነጋገር፣ በጽሑፍም ሆነ በቃል የሚገለጸውን ሀሳብ ሰብስቧል::

ኮሚሽኑ የሕዝብ ተመራጮቹን በማነጋገር ብቻ ሳይወሰን፣ እነዚህ ሰዎች በትክክል ከሕዝቡ የተመረጡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደርግ ነበር:: በተለይ የፈረንሣይና የመስኮብ መልዕክተኞች በአዘጋጆቹ በእንግሊዞች ላይ አንድ ጉድለት ለማግኘት ብርቱ ጥረት አድርገዋል::

# ሐቁን የሸፈነ ምርምር

የአራቱ ኃያላን መርማሪ ኮሚሽን አባሎች በሚፈጽሙት ተግባር፣ እያንዳንዳቸው ለየመንግሥታቸው ጥቅም ቅድሚያ እንዲሰጡ ስለታዘዙ፣ የሕዝቡን ሁኔታና ፍላጐት የሚያዳምጡበት ትክክለኛ አቋም አልነበራቸውም::

ከህዳር 1947 ዓ.ም እስከ ሰኔ 1948 ዓ.ም ድረስ ለሰባት ወራት የኤርትራን የሱማሌንና የሊቢያን ሕዝቦች ፍላጐት በማጥናት ከከረሙ በኋላ፣ አራቱ ዳኞች አስተያየታቸውን ሲሰጡ፣ ሁለት ለሁለት የተከፋፈሉ ሆነው ቀረቡ:: በሀሳብ ከተለያዩባቸው ብዙ ጉዳዮች ይልቅ፣ የተስማሙባቸውን ሶስት ነጥቦች በመጀመሪያ መግለጹ የሚቀል ይሆናል::

1.አራቱም፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ኤርትራ፣ ሱማሌና ሊቢያ፣ አንዳቸውም ነፃነት ተቀብለው ራሳቸውን ለማስተዳደር አልደረሱም ብለው ተስማሙ::

2.አራቱም፣ የሞቃዲሾ ሱማሌን ጣልያን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድረው ከመስጠት በስተቀር፣ ሌላ መፍትሔ የለውም አሉ::

3.አራቱም፣ ከኤርትራ ከሱማሌና ከሊቢያ ሕዝቦች በጣም አብዛኛዎቹ፣ የጣልያንን አስተዳደር የማይቀበሉ መሆናቸውን አረጋግጠዋል::

ሆኖም፣ መስኮብና ፈረንሣይ የጣልያንን ጥያቄ ለመደገፍ ተመሣሣይ አቋም ወስደው፣ ኤርትራ፣ ሱማሌና ሊቢያ ለነፃነት ደረጃ እስከሚበቁ ድረስ፣ ጣልያን በሞግዚትነት እንዲያስተዳድራቸው ጠየቁ::

በመስኮብ በኩል ጣልያንን በመርዳት ለአጭርና ለሩቅ ጊዜ ስለሚገኘው ጥቅም በተደረገው ጥናት፣ በሚያዝያ 1948 ዓ.ም በመላ ጣልያን በሚካሄደው የፖለቲካ ምርጫ የግራ ክንፎች በተለይም ኮሙኒስቶቹ እንደሚያሸንፉ ተገምቷል:: ኮሙኒስቶቹና ሶሻሊስቶቹም አዲስ ባወጡት ፖሊሲያቸው፣ ለጣልያን የቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶቿ እንዲመለሱላት ጽኑ ፍላጐታቸው ስለሆነ፣ ሶቪየት ሕብረት በዚህ በኩል ከፍተኛ እርዳታውን በመስጠት የወደፊቱን ወዳጅነት በትልቁ ለመገንባት ይመቻል ብሎ አምኗል:: ሆኖም የምርጫው ውጤት እንደታሰበው አሸናፊዎቹ የግራዎቹ ካልሆኑ፣ የመስኮብ አቋም የፖለቲካውን አየር ተከትሎ እንደሚለወጥ ይጠበቅ ነበር:: እንደተጠረጠረውም የጣልያን የፖለቲካ ምርጫ በሰጠው ውጤት አሸናፊዎቹ የክርስቲያን ዴሞክራቶችና ሊበራሎች መሆናቸው ሲታወቅ፣ መስኮብ የአዲሲቷ ጣልያን ደጋፊነቱን ለመሰረዝ ጊዜ አልወሰደም:: በመስከረም 1948 ዓ.ም የአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ ፓሪስ ላይ ሲደረግ፣ ኤርትራ፣ ሱማሌና፣ ሊቢያ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ሞግዚትነት ሶቪየት ሕብረት አባል በሆነበት በአንድ ዋና ኮሚቴ ቢተዳደሩ ይሻላል የሚል ሀሣብ ይዞ ቀረበ::

የፈረንሣይ ሬፑብሊክ ከ 1945 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለጣልያን ኮሎኒዎቿ በሙሉ እንዲመለሱላት የሰጠችውን ሙሉ ድጋፍ እስከ መጨረሻው ለመቀጠል መወሰኗ የሚያጠራጥር አልሆነም:: የአራቱ ኃያላን መርማሪ ኮሚሽን ኤርትራ በሰነበተበት ጊዜ፣ የፈረንሣዩ ወኪል የጣልያንን ዕድል ለማቃናት ምን ማድረግ እንዳለበት ከውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በምሥጢር የተሰጠው መምሪያ የሚከተለው ነበር::

1. ከጣልያን ጋር መሆን እንፈልጋለን የሚለው ወገን በተለይም «ፕሮ ኢጣሊያ » የሚያቀርበው ሀሳብ፣ የአብዛኛውን ሕዝብ ስሜት የሚወክል መስሎ በኮሚሽኑ አባሎች ዘንድ እንዲገመት ብርቱ ጥረት ማድረግ፣

2. ከኢትዮጵያ ጋር እንቀላቀል የሚሉት የአንድነት ማህበር አባሎች በሚቀርቡበት ጊዜ፣ የሕዝብ ወኪልነታቸው እስከምን ድረስ እንደሆነ፣ በሕዝቡም ስም ለመናገር የሚያስችላቸው ማስረጃ ምን እንደሆነ፣ በመስቀለኛ ጥያቄ አወናብዶ «ፍቅረ ሀገር» በአዲስ አበባ መንግሥት ገንዘብ የቆመ መሆኑን ማጋለጥ፣ .... ይህም በሚደረግበት ጊዜ ፈረንሣይ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ መስላ በግልጽ እንዳትታይ ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ፣

3. ኢትዮጵያ የአሰብን የባሕር በር እንድታገኝ ፈረንሣይ ሙሉ ድጋፏን ለመስጠት መወሰኗን ደጋግሞ ማሳወቅ፣

4. እንግሊዞች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ጣልያንን ከቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶቿ፣ በተለይም ከኤርትራና ከሊቢያ ለመንቀል ስለወሰኑ፣ ይህ ምኞታቸው በሌሎቹ አባሎች ዘንድ ተቀባይነት እንዳይኖረው የፈረንሣይ ወኪል የተለየ ጥረት እንዲያደርግ፣

5. በአሁኑ ጊዜ ለኤርትራ ሕዝብ በጣልያን ሞግዚትነት ከመተዳደር በስተቀር ሌላ የተሻለ መፍትሔ የለም በማለት፣ የኮሚሽኑን አባሎች ለማሳመን ጥረት ማድረግ፣

እንግዲህ፣ ከዚህ በላይ የተገለጸው ከ-ኬ-ዶርሰይ (quai D'orsay) የተሰጠው መምሪያ እንደሚያስረዳው፣ የመርማሪው ኮሚሽን ቡድን የኤርትራን ጉዳይ

ከማጥናቱ በፊት የመጨረሻው ፍርድ ምን መሆን እንዳለበት በፈረንሣይ በኩል ስለተወሰነ፣ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው የምስኪኑ ሕዝብ አስተያየትና ፍላጐት አይደመጥም ማለት ነው:: *

እንግሊዝና አሜሪካ አዲሲቷ ሬፑብሊክ ለተባለችው ጣልያን፤ ከሞቃዲሾ ሱማሊ በስተቀር ኤርትራና ሊቢያ ሊመለሱላት አይገባም ብለው፣ ገና ከመጀመሪያው የሰጡትን ውሳኔ አጽንተው ይዘዋል:: የሁለቱ አገሮች የመርማሪ ኮሚሽን አባሎች ባቀረቡት ራፖር፣ ከሃምሣ በመቶ በላይ የሆነው የኤርትራ ሕዝብ፣ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀልን እንደሚፈልግ በራፖራቸው ሲገልጡ፣ እንደዚሁም አብዛኛው ሕዝብ የጣልያን አስተዳደር እንዲመለስበት አለመፈለጉን አልሸሸጉም::

<u>እንግሊዞች ባቀረቡት ሀሳብ የኤርትራን ግዛት በሙሉ በተባበሩት መንግሥታት እርዳታ ኢትዮጵያ ለአሥር ዓመታት እንድታስተዳድር ኃላፊነት እንዲሰጣትና ከአሥር ዓመት በኋላ እንደ ሕዝቡ ፍላጐት ታይቶ ቋሚ ውሳኔ ቢሰጥ ይሻላል አሉ</u>:: ይህ ሀሳብ ኢትዮጵያን የሚረዳ መስሎ ቢታይም፣ ከዚሁ ጀርባ የታዘለ አንድ ሌላ ተንኰል መታቀዱ ግልጽ ነበር:: ይኸውም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ለአሥር ዓመታት መላ ኤርትራን ለማስተዳደር ዕድል ሲሰጠው፣ ቤቨን ያቀደውን የታላቋ ሱማሌን ፕሮገራ ለማስፈጸም፤ ኢትዮጵያ ኦጋዴንን በቀላሉ ትለቃለች የሚል ነው::

አሜሪካኖችም በበኩላቸው ኢትዮጵያን ለመርዳት የሚፈልጉ ለመምሰል ሞክረዋል:: ይሁን እንጂ ብዙውን ጊዜ እንደታየው ለቀድሞዎቹ የጣልያን ኮሎኒዎች መፍትሔ ይሆናል ብለው የሚያቀርቡት ሀሳብ ሁሉ፤ የተዘበራረቀና ለአፈጻጸም አስቸጋሪ በመሆኑ፣ ከየትኛውም ወገን ተቀባይና ደጋፊ አላገኙም:: ለምሣሌ፣ እንግሊዞች መላ ኤርትራን ኢትዮጵያ በሞግዚትነት እንድታስተዳድር ያቀረቡትን ሀሳብ ችላ ብለው፣

1. ከኤርትራ ግዛት ውስጥ ሶስቱ ደጋዎቹ አውራጃዎች አካለ ጉዛይ፣ ስራዬና ሀማሴን ከአሰብ የባሕር በር ጋር አሁኑኑ ለኢትዮጵያ እንዲሰጡ፣

2. የምዕራባዊው ቆላ አውራጃዎች በሙሉ፣ እንዲሁም የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች ወደፊት ተጠንተው ቋሚ ውሳኔ እስኪሰጣቸው ድረስ፣ በታላቋ ብሪታንያ አስተዳደር እንዲቆዩ፣ ......የሚል መፍትሔ ለብቻቸው ይዘው ቀረቡ::

እዚህ ላይ የጣልያን ፕሮፓጋንዳ አሜሪካኖችን ምን ያህል እንደማረከ ይታያል:: « ..... አሥመራና ምፅዋ በአውሮፓ ደረጃ የቈሙ ዘመናዊ ከተሞች በመሆናቸውና ነዋሪዎቹም በሙሉ የጣልያን ተወላጆች ስለሆኑ፣ ኢትዮጵያ ለማስተዳደር አቅም ያንሳታል .... » እያለ፤ የሮማ መንግሥት የሚነዛውን ወሬ አሜሪካኖች ተቀብለው፣ ለነዚህ ሁለት ከተሞች መተዳደሪያ ልዩ ቻርት እንዲዘጋጅ ሲጥሩ ቆይተዋል::

* REF. DOCUMENT K-AFRIQUE LEVANT SOUS TITRE "ETHIOPIE" VOLUME 54

በመሠረቱ እንግሊዝና አሜሪካ በኤርትራ ጉዳይ ከጣልያን ይልቅ የኢትዮጵያን ጥያቄ ለመደገፍ በተቀራረበ ሀሣብ ላይ ስለሚገኙ፣ እርስ በርሳቸው ተነጋግረው አቋማቸውን በአንድነት ለማስተባበር አይቸገሩም ነበር።

ከአሜሪካኖችና ከእንግሊዞች ይልቅ በጣም የሚያሳዝን ትዝብት ላይ የወደቀት መስኮብና ፈረንሣይ ናቸው። ከኤርትራ ከሱማሌና ከሊቢያ ሕዝቦች በጣም አብዛኛዎቹ፣ የዚህን ግፈኛ የሆነ የጣልያን አስተዳደር እንዳታመጡብን ሲሉ ያቀረቡትን አቤቱታ አናዳምጥም ብለው፣ የየራሳቸውን ፖለቲካና የኤኮኖሚ ጥቅም ሲያባርሩ፣ ትክክለኛ ፍርድ እንዳይሰጥ ዋናዎቹ እንቅፋቶች ሆኑ። በዶክመንት ላይ ሰፍሮ እንደታየው የመርማሪው ኮሚሽን አባሎች ለዳኝነት ሥራ የተላኩበት ተግባር፤ በየአገሩ ያለው አብዛኛው ሕዝብ ለወደፊት ዕድሉ ምን እንደሚፈልግ ጠይቀው ለመረዳት ነበር እንጂ፣ እነሱ በሕዝቡ ስም ሆነው ለእነሱ የሚጠቅማቸውን ለመወሰን አልነበረም።

በልማዱ እንደሚታወቀው ፖለቲካና ዳኝነት አብረው ሊጓዙ አይችሉም። በዳኝነት አሠራር ሁለትና ሁለት ሲደመር አራት ብቻ ነው መሆን የሚችለው ብሎ ሲቆም፣ በፖለቲካ ውሳኔ ሁለትና ሁለት፣ ሶስት ተኩል የመሆን ዕድል አለው። የአራቱ ኃያላን መንግሥታቶችም እስከ 1945 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ፤ በዓለም ላይ አንድነታቸውን አጽንተው በያዙት ወሰን የሌለው ሥልጣን፣ ለቀድሞዎቹ ለጣልያን ቅኝ ግዛቶች፣ የፈለጉትን የፖለቲካ ውሳኔ በማድረግ ፋንታ፣ አደባባይ ለበስ የሆነ የዴሞክራሲ ፍርድ በመስጠት እንደነቃለን ብለው ሲጓተቱ፤ ያሰቡት ሁሉ አልተሳካላቸውም። በመካከላቸው የተፈጠረው አለመግባባት፣ የኤርትራ፣ የሱማሌና የሊቢያ ሕዝቦች ፍላጐታቸው ምን እንደሆነ ለመርማሪው ኮሚሽን በገለጹት ሀሳብ ላይ ሳይሆን፤ የሕዝቡን ጥያቄ ወደ ጐን ትተው ለየራሳቸው የሚጠቅም ፍርድ ለመስጠት ሲጥሩ ነው። እጅግ አስገራሚ የሆነውም፣ በመስከረም 1948 ዓ.ም የአራቱ ታላላቆች የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ፓሪስ ላይ ሲሰበሰቡ፣ ቀደም ሲል በመርማሪው ኮሚሽን አባሎች መካከል ከደረሰው የሀሳብ መለያየት የበለጠ የማይግባቡ ሆነው መገኘታቸው ነው። በተመሳሳይ ሀሳብ አንድነታቸውን አፋፍመው የነበሩት ፈረንሣይና መስኮብ፣ በፓሪሱ ስብሰባ ላይ ተለያይተው ብቅ አሉ። ምን ጉድ ፈላ ? ..... ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ በሚያዝያ 1948 ዓ.ም በጣልያን አገር በተደረገው ጠቅላላ የፖለቲካ ምርጫ አሸናፊዎቹ ክርስቲያን ዴሞክራቶችና ሊበራሎች በመሆናቸው፤ ፈረንሣይ፣ እንግሊዝና አሜሪካ ሲደሰቱ፣ በኮሙኒስቶቹ መሸነፍ መስኮብ ትልቅ ሀዘን ላይ ወደቀ። ስለዚህ፣ ፈረንሣይ ለጣልያን ጥያቄ የሰጠችውን ድጋፍ ስታጸና፣ ሶቪየት ሕብረት ሀሳቡን ለውጦ ለራሱ ጥቅም የሚሻለውን መንገድ ፈላጊ በመሆኑ፤ የሁለቱ አገሮች የሀሳብ አንድነት የማይቀጥል ሆነ። አሜሪካና እንግሊዝም፣ ጣልያን ወደ ኤርትራና ወደ ሊቢያ መመለስ የለባትም ብለው የወሰኑትን አንለውጥም አሉ። በመጨረሻው እነዚህ አራቱ የዓለም ኃያላኖች፣ የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛቶች የወደፊት ዕድል ለመወሰን ያቃታቸው መሆኑን በትክክል ሲገነዘቡ፣ በ 1946 ዓ.ም በፓሪሱ የሠላም ጉባኤ ውሳኔ መሠረት፤ ጉዳዩን ለተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ለማቅረብ ተስማምተው መለያየት ግዴታ ሆነባቸው።

# ክፍል ሶስት

## የኤርትራ ጉዳይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሶስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ (ሚያዝያ - ግንቦት 1949)

ገጽ

1. ከኃላፊነት መሸሽ ........ 96
2. ሱማሌ ለጣልያን ትሰጥ፣ ኤርትራ በሁለት ትከፈል፣ (አሜሪካና እንግሊዝ) ....97
3. የመስኮብ ውርጅብኝ ........ 106
4. ስፎርሳ እና አክሊሉ ........ 110
5. የአምሣለ ገነት ጉባኤና ውሳኔ ........ 120
6. በኒውዮርክ ያልተጠበቀ ደስታ ........ 126
7. አቶ አክሊሉ፣ የትኛውን ይከተሉ ? ........ 129
8. ኢትዮጵያና ጣልያን ........ 132
9. የላቲን አሜሪካ አገሮች፣ የጣልያን ጠበቆች ........ 138
10. ኢትዮጵያና አራቱ ኃያላኖች ........ 142
11. የቤቨንና ስፎርሳ ስምምነት ........ 150
12. የቤቨን ስፎርሳ ስምምነት፣ በንዑስ ኮሚቴ "15" ........ 158
13. የዋናው ኮሚሲዮን ውጤት ........ 163
14. ጠቅላላው ጉባኤ፣ ከውሳኔው በፊት ........ 168
15. የማክሰኞ ግንቦት "17" ድራማ ........ 172
16. ዕድሜ ለሀይቲ መልዕክተኛ ........ 174
17. ጥሩው ዕድል አመለጠ ........ 178
18. የጃንሆይ አመለካከት ........ 181
19. የጓደኞች ትችት ........ 188

# ከኃላፊነት መሸሽ

መስከረም 15 ቀን 1948 ዓ.ም የአራቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች በአንድነት ፈርመው ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ጸሐፊ በላኩት ደብዳቤ፣ « .... ከጣልያን ጋር በተደረገው የዕርቅ ስምምነት በአንቀጽ 23 ቁጥር 3 አባሪ 11 ላይ የተገለጸውን መሠረት በማድረግ፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ አገሮች ጉዳይ መስከረም 21 ቀን 1948 ዓ.ም በሚከፈተው የድርጅቱ የሶስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ቀርቦ እንዲታይና እንዲወሰን ስንጠይቅ ክብር ይሰማናል .... » አሉ:: ክብሩ የት ላይ እንደሆነ ለማወቅ አብዛኛዎቹ አባል መንግሥታቶች እርስ በርሳቸው ሳይጠያየቁ አልቀሩም::

የኤርትራን፣ የሊቢያንና የሱማሌን ሕዝቦች የወደፊት ዕድል፣ የግል ጥቅም በማይመለከተው በትክክለኛ ሚዛን ላይ ተመሥርተው ውሳኔ መስጠት አቅቷቸው፣ ኃላፊነታቸውን ለተባበሩት መንግሥታት ሲወረውሩ፣ የሚያሳፍራቸው እንጂ የሚያስከብራቸው አልነበረም::

ለዓለም ሕዝብ እልቂት በጥጋብ የተነሱትን ናዚስቶችንና ፋሽስቶችን ተባብረን ወግተን የጋራ ድልን እንደአገኘነው ሁሉ፤ ለወደፊቱም በዚች ምድር ላይ የሠላም ሕይወትና ፀጥታ፣ ዋስትና እንዲኖረው ኃላፊነታችንን እንፈጽማለን ብለው፣ እነዚህ ኃያላን የተባሉ መንግሥታቶች የሰጡት ቃል፣ በድሆች አገሮች ላይ ያሳደረው ተስፋ ወሰን አልነበረውም::

በሩዝቬልት፣ በቸርችልና በስታሊን መካከል የተደረጉት የያልታ ስምምነቶች፣ የጋራ ጠላቶቻቸውን ናዚስቶችንና ፋሽስቶችን ድል ከመቱ በኋላ፣ ዓለምን ተከፋፍለው ለመምራት ስለሆነ፣ በየክልላቸው በሊበራሊዝምና በኮሙኒዝም አይዲዎሎጂ ኃይላቸውን ለማጠንከርና የሚመኙትን ለመፈጸም እሽቅድድም ቀጠሉ:: ሁሉም ለየጥቅማቸው የተሰለፉ በመሆናቸው፣ እንኳንስ በከፍተኛዎቹ የዓለም ፕሮብሌሞች ይቅርና፣ በአነስተኛዎቹም ጉዳዮች ላይ ተስማምተው መፍትሔ ለመስጠት የማይችሉ ሆኑ::

በ 1936 ዓ.ም የኢትዮጵያ ጉዳይ የዤኔቩን የመንግሥታት ማህበር ዓላማውን እንደአናጋው ሁሉ፣ የአራቱ ኃያላኖችም የአንድነት መንፈስና ትብብር ቋሚ መሠረት የሌለው መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ያጋለጣቸው የኤርትራ፣ የሊቢያና የሱማሌ ጉዳይ ነው:: ለሶስት ዓመታት በግራና በቀኝ እያምታቱ ይዘዋቸው የቆዩትን የኤርትራ፣ የሊቢያና የሱማሌ ዶሴዎች፤ አንድ ዓይነት መፍትሔ ሊያስገኙላቸው ስላልቻሉ፣ አራቱ ኃያላን መንግሥታቶች እፍረትና ውርደት ሳይሰማቸው፣ ኃላፊነቱን ለተባበሩት መንግሥታት ማስተላለፍ ግዴታ ሆነባቸው:: አራቱ ኃያላን የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ዶሴ ለተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ እንዲቀርብ ሲያደርጉ፣ በተለይ አሜሪካና እንግሊዝ ከአባል አገሮች መካከል በሚኖሯቸው ተከታዮችና ደጋፊዎች እነሱ በሚፈልጉት ዓይነት ጉዳዩ መፍትሔ ያገኛል ብለው ከፍ ያለ ተስፋ ሳያደርጉ አልቀሩም::

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እነዚህን ለሶስት ዓመታት ሲንገላቱ የኖሩ ፋይሎች ከተረከበ በኋላ፣ በነማን ነገረ ፈጅነት፤ በነማን ዳኝነት፤ ሙግቱ ሲጧጧፍ እንደቆየና የመጨረሻው ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ትርምሱ እንዴት እንደነበረ፣ በዝርዝር እንመለከታለን:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት

የሶስተኛውን ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ በሁለት ደረጃ ከፍሎ ያከናወነው፣ የመጀመሪያውን በመስከረም 1948 ዓ.ም ፓሪስ ላይ ሲሆን፤ ሁለተኛውን በሚያዝያ 1949 ዓ.ም በኒውዮርክ ነበር።

መስከረም 24 ቀን 1948 ዓ.ም ፓሪስ ላይ የተከፈተው የመጀመሪያው ክፍል የሶስተኛው ጠቅላላ ጉባኤ ሥራውን ሲጀምር፣ በአራቱ ኃያላን የውጭ ጉዳይ መማክርት ቢሮ የተዘጋጁት የኤርትራ፣ የሊቢያና የሱማሌ ዶሴዎች፣ ብዙ ዶክመንቶች ታጭቀውባቸው፣ ከምራቸው ለዓይን ስለሚያስደነግጥ፣ በዋናው ኮሚሲዮን ላይ የተሰበሰቡት የአባል መንግሥታት ወኪሎች፣ እነዚህን ጉዳዮች በአጭር ጊዜ ውስጥ መርምሮ ሀሳብ ለማቅረብ እጅግ ከባድ ሆነው ታይዋቸው። ጉዳዩን ረጋ ብሎ ለማጥናትና የበሰለ ሀሳብ ለማቅረብ ጊዜ ስለሚጠይቅ፣ በሚያዝያ 1949 ዓ.ም በኒውዮርክ ሌክ ሴክ ሰክሴስ ላይ ለሚከፈተው ለሁለተኛው ክፍል ጠቅላላ ስብሰባ እንዲተላለፍ፣ አባል አገሮች ተስማምተው ተለያዩ።

በዚህ ሀሳብ መሠረት የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛት ሕዝቦች የወደፊት ዕድል ለመወሰን፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ረቡዕ ሚያዝያ 6 ቀን 1949 ዓ.ም ኒውዮርክ በተከፈተው በሁለተኛው ክፍል ስብሰባው ላይ ጥናቱን ጀመረ።

## ሱማሌ ለጣልያን ትሰጥ፤ ኤርትራ በሁለት ትከፈል፤
### (የአሜሪካና የእንግሊዝ አቋም)

« .... ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች የተባበሩት መንግሥታት የሚሰጠው ውሳኔ የሶስት ሚሊዮን ሕዝቦችን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የድርጅቱንም የወደፊት ዕድል የሚመለከት ይሆናል ..... » ይህንን የማስጠንቀቂያ መንፈስ ያዘለ ቃል የወረወረው፣ የአሜሪካ መልዕክተኞች መሪ ጆን ፎስተር ደለስ (JOHN F. DULLES) ነው።

ረቡዕ ሚያዝያ 6 ቀን 1949 ዓ.ም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ኮሚሲዮን የኤርትራን፣ የሊቢያንና የሱማሌን ጉዳይ መመልከት ሲጀምር፣ ከአባል አገሮች መካከል የመጀመሪያው በር ከፋች ተናጋሪ፣ የአሜሪካ መልዕክተኞች መሪ ነበር። ሚስተር ደለስ (DULLES) በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዘንድ የአሜሪካ ነዋሪ አምባሳደር ሆኖ ከሠራ በኋላ፣ ከ 1952 ዓ.ም ጀምሮ በሕመም ሕይወቱ እስከ አለፈበት እስከ 1959 ዓ.ም ድረስ፤ የዩናይትድ ስቴትስ ፕሬዚዳንት የጀኔራል አይዘንሐወር የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ በዓለም ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ቦታ ይዞ እንደተጫወተ ታሪክ ያስታውሰዋል።

« የአራቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ባለሥልጣኖች በሶስት ዓመት ጊዜ ውስጥ፣ ውሳኔ ለመስጠት ያልተስማሙበትን ከፍተኛ ጉዳይ፣ ለተባበሩት መንግሥታት ሲያቀርቡ ይህንን የሚያህል ከባድ ኃላፊነትና ሥልጣን ድርጅቱ የሚቀበለው በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። » ካለ በኋላ፣ ጆን ፎስተር ደለስ ንግግሩን በመቀጠል « ..... ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች የተባበሩት መንግሥታት የሚሰጠው ውሳኔ የሶስት ሚሊዮን ሕዝቦችን ጉዳይ ብቻ ሳይሆን፣ የድርጅቱንም የወደፊት ዕድል የሚመለከት ይሆናል ..... » ሲል አስጠነቀቀ።

እነዚህን የቀድሞ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች፣ ካለፉት ስምንት ዓመታት ጀምሮ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ሲያስተዳድር ካገኘው ኤክስፔሪያንስ የሚሰጠውን ሀሳብ፣ በጥሞና ማዳመጥ አስፈላጊ መሆኑን ካሳሰበ በኋላ፤ የአሜሪካ መልዕክተኞች መሪ ለእያንዳንዱ አገር የሚጠቅም መስሎ የሚታየውን መፍትሔ ያቀረበው በሚከተለው አኳኋን ነበር::

1. ሊቢያ፤ የአገሩ አንድነት ተመሥርቶ ነፃነት እስከሚሰጥበት ጊዜ ድረስ የሲሬናይክ አውራጃ (CYRENAIQUE) በታላቋ ብሪታንያ መንግሥት አስተዳደር ሥር እንዲቆይ አስፈላጊነቱን የአሜሪካ መንግሥት ያምናል፤ ካለ በኋላ ለትሪፖሊታንያ እና ለፌዛን አውራጃዎች ምን መፍትሔ እንደሚገኝላቸው ጆን ፎስተር ደለስ አልተናገረም::

2. ኤርትራ፤ ይህ አገር እንዳለፉት ዘመናት ኢትዮጵያን ለማጥቃት ለሚፈልጉ ጠላቶች፣ የጦር ማከማቻና ማሸጋገሪያ መሆኑ እንዲቀር፤ የምሥራቁ አውራጃዎች በሙሉ፣ በቀጥታ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀሉ የአሜሪካ መንግሥት ይደግፋል:: ሌላው ከከረን በኋላ ያለውን የምዕራቡን አውራጃ፣ በሀይማኖቱና በባሕሉ ከሚመሳሰለው ከሱዳን ጋር ለመቀላቀል እንዲችል ተጠንቶ ቢወሰን ይበጃል::

3. ሶማሊ፤ ነፃነት ለመቀበልም ሆነ በኦቶኖሚ ለመተዳደር አገሩ ብቁ ካለመሆኑም በላይ፣ ለአካባቢው ሠላምና ፀጥታ አስጊ መስሎ ስለማይታይ፣ በተባበሩት መንግሥታት ስም አዲሲቷ የጣልያን ሬፑብሊክ በሞግዚትነት ለማስተዳደር እንዲሰጣት የሚደገፍ ነው::

በጠቅላላው፤ የአሜሪካ መልዕክተኞች መሪ ከሞላ ጐደል የጠቃቀሳቸው እነዚህ መፍትሔዎች፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ለተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን ለማቅረብ ባዘጋጃቸው ረቂቅ ውሳኔዎች ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን፣ የእንግሊዝ ዋና መልዕክተኛ ከሰጠው መግለጫ መረዳት ይቻላል::

ጆን ፎስተር ደለስ ያደረገው ዲስኩር ከእንግሊዝ በስተቀር፣ በሌሎቹ በተባበሩት መንግሥታት አባል አገሮች ላይ የሚማርክ ስሜት አልፈጠረም:: ለችግሮቹ መፍትሔ ያቀረበው ሀሳብ የተሟላና፣ በተረጋገጠ አቋም ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ፣ ሚስተር ደለስ የሰነዘራቸው አስተያየቶች ጉባኤው እንዲመክርበት እንደ ረቂቅ ውሳኔ ሆኖ አልተቆጠረም:: የሆነ ሆኖ የአሜሪካ መልዕክተኞች መሪ የገለጸው ሀሳብ፣ ምንጩ የፈለቀው ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥት መሆኑን አባል አገሮች ተረድተውታል::

ኮሚሲዮኑ ሥራውን ሲጀምር፣ ከአራቱ ኃያላን መንግሥታቶች የሚቀርቡትን መግለጫዎች ለማዳመጥ ቅድሚያ የሰጠ ስለሆነ፣ ከአሜሪካ መልዕክተኞች መሪ ቀጥሎ ፕሮግራም የተያዘለት ሁለተኛው ተናጋሪ፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴታ ሄክቶር ሜክኒል (HECTOR McNEIL) ሆነ::

የግርማዊ የእንግሊዝ ንጉሥ መንግሥት መልዕክተኛ የንግግሩ መክፈቻ ያደረገው፣ ወዳጁ የአሜሪካ ተወካይ የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛቶች የነበሩትን አገሮች፣ ታላቋ ብሪታንያ በማስተዳደር ለምትፈጽመው መልካም ተግባር በማድነቁ፣ የምሥጋና መልስ በማበርከት ነበር:: የአሜሪካ መልዕክተኞች መሪ ጆን

ፎስተር ደለስ ለጉባኤው ያቀረበው ሀሳብ፤ የታላቋ ብሪታንያን መሠረታዊ ዓላማ የተመረኮዘ ስለሆነ፣ የእንግሊዙ መልዕክተኛ ሰፋ ያለ ማብራሪያ ከመስጠቱ በስተቀር አዲስ ነገር አልጨመረም:: ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች አስተዳደር መፍትሔ ለመስጠት የእንግሊዝ መንግሥት ሀሳቡን ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በይፋ የሚያቀርበው ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሆነ፤ የጉባኤው ተካፋዮችና በተለይም የኢትዮጵያ መልዕክተኞች የሚያዳምጡት በጥንቃቄ ነበር::

1. ሊቢያ፤ « ...... ሶስቱ ዋና ዋና አውራጃዎች፤ ትሪፖሊታንያ፣ ሲረናይክና ፌዘን በአንድነት እንዲዋሀዱ የሚቀርበው ሀሳብ ተገቢ ነው ብላ ታላቋ ብሪታንያ ታምናለች:: እስከዛሬ ድረስ የፌዘን አውራጃ በፈረንሣይ እጅ ከመሆኑ በስተቀር ትሪፖሊታንያን እና ሲረናይክን እንግሊዝ ስታስተዳድር ስድስት ዓመት ሆኗል::

..... የአሜሪካ መልዕክተኛ፤ ባቀረበው ሀሳብ እንዳመለከተው፣ ሲረናይክ በእንግሊዝ አስተዳደር እንድትቆይ የተባበሩት መንግሥታት ከወሰነ፤ መንግሥቴ ሊቀበል ይችላል:: ትሪፖሊታንያ ግን፣ ሕዝቡም ከሲረናይክ የተለየ ስለሆነና በዚህ አውራጃ ታላቋ ብሪታንያም ለመቆየት ስለማትፈልግ፣ ሌላ መፍትሔ በአስቸኳይ እንዲሰጥ ያስፈልጋል:: የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ግን የትሪፖሊታንያንም አስተዳደር እንግሊዝ እንድትቀጥል ያስፈልጋል ብሎ ከጠየቀ፣ የምንቀበለው ለጥቂት ዓመታት ብቻ ይሆናል:: በነዚህ ጉዳዮች ላይ በትክክል መረዳት የሚያስፈልገው፤ የሲረናይክ ሕዝብ የጣልያን አስተዳደር ተመልሶ እንዳይመጣበት በጥብቅ ተቃውሞውን ያሰማ መሆኑን ነው:: ለሲሪናይክ፤ ከሕዝቡ ፍላጐት ውጭ ተወስኖ አስተዳደሩ ለጣልያን ይሰጥ ቢባል፣ ሕዝቡ ጦርነት ሊያነሣ ይችላል:: ስለዚህ ሲረናይክ ለጣልያን እንዳይሰጥ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት በጥብቅ ያሳስባል::

2. ኤርትራ፤ ...... በመላው እስላም የሆነው የኤርትራ የምዕራብዊው ቆላ ሕዝብ፣ ግልጽ በሆነ መንገድ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀልን እንደማይፈልግ አመልክቷል:: ይህ ሕዝብ በባሕሉም፣በሀይማኖቱም፣ በዘሩም ከሚቀራረበው ከሱዳን ጋር ቢቀላቀል፣ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ተገቢ የሆነ መፍትሔ ነው ብሎ ይገምታል::

...... በሕዝብ ቁጥር ብልጫ ያለው የምሥራቁ አውራጃና የደጋው ነዋሪ የሆነው ክፍል ግን፣ በዘርና በሀይማኖቱ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ተመሳሳይ ስለሆነ፣ ከኢትዮጵያ ጋር መዋሀድን እንደሚደግፍ ታውቋል:: ስለዚህ ከምዕራብዊው ቆላ አውራጃ በስተቀር የምሥራቁ የኤርትራ ግዛት ተከፍሎ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ይደግፋል:: .... ለሕዝቡ ጥቅምና ለአካባቢው ሠላም በማሰብ ኢትዮጵያም ለደረሰባት ጥቃት መደጐሚያ እንዲሆናት፣ ይህ መፍትሔ ቢወሰን የተሻለ ይሆናል::

3. ሱማሌ፤ ..... ይህን አገር የጣልያን መንግሥት ለማስተዳደር እንዲሰጠው የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ይደግፋል:: ...የፈረንሣይ መንግሥት ከዚህ ቀደም እንደገለጸውና የአራቱም ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን እንዳረጋገጠው፣ የሱማሌ ሕዝብ ነፃነትን ለመቀበል አልተዘጋጀም:: አገሩንም በሞግዚትነት ለማስተዳደር ከጣልያን በስተቀር ሌላ ችሎታና

ኢክስፔሪያንስ ያለው አገር የለም ..... » ሲል፣ ሚስተር ሜክኒል (Mc NEIL) አዲሲቷ ለተባለችው ጣልያን የድጋፍ አስተያየቱን ሰጠ::

የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኛ ንግግር ሲፈጸም፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ከአሜሪካና ከእንግሊዝ በቀረቡት ሀሳቦች ላይ የመንግሥታቸውን አቋም ለማስረዳት የጉባኤውን ሊቀመንበር ጠየቁ:: ለኢትዮጵያ እጅግ አሳሳቢ በሆነው በኤርትራ ጉዳይ ከታላቋ ብሪታንያ መንግሥትና ቀደም ሲልም ከዩናይትድ ስቴትስ የቀረበው ሀሳብ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መንግሥት የሚያረካ እንጂ ቅር የሚያሰኝ ይሆናል ተብሎ አልተገመተም ነበር::

ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ መፍትሔ እንዲሆን ከሞላ ጎደል አሜሪካና እንግሊዝ ባቀረቡት ሀሳብ ላይ፣ ኢትዮጵያ የምትቃወመው ምን እንደሆነ አቶ አክሊሉ በንግግራቸው መግቢያ ላይ አልገለጹም:: በመጀመሪያ፣ በጥንታዊው ዘመን የኢትዮጵያንና የኤርትራን፣ እንደዚሁም የሱማሌን ሕዝቦች የአንድነት ታሪክ በማብራራት፣ ቀጥሎም እነዚህ በአንድ አገር አስተዳደር ተጠቃልለው ይኖሩ የነበሩትን ሕዝቦች ለሃምሣ ዓመታት የለያያቸው ኮሎኒያሊስት ጣልያን መሆኑን፣ በመጨረሻም ኤርትራና ሱማሌ ወደ ጥንት አገራቸው እንዲመለሱ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት የጠየቀው፣ እንደ ጣልያን ግዛት ለማስፋፋት ሳይሆን፣ በሕዝቦች ታሪክ፣ በዘርና በባሕል አንድነት ላይ የተመሠረተ ትክክለኛ ጥያቄ ነው፣ በማለት ካስረዱ በኋላ፣ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልዕክተኛ ከአሜሪካና ከታላቋ ብሪታንያ በቀረበው ሀሳብ ላይ የንጉሠ ነገሥቱን መንግሥት ቅሬታና ተቃውሞ የገለጡት በሚቀጥለው አኳኋን ነበር::

1. « ...... በምንም መንገድ ጣልያን ተመልሳ ሱማሌን እንድትይዝ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አይቀበልም:: ዝም ብሎም አይመለከትም:: ...... ሱማሌን ለማስተዳደር ኃላፊነቱን መቀበል የሚገባት፣ ኢትዮጵያ መሆኗን መንግሥቱ በትክክል ያምናል::

2. ....... ስምንት ዓመት ሙሉ ፍርድ ለማግኘት በሚያሳዝን ሁኔታ ሲንገላታ የኖረው የኤርትራ ሕዝብ ጽኑ ፍላጐት፣ ከእናቱ ከኢትዮጵያ ጋር ለመቀላቀል እንጂ፣ ገሚሱ ተከፍሎ ለባዕድ አገር እንደ ዕቃ እንዲሰጥ አይደለም:: የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ደህና አድርጐ እንደተረዳው፣ የኤርትራ ሕዝብ ክርስቲያኑም ሆነ እስላሙ አንድነቱ እንዲነካበት አይፈልግም:: በዲሞክራሲ ሥርዓት ከሃምሣ በመቶ በላይ የሆነው የኤርትራ ሕዝብ፣ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀልን የጠየቀ መሆኑ መዘንጋት የለበትም::

3. ...... ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ጀምሮ፣ የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች የነበሩትን አገሮች ጉዳይ፣ የአራቱ ኃያላን መንግሥታት ተስማምተው መፍትሔ መስጠት ስለአቃታቸው፣ ዛሬ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚጠበቀው ውሳኔ ለመካከለኛው ምሥራቅና ለአፍሪካ ሕዝቦች ምን ያህል ከፍተኛ ጉዳይ እንደ ሆነ መታወቅ አለበት::

4. ......የተባበሩት መንግሥታት አባሎች እንዲገነዘቡት የሚያስፈልገው፣ የጣልያን መንግሥት ኤርትራና ሱማሌ ካልተመለሱልኝ ብሎ

የሚወተውተው፣ ለአገሩ ሕዝብ አስቦ ሳይሆን፣ ለዘለዓለም በማይሞተው ምኞቱ እነዚህን ሁለት አገሮች የጦር ማከማቻ በማድረግ፣ ለአራተኛ ጊዜ ኢትዮጵያን ለመውጋት መሆኑን ነው።

5. ..... በመጨረሻም የተባበሩት መንግሥታትን የምጠይቀው፣የታላላቅ አገሮችን ጥቅም ብቻ ሳይሆን፣ የታናናሽ አገሮችንም መብት በእኩል ደረጃ ለመጠበቅ ድርጅቱ የተጣለበትን ኃላፊነት በትክክል እንዲፈጽም ነው።

6. ......ሱማሌን መልሶ ለጣልያን ለመስጠት በያለበት የሚጠነሰሰውን ተንኮል ኢትዮጵያ አትቀበልም። ..... ኢትዮጵያ፣ የኤርትራ ሕዝብ ሳይከፋፈል ወደ ጥንት አገሩ እንዲመለስ ተገቢ ነው ብላ ትክክለኛ ፍርድ መጠየቋን አታቋርጥም ...... »

ብለው አክሊሉ ሀብተወልድ ንግግራቸውን ደመደሙ።

የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኛ ይህን የመሠለ አስተያየት ከኢትዮጵያ ልዑክ ይሰነዘራል ብሎ አይጠብቅም ነበር። « ..... በኤርትራ ግዛት ውስጥ ኢትዮጵያን ከማይፈልጉት እስላሞች ከሚኖሩበት ከምዕራብዊው አውራጃ በስተቀር፣ ሌላው በሙሉ የምፅዋና የአሰብ የባሕር በር ጭምር፣ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀዱ የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የሰጠውን ከፍተኛ ድጋፍና ያደረገውን ጥረት፣ አክሊሉ ሀብተወልድ ከቁም ነገር አለመቁጠሩ ያስገርማል። የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት የኢትዮጵያ ወዳጅ ባይሆን ኖሮ፣ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ጉባኤ ላይ፣ መስኮብና ፈረንሣይ ኤርትራ ለጣልያን ተመልሳ እንድትሰጥ የደከሙበትን ጉዳይ አያፈርስም ነበር። ኢትዮጵያ በፋሽስት የደረሰባትን ጥቃት በመመዘን፣ በአንድ ነገር ልትካስ ይገባል በሚል ቅን አስተያየት፣ ከታላቋ ብሪታንያ ለቀረበው የድጋፍ ሀሳብ፣ በተባበሩት መንግሥታት ሸንጎ ላይ ምሥጋና መደርደር ባያስፈልግ እንኳን፣ እስከዚህ ድረስ ግምት ሳይሰጠው የሚታለፍ መሆን አልነበረበትም።

..... ታላቋ ብሪታንያ ከፋሽስት ጣልያን ጋር ተዋግታ፣ የኢትዮጵያን ነፃነት አስመልሳ፣ ከስምንት ዓመታት ጀምሮ ኤርትራንና ሱማሌን የምታስተዳድረው ሕዝቡ እየተሰቃየ አይደለም። ይህ የተሰጠው አስተያየት ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከተው የኤርትራና የሱማሌ ሕዝብ ስሜት አለመሆኑ የታወቀ ነው። የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ፣ ከታላቋ ብሪታንያ ጋር በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ የሀሳብ ግጭት እንዲኖር መፈለጉን አሳይቶናል። በዚህ አነጋገሩ ለማስማት የሞከረው፣ ኢትዮጵያ ነፃነቷ የተሟላና ለታላቋ ብሪታንያ የተለየ ግምት የሌላት መሆኑ እንዲታወቅ ነው። እንግዲህ ለወደፊቱ የሚጠቅመውን እሱ ያውቃል። እኛም በያዝነው መንገድ እንቀጥላለን ....... » በማለት፣ የእንግሊዝ መልዕክተኞች መሪ በአቶ አክሊሉ ላይ አንድ ዓይነት ቅሬታ አሳደረ።

አቶ አክሊሉ፣ ለቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ባስተላለፉት ረዥም የቴሌግራም መልዕክት ላይ፣ ከእንግሊዝ መንግሥት በተሰጠው መግለጫ በበኩላቸው ምን ያህል ቅር እንደተሰኙ በሰፊው አስረድተዋል። በተለይ በጣም ያሳዘናቸው፣ ጠላታችን የሆነው ጣልያን እንደገና ተመልሶ ሱማሌን እንዲገዛ በይፋ መደገፉ ነው። ሱማሌን ለማስተዳደር ከጣልያን የተሻለ መንግሥት ስለሌለ፣ አዲሱ የጣልያን ሬፑብሊክ ኮሎኒ አስተዳደር ያለውን ኤክስፔሪያንስ በዚህ አገር ላይ ለማሳየት ይችላል፣ ሲል የእንግሊዝ መንግሥት የሰጠው መግለጫ በኢትዮጵያ በኩል የሚጠበቅ አልነበረም።

የእንግሊዙ መልዕክተኛ ሲናገር በሊቢያ፣ የሲረናይክ ሕዝብ የጣልያን አስተዳደር ተመልሶ እንዳይመጣበት ኃይለኛ ተቃውሞ ማድረጉን ገለጸ። የሱማሊያ ሕዝብ ግን የጣልያንን አስተዳደር ጨርሶ እንፈልግም፤ ጣልያን ተመልሶ ከሚመጣብን ሞታችንን እንመርጣለን፤ እያለ የሚያስማውን አቤቱታ ሚስተር ሜክኒል (McNEIL) በዝምታ አለፈው። ታላላቅ መንግሥታቶች የተባሉት ሁሉ መጀመሪያ የሚያስቡት ጥቅማቸውን እንደሆነ እናውቃለን። ይሁን እንጂ ለጥቅም ሲባል እንደዚህ የመሰለውን ሀቅ በግልጽ ለመሸፈጥ ሲሞክር ማየት ለምን አያሳዝንም ? ለምንስ አያበሳጭም ?

ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ ነው ብሎ የእንግሊዝ መንግሥት ያቀረበውን ሀሳብ፣ ኢትዮጵያ ለመቀበል አትችልም ። የእኛ ጥያቄ ኤርትራና ሱማሌ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀሉ ነው። የእንግሊዝ ሀሳብ፤ ሱማሌ አይገባችሁም። ለጣልያን መመለስ አለበት። ኤርትራ የምዕራቡ አውራጃ ተቆርጦ ለሱዳን ይሰጣል። ሌላው የምሥራቁና የደጋው ክፍል ከኢትዮጵያ ጋር ሊዋሀድ ይችላል የሚል ነው።

- <u>በሱማሊያ ጉዳይ፤</u> ላይ ጣልያን ተመልሳ እንድትመጣ ኢትዮጵያ አትቀበልም። ባላት አቅም ሁሉ ትታገላለች። አስፈላጊም ከሆነ በጦር ትዋጋለች።

-- <u>በኤርትራ ጉዳይ፤</u> ከአሜሪካና ከእንግሊዝ የቀረበው ሀሳብ፣ የኢትዮጵያን ጥያቄ የሚያረካ አይደለም። የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን በሰጠው ራፖር ከኤርትራ አብዛኛው ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር መቀላቀልን ይፈቅዳል ብሏል። እንግሊዝ ግን ለራሱ በማሰብ፤ ሀይማኖትን ተመርኩዞ ኤርትራ በሁለት እንድትከፈል ያቀረበውን ሀሳብ፤ በሚቻለን ሁሉ ተከራክረን ለማስለወጥ መሞከር አለብን። አንድ ጊዜ የእንግሊዝ መልዕክተኛ ሚስተር ሜክኒል በሰጠው መግለጫ እራሱ ተናግሮታል። « ..... የሀይማኖት ነፃነታቸው የተጠበቀላቸው ብዙ እስላሞች በኢትዮጵያ መኖራቸው የታወቀ ነው ... » ብሏል። እንግዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት አስተዳደር የሀይማኖት ነፃነትን የሚያከብር መሆኑ እየተረጋገጠ፣ በኤርትራ የምዕራቡ ክፍል ሕዝብ አብዛኛው እስላም በመሆኑ ብቻ፣ ለምን ተገንጥሎ ለሱዳን ዳረጉት ይሰጣል ?

የአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ንዴት በዚህ ጉዳይ ብቻ አይደለም። የእንግሊዙ መልዕክተኛ <u>ስለ ኤርትራ ጉዳይ</u> ያቀረበውን ሀሳብ ሲያብራራ በገለጻቸው ሁለት ዐረፍተ ነገሮች ላይ ቅር ተሰኝተዋል። የመጀመሪያው የምሥራቁና የደጋው ኤርትራዊ ሕዝብ በዘሩና በኦርቶዶክሳዊ ሀይማኖቱ ከትግራይ ሕዝብ ጋር ስለሚመሳሰል የሚለው ነው። ይህ አነጋገር ኢትዮጵያን በዘር ለመከፋፈል ከዚህ ቀደም እንግሊዞች ሞክረውት ያልተሳካላቸው ዕቅድ አሁንም ከሀሳባቸው ያልተሰረዘ መሆኑን የሚያመለክት ነው።

<u>ሁለተኛው ዐረፍተ ነገር፤</u> የምሥራቁና የደጋው የኤርትራ አውራጃ ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ድጋፉን ሲሰጥ፤ <u>« ኢትዮጵያ በፋሽስት ጥቃት የደረሰባት ስለሆነ እንድትካስ ያስፈልጋል፤ »</u> ሲል የሰነዘረው ቃል ነው። ኢትዮጵያ ልጆቿን በአንድነት ለመሰብሰብ ያቀረበችው ትክክለኛ ጥያቄ፣ በካሣ መልክ ሊታይላት አይገባም፤ ብለው አቶ አክሊሉ ያምናሉ።

ሚያዝያ 7 ቀን 1949 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የፖለቲካ ኮሚሲዮን ላይ፣ በታላቋ ብሪታንያና በኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪዎች መካከል የተፈጠረው የሀሳብ ልዩነት እንዴት እንደነበረ፤ ሪፖርቱ ከኒውዮርክ ወደ ሎንዶንና ወደ አዲስ አበባ በፍጥነት ተልኳል።

አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ለጃንሆይ እና ለጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ የላኩት የኮድ መልዕክት አዲስ አበባ ደርሶ እስኪፈታና ከዚያም ለጌቶቹ በቀም ጽሑፍ ተገልብጦ እስኪቀርብ፣ በእንግሊዞቹ በኩል ዜናው ቀድሞ ገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ደርሷል። አዲስ አበባ ያለው የእንግሊዝ አምባሳደር ሚስተር ዳንኤል ላሴል (DANIEL LASCELLES) ከሎንዶን ጋር ያለው የመገናኛ መስመር የሰዓቱን በሰዓት የሚያቀርብ ስለሆነ፣ የኒውዮርኩን ዜና በፍጥነት ማግኘቱ አያስደንቅም። ከዚህም በቀር የንጉሠ ነገሥቱ ልዩ ጸሐፊና የእንግሊዝ መንግሥት ታማኝ ወዳጅ የሆኑት አቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ ስለአሉለት፣ አምባሳደሩ በፈለገው ቀንና በፈለገው ሰዓት ጉዳዩን ለጃንሆይ ለማቅረብ የተለየ ዕድል አለው። በኒውዮርክ ስለደረሰው ሁኔታ የእንግሊዝ አምባሳደር በቀጥታ ከጃንሆይ ጋር ለመነጋገር አልፈለገም። ወይም ደግሞ የመንግሥቱን አስተያየት የሚገልጽ የኦፊሲየል ደብዳቤ አላቀረበም። በጊዋራንደም መልክ ለአቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድ አንድ ማስታወሻ ሲልክ፣ በተዘዋዋሪ ጉዳና ጃንሆይ እንዲያውቁት ማድረጉ ነው። በማስታወሻው ላይ የተጠቀሰው ቃል የሚከተለው ነበር።

« ..... ሚያዝያ 7 ቀን 1949 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኛ ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ መፍትሔ ለመስጠት ለፖለቲካ ኮሚሲዮን ሀሳብ አቀረበ። ይኸውም፣

1ኛ/ ከኤርትራ እስላም ከሆነውና ኢትዮጵያን ከማይፈልገው ከምዕራቡ አውራጃ በስተቀር ሌላው በሙሉ፣ ሁለቱ የባሕር ወደቦች አሰብና ምፅዋ፤ እንዲሁም ዋናው ከተማ አሥመራ ጭምር ከኢትዮጵያ ጋር እንዲዋሀዱ፤

2ኛ/ የጣልያን ሱማሌ ተብሎ የሚጠራው አገር ነፃነቱን ለመቀበል ብቁ ስላልሆነ፤ በተባበሩት መንግሥታት የበላይ ኃላፊነት ጣልያን በሞግዚትነት የወሰነ ጊዜ እንድታስተዳድር የሚል ነው።

ይህ ሀሳብ ለኮሚሲዮኑ እንደቀረበ የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በከረረ ቃላት አስተያየቱን ሲገልጥ፣ ከታላቋ ብሪታንያ የቀረበውን ሀሳብ ውድቅ አድርጐታል። የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ስም የገለጻቸው ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው።

1. <u>በኤርትራ ጉዳይ፤</u> ለሰምንት ዓመታት ሲሰቃይ የኖረው ሕዝብ አስቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጠው ያስፈልጋል። ይህም የሚጠበቀው ትክክለኛው ውሳኔ ሊያረካን የሚችለው፤ መላው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር በሙሉ ሲዋሀድ ብቻ ነው።

2. <u>በሱማሊያ ጉዳይ፤</u> ጣልያን ተመልሶ አገሩን እንዲያስተዳድር ከተደረገ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት አይቀበልም። ደግሞም ዝም ብሎ አይመለከትም። ሱማሌን ለማስተዳደር ይገባኛል ብላ ፍርድ የጠየቀች ኢትዮጵያ፤ በአቋሟ እስከ መጨረሻው ትታገላለች ቢያስፈልግም በጦር ትዋጋለች።

3. <u>የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፤</u> የታላላቆቹን ብቻ ሳይሆን የታናናሾቹንም መንግሥታት መብት በእኩል ደረጃ መጠበቅ አለበት።

.... የታላቋ ብሪታንያ መንግሥት ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች ጉዳይ መፍትሔ እንዲሆን ሀሳብ ሲያቀርብ፣ ለኢትዮጵያም የሚጠቅመውን በትክክለኛው መንገድ አስቦ ነው። የኢትዮጵያን መልዕክተኞች መሪ ሊያስቆጣ የቻለው ጉዳይ ምን እንደሆነ ለጊዜው አልታወቀም። ለማናቸውም የታላቋ ብሪታንያ መልዕክተኛ ያቀረበውን ሀሳብ ቈገፋበታል።...... »

ከዚህ ሁኔታ መረዳት የሚቻለው፣ አዲስ አበባ ያለው የእንግሊዝ አምባሳደር አክሊሉ ሀብተወልድ ስለአደረጉት ንግግር፣ የመንግሥቱን ቅሬታ ለንጉሠ ነገሥቱ በአፌሲል እንዲያቀርብ ከለንደን አልታዘዘም። ይሁን እንጂ በተዘዋዋሪ ጉዳና ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የእንግሊዝን ቅሬታ እንዲያውቁና አክሊሉንም እንዲያርሙ፣ በይፋ የማይወጣ የዲፕሎማሲ ስልት እንዲጫወት ከሎንዶን ሳይፈቀድለት አልቀረም። ከ 1943 ዓ.ም ጀምሮ፣ ለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ሥራ ኃላፊነት የተሰጣቸውን አቶ አክሊሉን እንግሊዞች እንዳልወደዱ ጃንሆይ ያውቃሉ። ምናልባት ይህች ኒውዮርክ ላይ የደረሰችው ግጭት አክሊሉን ከውጭ ጉዳይ ለማዛወር ትረዳ ይሆን ? የሚል የተስፋ ጭላንጭል አልጠፋም። አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ እንግሊዞችን አስቀይሟል የሚል ወሬ ከገነተ ልዑል ቤተመንግሥት ሲደርስ ጃንሆይን ሊያስቆጣ እንደሚችል ስለገመቱ፤ ለንጉሠ ነገሥቱና ለወልደጊዮርጊስ ሚያዝያ 7 ቀን 1949 ዓ.ም የደረሰውን ሁኔታ ዘርዝረው በኮድ ቴሌግራም ካስተላለፉ በኋላ፤ በቫሊዝ ዲፕሎማቲክ ለወንድማቸው ለአቶ መኰንን ሀብተወልድ በብዕራቸው በጻፉት ማስታወሻ ከገለጿቸው ሀሳቦች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

*« ...... ተዚህ ቀደም እንደነገርኩህ ጣልያን እኛን ለማጥቃት በኃይል ይሠራል። ኤርትራንና ሱማሌን መልሼ ታልያዝኩ ብሎ ተንኮሉን ቀጥሏል። ተሁሉ የሚያሣዝነው እንግሊዞች ወደ ጣልያን መዞራቸው ነው። ሱማሌ ለጣልያን እንድትሰጥ የተባበሩት መንግሥታትን በአፌሲየል ጠየቀ። በዚህ በጣም ተናደድኚ ኢትዮጵያ ይህን ሀሳብ አትቀበልም። ጣልያን ሱማሌ ላይ ለትሰፍር ዝም ብላ አትመለከትም ብዬ፣ የእንግሊዙ መልዕክተኛ ለተናገረው መልስ ሰጠሁት። ቀጥሎም ስለ ኤርትራ ጉዳይ ያው ተዚህ በፊት እንደነገርኩህ፣ የክርስቲያኑ ወገን ከኢትዮጵያ ጋር እንዲሆን፣ የእስላሙ ወገን ሱዳን ተቀላቅሎ እንግሊዞች እንዲያስተዳድሩት ይፈልጋሉ። የእንግሊዙ መላክተኛ ሀሳቡን ሲያቀርብ እኛ ይህ እንዲሆን የምንፈልገው ኢትዮጵያ በፋሽስት በደረሰባት ጥቃት ካሣ እንዲሆናት ነው ብሎ ተናገረ። በዚህም በጣም ተናደድኩ ። ኮሎኒያሊስት ጣልያን በሀይል ወግቶ የወሰደብን አገራችንና መሬታችን የሚመለስልን በፍርድ እንጂ በካሣ መልክ አይደለም። በንዴት ተነስቼ በሰጠሁት መልስ፣ በእንግሊዞች አስተዳደር ተስምንት ዓመት ጀምሮ የሚሰቃየው የኤርትራ ሕዝብ የጠየቀው ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል ነው ብየዋለሁ። በሱማሌ እና በኤርትራም ጉዳይ የተናገርኩትን የእንግሊዙም የአሜሪካኑም መላክተኞች ተቃወመን በማለት በእኔ ላይ ቂም መያዛቸውን አይቻለሁ። እናንተም እስካሁን ድረስ እንደተለመደው በእንግሊዝ አምባሳደር በኩል ወሬው ተፋፍሞ ሳይደርሳችሁ አይቀርም። እኔም ለጃንሆይ እና ለጸሐፊ ትእዛዝ የሆነውን ሁሉ እንዲያውቁት በረዥሙ ቴሌግራም አስተላልፌያለሁ። እነዚህ ታላላቅ የሚባሉ አገሮች በተለይም አሜሪካና እንግሊዝ፤ ትልቅ ቦታ ሆነው የትልቅ ሰዎች ሥራ ሲሠሩ ማየት አልቻልኩም። እንግሊዝ የተንኮሉን መንገድ ይከፍታል። አሜሪካ ምንም ሳያስብ አብሮ ይጓዛል። በዚህ ምክንያት እኔ እነዚህን አገሮች ማመንም ማክበርም አቅቶኛል። እንግሊዞችና አሜሪካኖች በእኔ ላይ ቅሬታቸው እየጨመረ ስለሄደ፣ ምንም ጸሐፊ ትእዛዝ ተእኔ ጋር ቢሆኑ ጃንሆይ ሠላም ለማግኘት፣ አክሊሉ ከውጭ ጉዳይ ቢዛወር ይሻላል ቢሉ አልገረምም። የደረሰው ይድረስ፣*

*ለእነዚህ አገሮች ደካማ ሆኜ መታየት አልፈልግም። የኢትዮጵያን ክብርና መብት የሚነካ ነገር ታጋጠመኝ መቃወሜንና የማስበውን መናገሬን አልተውም። አሁንም በዚህ ሰሞን እሥራኤል ነፃ መንግሥት ሆና (የሰው አገር ቀምታ) የተባበሩት መንግሥታት አባል እንድትሆን በሚደረገው ድምፅ እኛ ከዓረቦቹ ጋር ተቃዋሚ ስለምንሆን፤ የአሜሪካ ወኪል በንዴት ሊቃጠል ይችላል። እነሱ ተመጀመሪያ ጥቅማቸውን እንደሚከተሉ እኛም ለራሳችን መሥራት አለብን። በል እንግዲህ ይኸን ሁሉ ስትሠራ ለምን ሳትነግረኝ ቀረህ ? ብለህ እንዳትቆጣኝ፣ እኩለ ሌሊት ድረስ አልጋዬ ላይ ሆኜ በረዥሙ ጻፍኩልህ። ጃንሆይ ካለሁበት ሚኒስቴር እንድዛወር ከወሰኑ፣ እኔ ምን እንደምፈልግ የነገርኩህን አስብበት .....»*

*ያንተው አክሊሉ ሀብተወልድ*

አቶ አክሊሉ ለወንድማቸው በላኩት ማስታወሻ በኤርትራና በሱማሌ ጉዳይ ከታላላቆቹ መንግሥታቶች ጋር ያጋጠማቸውን ችግር ፣ ከጣልያንም ጋር የሚጠብቃቸውን ከፍተኛ ትግል፣ ብስጭትና ሥጋት በተቀላቀለበት መንፈስ ለማስረዳት ሞክረዋል። እንግሊዞችና አሜሪካኖች ጃንሆይን ገፋፍተው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን ቢለቁ፤ የአቶ አክሊሉ ምርጫ በፓሪስ የኢትዮጵያ አምባሳደርነት መሆኑ የታወቀ ነበር። እንደ ሎሬንሶ ታዕዛዝ ወደ ስታሊን አገር እንዳይወረወሩ በመጠኑ ሳይሰጉ አልቀሩም። ፓሪስ ቢሾሙ ብዙ ሰዎች ለሕይወታቸው ምቾት ለማግኘት ዕድሉ ተሰጣቸው ብለው ሀሜታ እንደሚነዙ ያውቃሉ። በዲፕሎማሲ ሥራ ኢትዮጵያን ለማገልገል ከፓሪስ በስተቀር ሌላ የሚሆን ቦታ የለም ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ፣ ከእንግሊዞችና ከአሜሪካኖች ጋር ያልተስማማ ሰው ሎንዶንም ዋሽንግተንም ሊመደብ አይችልም። በአገር ውስጥ ከውጭ ጉዳይ በስተቀር ሌሎቹ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፤ ከሥራ ልምዳቸውና ከዝንባሌያቸው ጋር የሚቀራረበው የትኛው እንደሆነ በግልጽ አይታያቸውም። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ውስጥ፣ ከእስያም ሆነ ከአፍሪካ ከፍተኛ ቦታ የተሰጠው ሰው ስለሌለ፣ በዚያን ጊዜ አክሊሉ እጩ ሆነው ቢቀርቡ፤ የረዳት ዋና ጸሐፊነት ሥራ ማግኘቱ አያዳግታቸውም ነበር። ይህም ቢሆን የአሜሪካና የእንግሊዝ መልካም ድጋፍ ከሌለበት ሊፈጸም አይችልም። ስለዚህ፤ ዞሮ ዞሮ ከእንግሎ አሜሪካ ተፅዕኖ ነፃ የሆነው ቦታ ፓሪስ ብቻ ስለሆነ፤ የጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስና የአቶ መኰንን ሀብተወልድ የጋራ ድጋፍ ጉዳዩን ያስፈጽመው ይሆናል ብለው አቶ አክሊሉ በሀሳባቸው ሲያወጡና ሲያወርዱ ቆይተዋል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ለጃንሆይና ለወልደጊዮርጊስ በሰፊው የላኩት ሪፖርት፣ ኮዱ እየተፈታ በቁም ጽሑፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ፣ በኒውዮርክ ስለደረሰው ሁኔታ አዲስ አበባ ካለው የእንግሊዝ አምባሳደር ለግርማዊነታቸው ልዩ ጸሐፊ የተላከው ሜሞራንደም ደርሷል። አቶ ተፈራወርቅ ኪዳነወልድም፣ የደረሳቸውን ማስታወሻ በአማርኛ አዘጋጅተው ለንጉሠ ነገሥቱ ሲያቀርቡ፣ ለታላቁ ባለሥልጣን ለጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ፣ ግልባጭ አልሰጡም ነበር። ነገር ግን በልዩ ጽሕፈት ቤት ያለው ተርጓሚ « ከጽሕፈት ሚኒስትሩ » ጋር የተለየ ግንኙነት ስለአለው፣ በየጊዜው እንደሚያደርገው ሁሉ፣ ከእንግሊዝ አምባሳደር ለተፈራወርቅ የተላከውን ማስታወሻ ኮፒ አድርጐ ለጸሐፊ ትእዛዝ ሰጥቷል። ጸሐፊ ትእዛዝ ወልደጊዮርጊስም ሁኔታው ስለአሳሰባቸው፣ ከአቶ አክሊሉ የተላከው ሪፖርት፣ በአስቸኳይ ተቀነባብሮ፣ የተፈራወርቅ ማስታወሻ ለጃንሆይ በሚደርስበት ሰዓት አብሮ እንዲቀርብና በአንድነት እንዲታይ አደረጉ።

# የመስኮብ ውርጅብኝ

የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ሚያዝያ 7 ቀን ስለደረሰው ሁኔታ ወደ አዲስ አበባ የላኩት ራፖር ታይቶ የንጉሥ ነገሥቱ ውሳኔ እስኪደርሳቸው፣ የሶቪየት ሕብረትና የጣልያን መልዕክተኞች፣ በኤርትራና በሱማሌ ጉዳይ የሚሰጡትን መግለጫዎች በጥብቅ የሚከታተሉበትና ለመልሱ የሚዘጋጁበት ጊዜ ነበር።

በጉባኤው ፕሮግራም መሠረት ከኃያላን መንግሥታቶች ውስጥ ሶስተኛው ተናጋሪ ሆኖ የተመዘገበው ሶቪየት ሕብረት ነው። አንድሬ ግሮሚኮ የመስኮብ መልዕክተኞች መሪ፣ ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ በሚያደርገው ንግግር፣ በእንግሊዞችና በአሜሪካኖች ላይ የስድብ ውርጅብኝ እንደሚነዛ ተጠብቋል። የሶቪየት ሕብረት መልዕክተኛ ንግግር ምንም እንኳን ኢትዮጵያ ባቀረበቻቸው በኤርትራና በሱማሌ ጥያቄዎች ላይ፣ በአሰብ በኩል የባሕር በር እንዲሰጣት ያስፈልጋል፤ የሚል ሀሳብ ከመሰንዘሩ በስተቀር፣ ሌላውን በሙሉ የሚቃወም ቢሆንም፣ ታላላቅና ኃያላን የተባሉትን እንግሊዝንና አሜሪካንን በዓለም መልዕክተኞች ፊት ለማዋረድ ባደረገው ጥረት፣ አክሊሉ ሀብተወልድ ደስ ብሏቸዋል።

« ..... የኢጣልያ ቅኝ ግዛት የነበሩት አገሮች ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ፣ ካለፉት ሶስት ዓመታት ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ጉዳያቸው ሳይወሰን፣ በኮሎኒያሊስት እንግሊዝ አስተዳደር ሲሰቃዩ የቆዩት በምን ምክንያት እንደሆነ፣ ለዚህም በኃላፊነት ተጠያቂዎቹ እነማን እንደሆኑ፣ የዓለም ጉባኤ ተገቢውን ጥያቄ ማቅረብ አለበት ..... » በሚል መግቢያ አንድሬ ግሮሚኮ ንግግሩን ጀመረ። የሶቪየት ሕብረት መንግሥት የመልዕክተኞች መሪ፣ በተባበሩት መንግሥታት አዳራሽ ውስጥ ይህንን ጥያቄ አስማምሮ እራሱ ካቀረበ በኋላ፤ መልሱንም እራሱ ተንትኖ ሰጥቷል።

« ....... ከ 1945 ዓ.ም እስከ 1948 ዓ.ም ድረስ፣ ኃላፊነት የተሰጣቸው አራቱ ኃያላን መንግሥታት (አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሣይና መስኮብ) የሊቢያን፣ የኤርትራንና የሱማሌን ጉዳይ ለመወሰን ያልቻሉት፤ ታላቋ ብሪታንያና አሜሪካ እንቅፋት በመሆናቸው ነው ..... » ሲል፤ አንድሬ ግሮሚኮ ለጉባኤው አስረዳ። የሶቪየት ሕብረት ግን የእነዚህ የድሆች አገሮች ጉዳይ፣ በሕዝቡ ፍላጎት መሠረት ተገቢ የሆነ ውሳኔ እንዲሰጠው ብዙ ጥረት ማድረጉን ከጠቀሰ በኋላ፤ እንግሊዝ፣ አሜሪካና ፈረንሣይ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት የውጭ ጉዳይ ምክር ቤት ውስጥ ይሠሩት የነበረውን ተንኮል፣ የተባበሩት መንግሥታት አባሎች ማወቅ አለባቸው በማለት፣ ምሥጢሩን መተንተን ጀመረ።

1ኛ/ « .....መስከረም 13 ቀን 1945 ዓ.ም የአሜሪካ መንግሥት ለአራቱ ኃያላን መንግሥታት ባቀረበው ሀሳብ፤ የጣልያን ኮሎኒ የነበሩት ሶስቱም አገሮች፤ በታላቋ ብሪታንያ እና በፈረንሣይ፣ በመስኮብና በአሜሪካ የጋራ ሞግዚትነት ለተወሰነ ጊዜ ቢተዳደሩ ይሻላል አለ። ይህ ሀሳብ ሲጠና ከቆየ በኋላ ፈረንሣይና መስኮብ የአሜሪካንን እቅድ ለመቀበል ሲስናዱ፣ ታላቋ ብሪታንያ በድንገት ተገንጥላ፣ ልዩ ልዩ ምክንያቶች እየፈጠረች ስለአደናቀፈች፣ ለጉዳዩ መፍትሔ ሌላ ዘዴ ማጥናት ግዴታ ሆነ።

2ኛ/ ግንቦት 6 ቀን 1946 ዓ.ም ታላቋ ብሪታንያ፣ የኤርትራን ጉዳይ ወደ ጐን ትታ፣ ለሊቢያና ለሱማሌ አዲስ ሀሳብ አለኝ ብላ ቀረበች:: ይኸውም በሊቢያ ሲረናይከና ትሪፖሊታንያ የተባሉት አውራጃዎች በአንድነት ተዋህደው፣ ነፃ መንግሥት ለማቋቋም ይቻላል:: የጣልያን ሱማሌ፣ የእንግሊዝ ሱማሌ ሳንድና በኢትዮጵያ ያለው የኦጋዴን አውራጃ በአንድነት ተጠቃለው፣ ትልቋ ሱማሌ የሚባል አገር ለመመሥረት እንዲቻል እና፣ ሞግዚትነቱም እንዲሰጣት፣ ታላቋ ብሪታንያ ያለ ሀፍረት ጥያቄዋን አቀረበች:: በተለይ እጅግ የሚያስገርመው የታላቋ ብሪታንያን ዕቅድ የአሜሪካም መንግሥት ደጋፊ ሆኖ ማጫፈሩ ነው:: የሶቪየት ሕብረት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሙሴ ሞሎቶቭ የታላቋ ብሪታንያን ውጥን፣ የቅኝ ግዛቶቿን ለማስፋፋት መሆኑን ስለተረዳው፣ በይፋ ተቃወመ::

3ኛ/ ግንቦት 10 ቀን 1946 ዓ.ም የሶቪየት ሕብረት ባቀረበው ሀሳብ ሊቢያ፣ ሱማሌና ኤርትራ፣ ለተወሰነ ጊዜ በጣልያን ሞግዚትነት እንዲተዳደሩ ቢደረግ ይሻላል አለ:: ወዲያው ፈረንሣይና አሜሪካ ሀሳቡን ደገፉት:: እንደተለመደው ታላቋ ብሪታንያ የተንኮል ተቃውሞዋን ስታቀርብ፣ አሜሪካም ዘላ ከእሷው ጋር ተሰለፈች:: እንግዲህ ይህ ሁሉ የሚያሳየው ምንድን ነው ? ታላቋ ብሪታንያ እያምታታች በአፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ የቅኝ ግዛቶቿን ለማስፋፋት አሜሪካ በታላቋ ብሪታንያ ቀያሽነት በነዚህ አገሮች ላይ የጦር ኃይሏን ማከማቻ ለማድረግ፣ ፈረንሣይ በቅኝ ግዛቶቿ አካባቢ፣ የአገሮች ነፃነትና የሕዝብ መብት እንዳይመሠረት፣ ሁሉም ለየግል ጥቅማቸው ነቅተው የሚጥሩ መሆናቸውን ነው::... » በማለት የሶቪየት ሕብረት መንግሥት መልዕክተኛ ምዕራባውያኖችን በሰፊው አወገዘ::

የአንድሬ ግሮሚኮ ዲስኩር በተጨማሪ ለማስገንዘብ የፈለገው፣ በዚህ ዓለም ለታናናሽ አገሮችና ለሕዝቦች ትክክለኛ መብት ተቆርቋሪና አለኝታ፣ ከሶቪየት ሕብረት በስተቀር ሌላ መንግሥት አለመኖሩን ነው:: በመጨረሻው ለሊቢያ፣ ለኤርትራና ለሱማሌ ጉዳይ መፍትሔ ይሆናል ብሎ ያቀረበው ሀሳብ፣ እነዚህ የቀድሞ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ለተወሰነ ጊዜ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት የጋራ ሞግዚትነት እንዲተዳደሩ ከዚህ ቀደም በመስከረም 13 ቀን 1945 ዓ.ም ከአሜሪካ ታቅዶ የነበረውን ፕላን በመደገፍ ነው::

ሶስቱ የምዕራብ ኃያላን መንግሥታት (አሜሪካ፣ እንግሊዝና ፈረንሣይ) በዓለም ላይ ለተደቀኑት ችግሮች ሁሉ መፍትሔ የሚፈልጉት ከየራሳቸው ጥቅም ጋር እያያያዙ ነው ብሎ፣ ግሮሚኮ የተናገረው ስህተት አይደለም:: በሌላ በኩል ደግሞ ሶቪየት ሕብረትም ከምዕራባውያኖች የተሻለ የራሱን ጥቅም ሳይመለከት ለባለጉዳዮቹ ብቻ የሚያስብ ነው ማለት አይቻልም:: የቀድሞዎቹን የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ተስማምተው ተገቢ ውሳኔ ለመስጠት ባለመቻላቸው በተባበሩት መንግሥታት መወቀስ ያለባቸው በአንድነት አራቱም ኃያላን መንግሥታት ናቸው እንጂ፣ ግሮሚኮ ለማሳመን እንደሞከረው፣ ሶቪየት ሕብረት ተነጥሎ ቅዱስ የሚሆንበት ምክንያት የለም:: ከ 1945 እስከ 1949 ዓ.ም ድረስ ስለ ቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ፣ የሶቪየት ሕብረት መንግሥት በተለያዩ ጊዜያቶች ሶስት ጊዜ አቋሙን ሲለውጥ ታይቷል::

መጀመሪያ መስከረም 13 ቀን 1945 ዓ.ም የአሜሪካ መንግሥት ሊቢያ ኤርትራና ሱማሌ፣ በአራቱ ኃያላን መንግሥታት ሞግዚትነት ለተወሰነ ጊዜ ቢተዳደሩ ይሻላል ሲል ያቀረበውን ሀሳብ ሶቪየት ሕብረት ደገፈ:: ቀጥሎ፣

የቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ተመልሰው ለጣልያን እንዲሰጡ ከፈረንሣይ በቀረበው ሀሳብ እስማማለሁ አለ:: አሁን ደግሞ ለሶስተኛ ጊዜ፤ በዚህ በሚያዝያ 9 ቀን 1949 ዓ.ም ለተባበሩት መንግሥታት ያቀረበው መፍትሔ፤ ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ መስኮብ አባል በሆነበት በአራቱ ኃያላን መንግሥታት የጋራ ሞግዚትነት እንዲተዳደሩ ያስፈልጋል አለ:: በጠቅላላው ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ ጉዳይ፣ የሶቪየት ሕብረት መንግሥት ሀሳብ በአንድ አቋም ላይ ጸንቶ አልታየም:: የመስኮብ መልዕክተኞች መሪ ላደረገው ንግግር መልስ ለመስጠት በቀጣ መንፈስ መድረኩን የያዘው፤ የታላቋ ብሪታንያ ልዑክ ሚስተር ሄክቶር ሜክኒል (HECTOR McNEIL) ነበር::

« ..... <u>ከሶስት ቀናት በፊት የኢትዮጵያ መልዕክተኛ ባደረገው ንግግር፣ ታላቋ ብሪታንያ ያቀረበችውን ሀሳብ አለመቀበሉን አመልክቷል::</u> ቀጥሎም የፈረንሣዩ መልዕክተኛ፣ ከታላቋ ብሪታንያ የተለየ ነው ብሎ የሚያምንበትን የራሱን ሀሳብ ለማሳመን ጥሯል:: እንደዚሁም ቀደም ሲል የብራዚሉ መልዕክተኛ ከታላቋ ብሪታንያ አስተያየት ጋር አለመስማማቱን ገልጿል:: ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ መልዕክተኞች የተናገሩት፣ የተሰበሰብንበትን ጉዳይ በሚመለከት ነው፣ ብለን እንገምታለን:: የሶቪየት ሕብረት መልዕክተኛ ግን ያደረገው ዲስኩር፣ ሁላችንንም በሰድብ ለማጥቃትና የራሱን ፕሮፓጋንዳ ለመንዛት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

...... የሶቪየት ሕብረት በየጊዜው እንደ አየር አቋሙን እየለዋወጠ የሚያደርገው ማምታታት፣ ለተሰበሰብንበት ጉዳይ ቀና የሆነ መፍትሔ ለማበርከት ሳይሆን፣ በተቻለው መጠን ለጉባኤያችን የተወሳሰበ ችግር ለመፍጠር መሆኑን የአባል መንግሥታት እንደራሴዎች እንዲያውቁት እንጠይቃለን ...... » በማለት ሚስተር ሜክኒል (McNEIL) ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ ንግግሩን ፈጸመ::

አንድሬ ግሮሚኮ ባደረገው ንግግር፤ ለኢትዮጵያ በኤርትራ በኩል የባሕር በር ተከልሎ እንዲሰጣት ማስፈለጉን እስማማለሁ ከማለት በስተቀር፣ ለሌሎቹ ጥያቄዎቿ ተቃዋሚነቱን አልለወጠም:: የመስኮብ አስተያየት እንኳንስ ሱማሌን ለመጨመር ይቅርና፣ የታሪክ፣ የባሕልና፣ የዘር አንድነት መኖሩ በትክክል የሚታመንበት የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መመለስ አጥብቆ የሚቃወም ነው:: የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ የሶቪየት ሕብረት መንግሥት ስለ ኤርትራና ስለ ሱማሌ ጉዳይ ያቀረበውን መፍትሔ ተቃውመው መልስ ቢሰጡ ኖሮ፣ ከእንግሊዝና ከአሜሪካ ጋር የሻከረውን ግንኙነታቸውን ለማሻሻል ጥሩ አጋጣሚ አግኝተው ነበር:: ነገር ግን በአቶ አክሊሉ አስተያየት ከመስኮብ ጋር በይፋ ጠብ መፍጠሩ፣ የብዙዎቹን ታናናሽ አገሮች ጠላትነት ማብዛት ስለሆነ፤ ገና ለገና የእንግሊዝና የአሜሪካ መልዕክተኞች ይደሰታሉ ብለን፤ ከጥቅሙ ጉዳቱ እንዲያመዝንብን አንፈልግም ብለው ተውት::

የታወቀው የመስኮብ ዲፕሎማሲ መሪ ያደረገው ከፍ ያለ የዘለፋ ንግግር፣ ጠላቶቹን ምዕራባውያኖችን ያበሳጨ ቢሆንም፤ ከአብዛኛዎቹ መልዕክተኞች መካከል ብዙ ወዳጆች ለመማረክና ለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች መፍትሔ ነው ብሎ ላቀረበው ሀሳብ በቂ ደጋፊዎች ለማግኘት አልቻለም::

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከተቋቋመበት ከ 1945 ዓ.ም ጀምሮ በተደረጉት የዓለም አቀፍ ጉባኤዎች ላይ፣ ያገሩ መልዕክተኛ በመሆን ያለማቋረጥ የተሳተፈው አንድሬ ግሮሚኮ፣ ከምዕራባውያኖች ጋር አተካሮ ለመግጠም የተለየ




*« ...... ታላቋ ብሪታንያ፤ አሜሪካና ፈረንሣይ ተባብረው፣ ሊቢያን ኤርትራንና ሱማሌን ተከፋፍለው የጦር ኃይሎቻቸው ማከማቻ ሊያደርጓቸው ነው ...... »*

አንድሬ ግሮሚኮ የመስኮብ መልዕክተኛ
(ሚያዝያ 1949)
(ፎቶ U.N)

ስጦታ ነበረው:: ከ 1957 ዓ.ም እስከ 1985 ዓ.ም ድረስ (ክሙሲ ኒየት) ከሞሎቶቭ ቀጥሎ ለ28 ዓመታት የሶቪየት ሕብረት መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ የምዕራባውያኖችን ልብ ሲያቆስል የኖረ በመሆኑ፣ የሀያኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ በስፊው ያስታውሰዋል::

## ስፎርሳ እና አክሊሉ

ሰኞ ሚያዝያ 11 **ቀን 1949 ዓ.ም** በኒውዮርክ አቆጣጠር ከእኩለ ቀን በፊት በአራት ሰዓት የተባበሩት **መንግሥታት የመጀመሪያው** ኮሚሲዮን፣ የአዲሲቷ የጣልያን ሬፑብሊክ የውጭ **ጉዳይ ሚኒስትር ኮምት ካርሎ** ስፎርሳ "COMTE CARLO SFORZA" ስለ ኤርትራ፣ **ሱማሊና ሊቢያ ጉዳይ፣ የመንግሥቱን** አቋም እንዲገልጥ የተጋበዘበት ቀን ነበር:: የ 77 **ዓመት (ሰባ ሰባት) ዕድሜ** ያለው ካርሎ ስፎርሳ፣ በሰሜን ጣልያን እጅግ ከታወቀውና ከተከበረው **ከካስቴ ሳን ጆቫኒ ስፎርሳ** "CASTE S.GIOVANNI SFORZA" ቤተሰብ **ዘርፍ የተወለደ እና፣** አባቱ ዮሐንስ ስፎርሳ የታሪክ ሊቅ ተብሎ የተነገረለት ታላቅ ሰው ነው:: በ 1872 **ዓ.ም** የተወለደው ካርሎ ስፎርሳ ከ 24 ዓመት ዕድሜው ጀምሮ በዲፕሎማሲ ሞያ ሲያገለግል ቆይቶ፣ በ 1920 **ዓ.ም የጂሊዮቲ** (GILIOTTI) መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ነበር:: ሙሶሊኒ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ ከመሾሙ ከጥቂት ወራት በፊት፣ ካርሎ ስፎርሳ በፓሪስ የጣልያን አምባሳደር ሆነ:: የሹመት ደብዳቤውን ካቀረበ በኋላ፣ የአምባሳደርነት ሥራውን ለስድስት ወራት እንኳን መቀጠል አልቻለም:: በህዳር 1922 ዓ.ም የጣልያን ንጉሥ ቪክቶር አማኑኤል ሳልሣዊ፣ የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ሥልጣን ለሙሶሊኒ ሲሰጥ፣ አምባሳደር ስፎርሳ የፋሽስት ተቃዋሚነቱን ገልጦ በፈረንሣይ አገር ስደተኛ ሆነ:: ከ 1922 ዓ.ም ጀምሮ ሙሶሊኒ ከሥልጣን እስከወረደበት እስከ 1943 ዓ.ም ድረስ፣ ካርሎ ስፎርሳ የሙሶሊኒን መንግሥት ለመጣል በተደረገው የፖለቲካ ትግል የተካፈለ ነው ተብሎ ይነገርለታል:: የሙሶሊኒ ዘመን ሲደመሰስ ካርሎ ስፎርሳ አገሩ ተመልሶ የፖለቲካ ሥራ ጀመረ:: ጣልያን አዲሲቷ ሬፑብሊክ ተብላ ከተቋቋመች በኋላ፣ በደጋስፐሪ የሚመራው የክርስቲያን ዴሞክራት ፓርቲ የመንግሥቱን የአስተዳደር ሥልጣን ሲይዝ፣ ከ 1947 ዓ.ም ጀምሮ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ በሕመም ምክንያት እስከለቀቀበት እስከ 1951 ዓ.ም ድረስ ቆየ::

ሰኞ ሚያዝያ 11 ቀን 1949 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት መድረክ ላይ እንዲናገር ፕሮግራም የተመደበለት፣ ኮምት ካርሎ ስፎርሳ የሚሰጠው መግለጫ፣ ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛት አገሮች ጉዳይ ስለሆነ፣ በሙሶሊኒ ዘመን በኮሎኒዎች አስተዳደር ከፍተኛ ሥልጣን የነበራቸው እነ ኤንሪኮ ቸሩሊ (ENRICO CERULLI) የአዲሲቷን ሬፑብሊክ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አጅበው መጥተዋል:: የሙሶሊኒ የምሥራቅ አፍሪካ ኮሎኒዎች ምክትል ጠቅላይ ገዥ ሆኖ ለሰባት ዓመት ለፋሽስቱ መንግሥት ቅን አገልግሎት ያበረከተው ቸሩሊ "CERULLI" ኮቱን ገልብጦ የኮምት ስፎርሳ አማካሪ ሆኖ ኒውዮርክ መምጣቱን፤ በመጀመሪያ ስምቶ ለኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ለአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ የነገራቸው፣ ልዩ ጸሐፊያቸው ልጅ እምሩ ዘለቀ ነበር:: በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አስቃቂ የሆነ ግፍ የፈጸመ ወንጀለኛ በመሆኑ፣ ከጉባኤው አዳራሽ እንዲከለከል የአራቱ ኃያላን መልዕክተኞችን እርዳታ ለማግኘት በእነ አቶ አክሊሉ በኩል የተደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀረ:: ሆኖም ኢትዮጵያ በአንድ መንገድ ተቃውሞዋን ማስማት ስለአለባት፣ ምቹው ጊዜ ከኮምት ስፎርሳ መግለጫ በኋላ ቢሆን ይሻላል ተብሎ በኢትዮጵያ መልዕክተኞች በኩል ተወሰነ::




*« ....... የሶቪየት ሕብረት በየጊዜው እንደ አየር አቋሙን እየለዋወጠ፣ በምዕራባውያኖች ላይ የሚነዛው ስድብ፣ በተባበሩት መንግሥታት ላይ የተወሳሰበ ችግር ለመፍጠር መሆኑን አባል አገሮች እንዲገነዘቡት ያስፈልጋል ....... »*

ሄክቶር ሜክኒል የእንግሊዝ መልዕክተኛ
(ሚያዝያ 1949)
(ፎቶ U.N)

ከጠዋቱ በአራት ሰዓት የተባበሩት መንግሥታት የዋናው ኮሚሲዮን ሊቀመንበር፣ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲናገር መድረኩን ሰጠው:: በዚያን ጊዜ ጣልያን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባል ለመሆን ገና ስላልተፈቀደላት፣ የተሰማውን ሀዘን ከገለጸ በኋላ፤ ካርሎ ስፎርሳ ንግግሩን የጀመረው « አዲሲቷ የጣልያን ሬፑብሊክ፣ የፋሽስት አስተዳደር ላደረሰው ጥፋት በኃላፊነት አትጠየቅም » ብሎ ነው:: ከዚህ ቀጥሎ የሀሳቡንና የምኞቱን ጠቅላላ ሁኔታ ፍንጭ ሲሰጥ « ..... አዲሲቷ ሬፑብሊክ ይዞታዎቿ የነበሩትን የአፍሪካ አገሮች ለማስተዳደር ኃላፊነቱ ከተሰጣት ያላትን አቅም ሁሉ ከንድታ፣ ለማልማትና በተቻለም ፍጥነት ለነፃነት ደረጃ ለማብቃት ቃል ትገባለች:: ....... እንዲሁም፤ ጣልያን ይህንን የተቀደሰ ተግባር ለመፈጸም ከተከለከለች፣ ጠቅላላውን የጋራ ዓላማችንን እና በተለይም ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የአፍሪካን ሕዝቦች ጥቅም በብርቱ የሚፃረር ይሆናል ...... » አለ:: .

የጣልያን ፍላጐቷና የምታደርገው ከፍተኛ ጥረት፣ የቀድሞዎቹን ቅኝ ግዛቶቿን፣ ሊቢያን፣ ኤርትራንና ሱማሌን መልሶ ለመረከብ መሆኑ፣ ከአራት ዓመታት በፊት የታወቀ ስለሆነ፣ የመጀመሪያው ክፍል የኮምት ካርሎ ስፎርሳ ንግግር፤ ለኢትዮጵያ መልዕክተኞች አዲስ ነገር ሆኖ አልታየም:: ትልቁ ጉድ፤ በተለይ ስለ ኤርትራ መሠረታዊ ታሪክ የተናገረው ነው:: « ..... <u>ኤርትራ መቸውንም ቢሆን የኢትዮጵያ ሆና አታውቅም::</u> ..... ወደፊትም ኢትዮጵያ ኤርትራን ለማስተዳደር ከአቅሟ በላይ ስለሆነ አትችለውም:: ..... ኤርትራን ከኢትዮጵያ ጋር ማቀላቀል የችግሩ መፍትሔ አይደለም:: ይልቁንም የአገሩን ሕዝብ በማስተባበር እያለሙ የሚኖሩት ጣልያኖች፣ ለቅቀው እንዲወጡ የሚያደርግ ሁኔታ ስለሚፈጠር፣ የኤርትራ ኢኮኖሚ ከመጠን በላይ ይወድቃል:: ..... ስለዚህ ለኤርትራ ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያም እንዲጠቅም በማሰብ፣ አስተዳደሩ ለጣልያን እንዲሰጥ መንግሥቴ ይጠይቃል:: ..... » ይህንን በመሰለ አነጋገር የኢትዮጵያን መልዕክተኞች ካበሳጨ በኋላ፣ ኮምት ስፎርሳ በራስ እምሩ ኃይለሥላሴ ስም በኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ የተገለጸውን አስተያየት ጠቅሶ መውቀስ ጀመረ::

ጣልያን ወደ ኤርትራም ሆነ ወደ ሱማሌ እንድትመለስ፤ ኢትዮጵያ ጨርሶ የማትቀበለው መሆኑን ደጋግማ አስታውቃለች:: የኢትዮጵያ አቤቱታ ችላ ተብሎ የጣልያን ፍላጐት እንዲፈጸም፣ የተባበሩት መንግሥታት ቢወስን፣ አገራችን ነፃነቷን ለመከላከል እርምጃ መውሰድ ትገደዳለች፤ በሚል መልክ የተዘጋጀ አንድ መግለጫ፤ በዋሽንግተን የግርማዊነታቸው ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ ፊርመውበት፣ ለኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ተልኮ ነበር:: ይህ መግለጫ የኢትዮጵያን አቋም በግልጽ ሁኔታ የሚያስረዳ እና ከዚህም በላይ መግለጫው የታተመው በራስ እምሩ ፊርማ በመሆኑ፤ የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ፣ ኮምት ስፎርሳ በተባበሩት መንግሥታት ጉባኤ ላይ ቀርቦ ለመጀመሪያ ጊዜ በሚናገርበት ዕለት፣ <u>በዚህ በሰኞ ሚያዝያ 11 ቀን 1949 ዓ.ም</u> አትሞ አወጣው::

የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በጋዜጣው ላይ ስለተገለጸው ሀሳብ ሲናገር፣ « .... በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ሚኒስትር በሰጠው መግለጫ፤ በኤርትራና እንዲሁም በኢትዮጵያ የኖሩት ጣልያኖች ምንም ዓይነት ሰብዓዊ መንፈስ የሌላቸውና አረመኔዎች የነበሩ ሕዝቦች ናቸው ብሎ የዓለምን ሕዝብ ለማሳመን ይቃጣል:: ቀጥሎም የጣልያን መንግሥት ኤርትራን መልሶ ለመያዝ የሚጥረው፣ ኢትዮጵያን ለመውጋት የጦር መሣሪያ ማከማቻ ለማድረግ ነው ይላል:: ይህ ሁሉ አስተያየት ትክክል አይደለም:: የኢትዮጵያን በፋሽስት መጠቃት፣ ከራሴ ጀምሮ



ስፎርሳ እና አክሊሉ

*« ...... ኤርትራ የኢትዮጵያ ሆና አታውቅም። ኤርትራን የፈጠረች ጣልያን ነች ...... »*

*« ....... ታሪክ አይሸፈጥም። የጣልያን የሀሰት ፕሮፓጋንዳ የኤርትራን ኢትዮጵያነት አይደመስሰውም። ....... »*

ኒውዮርክ ሚያዝያ 11ቀን 1949 ዓ.ም

አብዛኛው የጣልያን ሕዝብ ተቃውሟል:: የጣልያን ሕዝብ የፋሽስትን አገዛዝ ደምስሶ፣ ዴሞክራሲ መሥርቷል:: የአዲሲቷ ጣልያን መንግሥት ኤርትራን ለማስተዳደር ኃላፊነት ከተሰጠው በምንም ምክንያት ኢትዮጵያን ለማጥቃት፣ እንደማይሞክር፣ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የበላይ ተቆጣጣሪነት፣ አስፈላጊውን ዋስትና መስጠት ይቻላል ...... » ካለ በኋላ፤ ኮምት ስፎርሳ ወደ ንግግሩ ማክተሚያ ላይ፣ ኢትዮጵያ ለኤኮኖሚ ዕድገቷ በአሰብ በኩል የባሕር በር ተቀይሶ እንዲሰጣት የጣልያን መንግሥት **የሚደገፍ መሆኑን** ገለጸ:: ይህንን ሀሳብ በመስንዘሩ የኢትዮጵያን መልዕክ**ተኞ** ንዴት **በመጠኑም** ቢሆን ሊያበርደው የሚችል መስሎት ነበር:: ኮምት ስፎርሳ **እንደገመተው** አልሆነም:: የሠላሣ ሰባት ዓመት ዕድሜ ካላቸው ከኢትዮጵያ **መልዕክተኞች መሪ** የቀረበለት መልስ የሰባ ሰባት ዓመት ዕድሜ ያለውን **አዛውንት፣ ከጠበቀው** በላይ ሆኖ ክፉኛ አበሳጭቶታል::

« ...... **ከሁሉ ይበልጥ እጅግ** አድርጉ የሚያሳዝነኝ፣ እውነተኛን ታሪክ ሸፍጦ በህሰት ለመሸፈን **ሙከራ** ሲደረግ ማየቴ ነው:: የአንድ ትልቅ የታሪክ ሊቃውንት ቤተሰብ ተወላጅ የሆነ ሰው፤ በከፍተኛ ዕድሜውም በዚህ ዓለም ብዙ የፖለቲካ ሁኔታዎች ሲለዋወጡ የተካፈለና፤ ሰፊ ኤክስፔሪያንስ ያለው ነው ተብሎ ልዩ ዝና የተሰጠው ኮምት ስፎርሳ፣ « <u>ኤርትራ የኢትዮጵያ ሆና አታውቅም</u> » ብሎ ለመዋሸት ይደፍራል ብዬ ከቶ አልጠረጥርም ነበር:: ምናልባት እዚህ የተሰበሰቡት የመንግሥታት መልዕክተኞች የኢትዮጵያንና የአካባቢዋን ታሪክ ጠ ልቀው ያልተከታተሉ ናቸው ብሎ በመገመት ነው እንዳልል፣ ይህንን የመሰለው ስህተት ከኮምት ስፎርሳ የሚጠበቅ አይመስለኝም:: ያም ሆነ ይህ፣ በዚህ እጅግ በተከበረ የዓለም መንግሥታት ስብሰባ ላይ ከጣልያን መንግሥት የቀረበው መሠረት የሌለው መግለጫ ለዛሬም ሆነ ለወደፊቱ በማያዳግም ሁኔታ መታረም ያስፈልገዋል:: ..... የሩቁን ታሪክ ለጊዜው ትተን የቅርቡን ዘመን ብቻ ብንመለከት እንኳን፣ በ1884 ዓ.ም የዛሬ ስልሣ አምስት ዓመት በኢትዮጵያ፤ በእንግሊዝና በጣልያን መንግሥታት መካከል በተፈረመው የሠላም ውል የኤርትራ ግዛት የኢትዮጵያ መሆኑ ስለተረጋገጠ፣ ዛሬ ይህንን ማስረጃ እንዴት አድርጌ መካድ ይቻላል ? ሁለተኛ በ1885 ዓ.ም የጣልያን ኮሎኒያሊስት መንግሥት የኤርትራን አውራጃዎች በቅኝ ግዛት የያዘው፤ ከኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አስተዳደር ላይ በጦር ተዋግቶ በመንጠቅ መሆኑን ኮምት ስፎርሳ እንዴት ይረሳዋል ? ...... እንግዲህ እውነተኛውን ታሪክ ለመሸፈንና የተባበሩት መንግሥታት አባሎችን ለማሳሳት የአዲሲቷ ጣልያን መንግሥት ግብ ስለሆነ፣ እውነተኛውን የኢትዮጵያና የኤርትራን አንድነት መሠረታዊ ታሪክ ባጭሩ የሚገልጽ ዶክመንት በዛሬው ዕለት የሥራ ረዳቶቼ ለእያንዳንዱ መልዕክተኛ እንዲያቀርቡ ይደረጋል:: በዚህ ዶክመንት በኮምት ስፎርሳ ዛሬ የተነገረው የታሪክ መግለጫ ምን ያህል ከእውነት የራቀ መሆኑን በቀላሉ መረዳት ስለሚቻል፣ ወደ ሌሎቹ ጉዳዮች እዛወራለሁ::

.....የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮምት ስፎርሳ፣ ኤርትራ ለጣልያን መንግሥት እንዲመለስለት የሚጠይቀው፣ <u>ኤርትራን ከችግሯ ለማዳን ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያም ጥቅም በማሰብ ነው</u> ብሏል:: የተባበሩት መንግሥታት አባሎች እንደሚያስታውሱት፣ የአራቱ ኃያላን መንግሥታት መርማሪ ኮሚሽን ባቀረበው ራፖር፣ <u>ከኤርትራ ሕዝብ ዘጠና በመቶው የጣልያን አስተዳደር እንዳይመለስበት</u> አጥብቆ የሚቃወም መሆኑን አስገንዝቧል:: በዚህ አንጻር ደግሞ ስንመለከተው፣ <u>ሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መቶ በመቶው</u> ከጣልያን የሚፈልገው አንዳች ነገር አለመኖሩን ማረጋገጥ ይቻላል:: ስለዚህ ብዙ ዝርዝር ውስጥ ሳልገባ ኮምት ስፎርሳን

አጥብቆ የምጠይቀው፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን ሕይወት ለመወሰን፣ የሚጠቅመውንና የሚጐዳውን ለመለየት፣ የሚበቃ ችሎታና ነፃነት ስለአለው፣ የጣልያን መንግሥት ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ሕዝብ አሳቢነቱን ቢረሣው ይሻላል:: እስከዛሬ ድረስ የጣልያን መንግሥታቶች፣ ዲሞክራት ነን ባይዎቹም ሆኑ ፋሽስቶቹ፣ በአገሬ ላይ የተደጋገመ ወረራ የፈጸሙት፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሥልጣኔ በማሰብ ነው የሚል ፕሮፓጋንዳ እየነዙ መሆኑን፤ የዓለም ሕዝብ በጥልቅ እንዲገነዘበው ያስፈልጋል:: እኛ ኢትዮጵያውያኖች በሥልጣኔ ወደ ኋላም እንቅር ወደፊትም እንግፋ፣ ጉዳቱም ጥቅሙም የራሳችን ስለሆነ፣ የነፃነታችን ገፋፊና የታሪካችን ደምሳሽ ለመሆን የሚጥረውን የኮሎኒያሊስት ምክርና ድጋፍ አንቀበልም:: ጥንትም ለነፃነታችን ስንሰዋ ኖረናል:: ዛሬም ለነፃነታችን እንሞታለን::

..... በጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አስተያየት ኤርትራ ከኢትዮጵያ ጋር የተቀላቀለች እንደሆነ፣ በአገሩ ላይ የሚኖሩት ስላሣ ሺህ ጣልያኖች በሙሉ ለቀው ይወጣሉ ተብሏል:: ....... በዚህ አነጋገር ማንን ለማስፈራራት፣ ወይም ለማስጠንቀቅ እንደተፈለገ አልገባኝም:: መጀመሪያ ሠላሳ ሺህ የጣልያን ዜጐች በኤርትራ የሉም:: ሁለተኛ በሚገባ መታወቅ ያለበት ወደ ኤርትራም ሆነ ወደ ኢትዮጵያ ተልከው፤ በሰው አገር ባለርስት ሆነው እንዲሰፍሩ የተደረጉት የጣልያን ዜጐች፤ ለራሳቸው የተመቻቸ ሕይወት እንዲያገኙ ታስቦ ነው እንጂ፣ ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ይሰጣሉ ተብሎ አይደለም:: ሶስተኛ እነዚህ ጣልያኖች ወደ አገራቸው ቢመለሱ፣ የሥራ ዕድልና ምቾት ያለው የሕይወት ሞቅትና የሚያገኙ ቢሆን ኖሮ፣ የፋሽስት ሥልጣን ከተባረረ በኋላ እስካሁን ድረስ በኤርትራም ሆነ በኢትዮጵያ አይቆዩም ነበር:: ኮምት ስፎርሳ ደህና አድርጐ ያውቀዋል:: ነፃነታችን ከተመለሰ በኋላ በኢትዮጵያ የሚኖሩት ጣልያኖች ንጉሠ ነገሥታችንን እየተማጸኑ፣ የመኖሪያ ፈቃድ እየተሰጣቸው እዚያው እሉበት ቀሩ እንጂ፣ ወደ አገራቸው ወደ ጣልያን ለመመለስ ጨርሶ አልፈለጉም:: በኤርትራም የሚኖሩት ጣልያኖች፣ አንዳንዶቹ ወደ መሐል ኢትዮጵያ ተዛውረው ለመኖር፣ ሌሎቹም እዚያው አሉበት ለመቆየት ጠየቁ እንጂ፤ ወደ አገራቸው ወደ ጣልያን እንመለስ አላሉም:: ኤርትራ ከእናት አገሯ ከኢትዮጵያ ስትቀላቀል ደግሞ በኤርትራም ሆነ በኢትዮጵያ የሚኖሩት ጣልያኖች እጅግ የሚፈነጥዙ፣ ከሕዝቡም ከመንግሥቱም ጋር ጠባያቸውን አሳምረው ተስማምተው ለመኖር የሚፈልጉ ናቸው እንጂ፤ ይህንን የተመቸ ሕይወት ትተው በችግር ለመቆላት ወደ ጣልያን የሚመለሱ አይደሉም::

...... በዛሬው ዕለት በኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ሚኒስትር የሰጡት አስተያየት፤ ተገቢም ትክክልም አልነበረም በማለት የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ለጉባኤያችን ስለአስረዳ፤ አስፈላጊውን ማብራሪያ ማቅረብ ግዴታ ሆኖብኛል::

በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትርና ልዩ መልዕክተኛ የሆኑት ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ፣ ጣልያን ኢትዮጵያን በጦር ኃይል በወረረ ጊዜ፤ እስከ መጨረሻው በጀግንነት የተዋጉ ታላቅ የጦር መሪ የነበሩ ጀኔራል ናቸው:: የጣልያን ጦር በዓለም ሕግ የተከለከለውን የመርዝ ጢስና ጋዝ በሕዝቡ ላይ እየረጨና እያጥለቀለቀ የፈጸመውን አሰቃቂ የጭካኔ ሥራ፣ ራስ እምሩ በዓይናቸው ያዩ ናቸው:: የኢትዮጵያ ሠራዊት በጦር ሳይሆን በተነሰነሰበት መርዝ እና ጋዝ ድል ሲሆን፤ ራስ እምሩ በፋሽስቶች ተይዘው ጣልያን አገር ተወስደው ለሰባት ዓመታት በእሥር የተጉላሉና ብዙ መከራ የተቀበሉ ናቸው::

ስለዚህ ጣልያኖች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ስለአደረሱት የአረመኔነት ተግባር፣ በኤርትራና በኢትዮጵያም የተማሩትን ሰዎች ሁሉ እያደኑ በመግደል የፈጸሙትን ወንጀል፣ ራስ እምሩ ጠቅሰው የተናገሩት ትክክለኛውን እና እራሳቸው የተካፈሉበትን ታሪክ ስለሆነ፣ በተለይ የፋሽስት ተቃዋሚና አርበኛ የተባለውን ክምት ስፎርሳን የሚያስደስተው መሆን ነበረበት እንጂ የሚያሳዝነው ይሆናል ብዬ አልጠብቅም ነበር::

...... ራስ እምሩ ለኒውዮርክ ታይምስ የሰጡት መግለጫ፣ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ካርሎ ስፎርሳ ከአሥር ቀን በፊት ስለ ኤርትራ ጉዳይ ለጋዜጠኞች ለሰጠው ኢንተርቪው መልስ ነው:: « ..... ኤርትራን ለማስተዳደር ኃላፊነቱ ለጣልያን መስጠት አለበት:: ኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ ማቀላቀል የሚያስከትለው አደጋ ብዙ ነው:: ..... » እያለ ክምት ስፎርሳ የፈለገውን ሲናገር፣ ኢትዮጵያም በበኩሏ የምታስበውን ለመግለጽ መብቷ መሆኑ የሚያከራክር አይደለም:: በዋሽንግተን የኢትዮጵያ ሚኒስትር እንደገለጹት፣ የጣልያን መንግሥት በአንድ ትውልድ ዘመን ውስጥ ሶስት ጊዜ ኢትዮጵያን የወጋው፣ የኢትዮጵያ አካል በሆኑት በኤርትራና በሱማሌ በኩል ጦር እያደራጀ መሆኑን ዓለም እንዲገነዘበው ደጋግመን አስረድተናል:: የምናስማው ጩኸት ችላ ተብሎ፣ እንደገና ጣልያን ተመልሶ በኤርትራና በሱማሌ ላይ እንዲሰፍር ከተፈቀደለት፣ ኢትዮጵያ ለአራተኛ ጊዜ ከሚደርስባት ወረራ ለመከላከል አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ትገደዳለች:: ኢትዮጵያ ነፃነቷ እንዳይነካ መጠንቀቅና መዘጋጀት አለባት ስንል፣ እንደ ጠብ ጫሪና እንደ ዛቻ ለፋፊ ሆነን መገመት የለብንም:: ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት አባሎችን የምታሳስበው፣ ባለፉት ዘመናት የደረሱባት ፈተናዎች እንዳይደገሙባት፣ ለነፃነቷና ለግዛቶቿ ዋስትና ላቀረበችው ጥያቄ ትክክለኛ የሆነ ፍርድ እንዲሰጣት ነው:: ለነፃነታችን ዋስትና ..... ብለን ስንናገር፣ ክምት ስፎርሳ ደጋግሞ የሰጠን መልስ « <u>የፋሽስት አይዲዮሎጂና አስተዳደር ተደምስሶ አዲሲቷ የጣልያን ሬፑብሊክ ተወልዳለች:: ስለዚህ ኢትዮጵያን የሚያሠጋት ምንም ነገር የለም</u> ..... » የሚል መሆኑን እናውቃለን::

...... እኛ ኢትዮጵያውያኖች በሰው እገር የውስጥ አስተዳደር ጉዳይ ገብቶ መተቸት ዓላማችንም ልማዳችንም አይደለም:: ነገር ግን ፋሽስቶችን በሚመለከት ጉዳይ ስቃዩን የተቀበልን በመሆናችን የፋሽዝምን ከዓለም ገጽ መጥፋት ለመከታተልም አስተያየት ለመስጠትም ተግባራችን ነው ብለን እናምናለን:: እርግጥ የፋሽስቶቹ መሪ የነበረው ቤኔቶ ሙሶሊኒ ፍርድ መቀበሉን እናውቃለን:: ነገር ግን አብረውት ተሰልፈው ያገለገሉትና በሥልጣን የጨፈሩት ፋሽስቶች ሁሉ «አዲሲቷ» ከተባለችው ከጣልያን ሬፑብሊክ መንግሥት አባልነት የተሰረዙ ናቸው ለማለት አይቻልም:: ለምሣሌ በዛሬው ዕለት የኮምት ስፎርሳ የክብር ተከታዮች ሆነው በዚህ አዳራሽ ከፊታችን የሚታዩት የጣልያን ባለሥልጣኖች፣ እነማን መሆናቸውን፣ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች በጥንቃቄ እስተውለዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በመርዝና በጋዝ እየነደደ በሚያልቅበት ዘመን የሙሶሊኒ ወኪል ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ በሥልጣን ሲፈነጭ የቆየው፣ ኋላም ፋሽስት ድል ሲሆን ለወንጀለኞች በተቋቋመው የጦር ፍርድ ቤት ስሙ ተመዝግቦ የነበረው፣ ኤንሪኮ ቸሩሊ (ENRICO CERULLI) ዛሬ የአዲሲቷ ሬፑብሊክ ጣልያን መልዕክተኛ ሆኖ በዚህ አዳራሽ ወንበር ይዞ ስናየው፣ ምን ያህል የሚያበሳጭ፣ ምን ያህል የሚያሳዝን፣ ምን ያህል አሳፋሪ ድርጊት መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት አባሎች እንዲገነዘቡት ያስፈልጋል ..... » ብለው፣ አቶ አክሊሉ ንግግራቸውን ከመፈጸማቸው በፊት፣ <u>የጣልያን መልዕክተኛ አምባሳደር ኢንሪኮ ቸሩሊ</u>

መቀመጫውን ለቅቆ በሩጫ ከአዳራሹ ወጣ:: የቸሩሊ ከወንበሩ ዘሎ በሩጫ መውጣት ለአቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በሞቀ ስሜት ጣልያን ከፋሽስት ነፃ አልወጣችም ብሎ ለመተንተንና ለማሳመን መልካም አጋጣሚ ከፈተላቸው::

« ...... የፋሽስቶቹ መሪ ቤኒቶ ሙሶሊኒ ተገድሎ በሉካንዳ ሜንጠ መንጠ ልጠሉ በጣልያን የፋሺዝም ፍጻሜ ሆኗል ማለት አይደለም:: «አዲሲቷ» የሚል ስያሜ የተቀጠለላት ጣልያን፤ ከንጉሣዊ ዘውድ ወደ ሬፑብሊክ መንበር ተዛወረች እንጂ፣ ፋሺስት የነበሩት አስተዳዳሪዎቿ አልተደመሰሱም:: የሙሶሊኒ ታማኝ የነበሩት አገልጋዮች ሁሉ ይኸው በዚህ አዳራሽ ዛሬ እንደታየው ሸሚዞቻቸውን እየለወጡ በየሥልጣኑ ዘርፍ ተሰግስገዋል:: እንኳንስ የልብሶቻቸውን ቀለም ስማቸውንም ቢለውጡ፤ ያንን ሁሉ የፈጸሙትን ግፍ የሚከፍሉበት ቀን እንደሚመጣ አንጠራጠርም:: እንግዲህ አሮጊቷም ተባለች አዲሲቷ፣ በጣልያን መንግሥት ላይ ኢትዮጵያ ምንም ዓይነት እምነት እንዳይኖራት የሚያግዳት፣ ይህን ዛሬ ያየነውን የመሳሰሉት ሁኔታዎች መሆናቸውን፣ የዓለም ሕዝብ እንደሚረዳልን ተስፋችንን አንቆርጥም ...... »ካሉ በኋላ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ንግግራቸውን የፈጸሙት በሚከተሉት ቃላቶች ነበር:: « ..... ኢትዮጵያ በኮሎኒያሊስት ጣልያን በጦር ኃይል የተወሰዱባት ሕዝቦቿና ግዛቶቿ ኤርትራና ሱማሌ፤ እንዲመለሱላት ተገቢና ትክክለኛ የሆነ ጥያቄዋን አቅርባለች:: ..... አዲሲቷ ሬፑብሊክ የተባለችውም ጣልያን እነዚህ አገሮች ካለፉት 60 ዓመታት ጀምሮ መጀመሪያ በአያቶቼ ቀጥሎም ፋሽስቶች በሆኑት አባቶቼ፤ ሲያያዙ የመጡ ቅኝ ግዛቶቼ ስለሆኑ፤ በውርስ ለኔ ይገባኛል ብላ ለሙግት ቀርባለች:: እንግዲህ በነዚህ ጉዳዮች ላይ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ታሪካዊና ትክክለኛ ውሳኔ ይሰጥበታል ብለን፤ በጽኑ ተስፋ ከመጠበቅ በስተቀር፣ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ብቸኛና ፍርድ ሲነፈገው የኖረ አገር፣ ሌላ ምን ምርጫ ሊኖረው ይችላል ?...... »

አቶ አክሊሉ ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ላደረጉት ሰፊ ንግግር፣ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መልስ ሳይሰጥበት የዕለቱ ጉባኤ ተፈጸመ:: ምክንያቱ ለምን እንደሆነ በዚያን ጊዜ የጣልያን የውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትር የነበረውና፤ የኮምት ስፎርሳ የመልዕክተኞች ቡድን አባል ሆኖ በተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ የተካፈለው፣ ጁሴፔ ብሩዛስካ (GUISSEPE BRUSASCA) የሚከተለውን አስተያየት ሰጥቷል::

« ..... የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በዕድሜው ወጣት በመንፈሱ ንቁና በትምህርቱ የበሰለ መሆኑን እናውቃለን:: ነገር ግን አክሊሉ ሀብተወልድ በየጉባኤው አዳራሽ የሚያደርገው ንግግር ሁሉ የኢትዮጵያን ፖሊሲ ለማስረዳት ሳይሆን፣ በተለይ በጣልያን መንግሥትና ሕዝብ ላይ ያለውን የግል ቂምና ጥላቻ ለመግለጽ ሲል በመሆኑ፣ ኮምት ስፎርሳና እኛም ረዳቶቹ እናዝንበት ነበር:: ...... ሚያዝያ 11 ቀን 1949 ዓ.ም ኮምት ስፎርሳ ላደረገው ንግግር የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ መልስ መስጠቱ አይቀርም ብለን ሁላችንም ጠብቀናል:: ነገር ግን የፋሽዝም ተቀዋሚና አርበኛ በሆነው፣ ኢትዮጵያ በሙሶሊኒ ዘመን ለደረሰባት ጥቃት ተቆርቋሪነቱን በይፋ በገለጸው፣ በዚህ ሁሉ ሥራው በዓለም ላይ ዝናው በታወቀለት በኮምት ስፎርሳ ላይ፤ ይህን ያህል ውርጅብኝ ያጕርፋል ብለን አላሰብንም:: ቀጥሎም ፕሮፌሰር ኤንሪኮ ቸሩሊን (PROF. ENRICO CERULLI) አዋርዳለሁ በማለት፤ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ ተገቢ ያልሆኑ ቃላቶች ተጠቀመ:: ለምሣሌ በጦርነቱ ፍጻሜ ላይ በተቋቋመው የወንጀለኞች ፍርድ ቤት የቸሩሊ ስም ተመዝግቦ እንደነበረ የሰማነው ከአክሊሉ ነው:: እኛ የምናውቀው

የለም። ፕሮፌሰር ቸሩሊ በኢትዮጵያ በሥልጣን በቆየበት ዘመን የፈጸማቸውን የተደረገ አንድ ስህተት አለ። ይኸውም ታሪክን በሚመለከት ጉዳይ፣ ኤርትራ የኢትዮጵያ ሆና አታውቅም የሚለው ቃል ነው። ዲስኩሩ ሲዘጋጅ ይህችን ቃል ያከለበት፣ ኋላም አክሊሉ መዓቱን ያወረደበት ምስኪን ቸሩሊ ነበር። የዚችን ስህተት ጫፍ በመያዝ፣ አክሊሉ እስከ ኮምት ስፎርሳ ቤተሰብ ድረስ እየተንደረደረ፣ ፀረ ጣልያን የሆነ ዲስኩሩን ለማስፋፋት ጥሩ መክፈቻ ሆነለት። የአክሊሉ መልስ ሁሉም የሚነቀፍ ነው ባይባልም፣ አንዳንድ የሠነዘራቸው አስተያየቶች በጣም አስገርመውናል። ለምሣሌ «ሙሶሊኒ» ሞተ እንጂ ፋሺዝም አልተነካም። የአሁኖቹም ባለሥልጣኖች ሸሚዛቸውን ቀየሩ እንጂ ሁሉም የሙሶሊኒ አገልጋዮች የነበሩ ናቸው፤ ብሎ የተናገረው፤ በጣም የሚያሳዝን ነው። በአጋጣሚ ቸሩሊን መልዕክተኛ ሆኖ በማየቱ ብቻ፣ ሁላችንንም በአንድ ጉድጓድ ውስጥ መክተት አልነበረበትም። ደግሞስ አክሊሉ መቼ አጣው? በሙሶሊኒ ዘመን በሥራ ላይ የነበረ ሁሉ እንዴት ወንጀለኛ ሊባል ይችላል ? እንደዚህ ከሆነማ፣ ሙሶሊኒ በኢትዮጵያ ላይ በነገሠበት ዘመን፣ ለፋሺስት ሲያገለግሉ የነበሩትን ኢትዮጵያውያኖች ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ተረክበው ለምን በሥልጣን ላይ አስቀመጧቸው ? ...... ስለዚህ አክሊሉ የሚስጠንን መልስ ለመስማት ደስ ይለን ነበር። ነገር ግን ይህንን ጥያቄ ለማቅረብ ዕድሉ አልገጠመንም። በጠቅላላው አክሊሉ ህብተወልድ በጣልያን መንግሥትና ሕዝብ ላይ ከፍ ያለ ጥላቻ ስለአለው፣ የምንሰጣቸውን መግለጫዎች የሚተረጉማቸው በየሠረዝ ነጥቡና በየማሠሪያ ነጥቡ ስለሆነ፣ ንትርኩ እንዳይስፋፋ ለአክሊሉ መልስ መስጠት አያስፈልግም ብሎ ኮምት ስፎርሳ ወሰነ። ...... »

ፀረ ፋሽስት በሚል ዝና ስሙ የተወደሰለት ኮምት ካርሎ ስፎርሳ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በተባበሩት መንግሥታት ኮሚሲዮን ላይ ተገኝቶ ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ የመንግሥቱን አስተያየት እንዲሰጥ ሲጋበዝ፣ የሚያደርገው ንግግር የተቆጠበና የተለቀመ መሆን ነበረበት። ጁሴፔ ብሩዛውስካ፣ በኮምት ስፎርሳ ዲስኩር ላይ የነበረው ስህተት አንድ ብቻ ነበር ብሏል። አንድ ብቻ ሳይሆን ብዙዎች ነበሩ። ለምሣሌ ከብዙዎቹ በጥቂቱ « ኤርትራ ለጣልያን መንግሥት ብትሰጥ ጥቅሙ የኢትዮጵያም ነው » ብሎ መናገር ከፍ ያለ ድፍረት ነው። ቀጥሎም በኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ የኢትዮጵያ አስተያየት ለምን ታተመ ? ብሎ በተባበሩት መንግሥታት ሸንጐ ላይ ወቀሳ ማቅረብ ተገቢ አልነበረም። ከዚህ ሁሉ አልፎ ደግሞ በተባበሩት መንግሥታት አዳራሽ ውስጥ በነቸሩሊ ታጅቦ መቅረቡ፣ የኢትዮጵያን መልዕክተኞች ቢያስቆጣ ምን ያስገርማል ? በጠቅላላው ኮምት ስፎርሳ በሰጠው መግለጫ፣ ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያን መልዕክተኞች እጅግ ያናደደ ሲሆን፤ ወዳጆቼ የሚላቸውን የኃያላን መንግሥታቶችንም እንደራሴዎች አላስደሰተም።

የጣልያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር መግለጫውን በሰጠ ማግሥት ሚያዝያ 12 ቀን 1949 ዓ.ም የአሜሪካ መልዕክተኞች መሪ ጆን ፎስተር ደለስና የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሮበርት ሹማን (ROBERT SCHUMAN) ተገናኝተው፣ ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ ሲወያዩ፣ በዋዜማው ኮምት ስፎርሳ ያደረገው ዲስኩር እንዳልጣማቸው አውስተዋል። በተለይም የፈረንሣዩ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሰጠው አስተያየት፣ የስፎርሳ መግለጫ በሚገባ ያልተዘጋጀና ያልተስተካከለ በመሆኑ ያሳዝናል ካለ በኋላ፣ ይህ ሁኔታ የሚያሳየው በድንገት ብልጭ የሚልላቸውን ሀሳብ በመዘርገፍ የታወቁትን የጣልያኖችን ችኩልነት ነው ብሏል።

የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኮምት ስፎርሳ ፍሬ ቢስ ዲስኩር ማዘኑን የገለጸው፣ በተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን ላይ የጣልያንን አቋም አዳከመው ብሎ በመቆጨት ነው:: ሙሲ ሹማን ለፎስተር ደለስ እንደነገረው፣ ለአዲሲቷ ጣልያን ከቀድሞዎቹ ቅኝ ግዛቶቿ የሞቃዲሾ ሱማሌ ብቻ ቢመለስላት ይበቃል የሚባለውን ሀሳብ አይቀበልም:: ከኤርትራ በስተቀር፣ ከሊቢያም የትሪፖሊታንያ ክፍለ ሀገር ለጣልያን እንዲሰጥ ያስፈልጋል ብሏል:: ይህ የሚያሣየው ስለቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ የፈረንሣይ መንግሥት በመጠኑም ቢሆን የፖሊሲ ለውጥ ማድረጉን ነው:: ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ ከ 1945 ዓ.ም ጀምሮ፣ ሊቢያ፣ ኤርትራና ሱማሌ ለጣልያን መመለስ አለባቸው ብሎ የፈረንሣይ መንግሥት በያለበት ድምፁን ያሰማ እንደነበረ ይታወሳል:: ስለ ፈረንሣይ አቋም ጉዳይ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ በሚያዝያ 1949 ዓ.ም ለጃንሆይ በላኩት ቴሌግራም እንዲህ ብለዋል::

« ..... ጃንሆይ እንደሚያስታውሱት ባለፈው ነሐሴ ወር ፓሪስ ሄጄ ከአዲሱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሙሲ ሹማን ጋር ባደረግኩት ንግግር፣ ፈረንሣይ እንደአለፈው እንደነ ጕርኘ ቢዶ ዘመን በኤርትራ ጉዳይ እንደማታስቸግረን ቃል ገብቶልኝ ነበር:: ዛሬም ኒውዮርክ ተገናኝተን ሳነጋግረው አስተያየቱ አለመለወጡን ተረድቻለሁ:: ሆኖም ጃንሆይ እንደሚያውቁት ተለዋዋጭ በሆነው በፈረንሣይ መንግሥት ፖሊሲ ላይ ብዙ መተማመን አይቻልም:: በኔ ግምት የፈረንሣይ መንግሥት ለጣልያን ጠበቃ እየሆነ በኤርትራ ጉዳይ ላይ በየኮሚሲዮኑ የሚያደርስብንን ተቃውሞ ካቆመልን፣ አንድ ትልቅ ነገር ነው:: የፈረንሣይ መንግሥት እርዳታ ከዚህ አልፎ፣ ከአቆርዳት አውራጃ በስተቀር ሌላው የኤርትራ ክፍል ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀል እንግሊዞች ያቀረቡትን ሀሳብ ይደግፍ ይሆናል የሚል አስተያየት አለ:: በኒውዮርክ ስብሰባችን ላይ ሙሲ ሹማን ለረዥም ጊዜ ለመገኘት ስለማይችል፣ በእሱ ስም የፈረንሣይ መልዕክተኞች መሪ እየሆነ በየኮሚሲዮኑ የሚካፈለው የፖለቲካ ዋና ዲሬክተሩ ሙሲ ሞሪስ ኩቭ ደሙርቪል ነው:: ( MORICE COUVE DE MURVILLES ) ይህ ሰው በጦርነቱ ዘመን በቪሺ (VICHY) የተቋቋመውን የነ ላቫልን የፋሽስት መንግሥት የተቃወመና፣ ከጀኔራል ደጎል ጋር የተሰለፈ በመሆኑ የተከበረ ታሪክ አለው:: በኢትዮጵያና በፈረንሣይ መካከል ስለአለን ጥንታዊ ግንኙነትና፣ በተለይም ስለ ኤርትራ ያቀረብነውን ጥያቄ በሰፊው ነግሬው፣ በቀና መንፈስ አዳምጦኛል:: ኩቭ ደ ሙርቪል በጣም ጨዋና አርቆ አስተዋይ ስለሆነ፣ ጃንሆይን ሲያሳዝን የኖረውን የፈረንሣይን ግንኙነታችንን በጥሩ ወዳጅነት እንደሚያስተካክለው ተስፋ አድርጌያለሁ:: ..... »

አቶ አክሊሉ እንዳሉት ሮበርት ሹማን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ከያዘ በኋላ፣ በቀድሞዎቹ የጣልያን ቅኝ ግዛቶች ጉዳይ የፈረንሣይ መንግሥት በመጠኑ ያደረገው የፖሊሲ ለውጥ በከፊልም ቢሆን ለኢትዮጵያ ክፉ አልነበረም:: በጥር ወር 1949 ዓ.ም ሙሲ ሹማን ሎንዶን ሄዶ ከእንግሊዝ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ከሚስተር ኧርነስት ቤቨን ጋር ሲነጋገር የገለጸው ሀሳብ እንዲህ የሚል ነበር:: «ጣልያኖች የሞቃዲሾ ሱማሌና ከሊቢያ የትሪፖሊታንያ ክፍለ ሀገር እንዲሰጣቸው ያስፈልጋል:: እነዚህን አገሮች ካገኙ፣ በተጨማሪ ኤርትራን መጠየቅ ኢትዮጵያን ችግር ላይ መጣል ስለሆነ አያስፈልግም ብዬ ለኮምት ስፎርሳ በግልጽ ነግሬዋለሁ:: ኮምት ስፎርሳም ሠላሣ ሺህ የሚሆኑ ጣልያኖች የሚኖሩበት የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች ለጣልያን ከተሰጡ፣ ሌሎቹ ደጋማ የሆኑት አውራጃዎችና የአሰብ የባሕር በር ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀሉ ቢደረግ የጣልያን

መንግሥት ቅር እንደማይሰኝ አረጋግጦልኛል:: ...... የፈረንሣይ መንግሥት ባለው ጠቅላላ አመለካከት፣ የአሥመራና የምፅዋ ከተሞች በጂኦግራፊና በታሪክ፣ በፖለቲካና በኤኮኖሚ ረገድ ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ከፍተኛ ጉዳዮች መሆናቸውን ይገነዘባል:: ..... » ካለ በኋላ፣ ጣልያንና ኢትዮጵያ ተባብረው በጋራ ሞግዚትነት አሥመራንና ምፅዋን እንዲያስተዳድሩ ቢደረግ የተሻለ አይሆንም ወይ ? ሲል ሮበርት ሹማን የታላቋ ብሪታንያን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ጠየቀ:: ቤቨን ይህንን ሀሳብ አልተቀበለም:: « .... በዘርና በሀይማኖት የሚመሳሰለው የደጋው የኤርትራ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ጋር ሲቀላቀል፣ ከዚሁ ውስጥ አሥመራና ምፅዋ ተቆርጠው ሊወጡ አይችሉም:: የጣልያን ስጋት በአሥመራና በምፅዋ ለሚኖሩት ዜጐቿ ሲሆን፣ ኢትዮጵያም በዚያ ሠፈር የጣልያንን ሥልጣን ማየት አትፈልግም:: ለዚህ መፍትሔ የሚሆነው የጣልያን መንግሥት ኤርትራ እንዲመለስለት ያቀረበውን ጥያቄ ሠርዞ፣ ከኢትዮጵያ ጋር በኤኮኖሚና በልማት ረገድ ተባብሮ ለጋራ ጥቅም ለመሥራት የሚያስችል የሠላምና የወዳጅነት ስምምነት መመሥረት ነው:: ጣልያን ለዚህ ከተዘጋጀች፣ ኢትዮጵያም እንደምትቀበል አምናለሁ .... » ሲል ኧርነስት ቤቨን ሀሳቡን ደምድሟል::

የእንግሊዝና የፈረንሣይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ለንደን ላይ ከተነጋገሩ ከአራት ወር በኋላ፣ የኤርትራ ጉዳይ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መታየት ሲጀምር፣ እንግሊዞች ሀሳባቸውን አልለወጡም:: ያው ደጋግመው በተናገሩት ከአቆርዳት በስተቀር ሌሎቹ የኤርትራ አውራጃዎች ከኢትዮጵያ ጋር እንዲቀላቀሉ በሚለው ሀሳብ ረግተዋል:: የፈረንሣይ አቋም ግን የጠራ መልክ ይዞ አልታየም:: በእርግጥ ኤርትራ ለጣልያን ይመለስ ማለቱን አቁሟል:: ስለ አሥመራና ምፅዋ ከተሞች አስተዳደር ግን፣ የጣልያን እጅ የሚገባበትን ዘዴ ለማግኘት እንደሚጥሩ ይታይባቸው ነበር::

ሚያዝያ 12 ቀን 1949 ዓ.ም አቶ አክሊሉ ለጃንሆይ በላኩት ቴሌግራም፣ ምንም እንኳን በፈረንሣይ ፖሊሲ መተማመን ባይቻል በኒውዮርክ የፈረንሣይ መልዕክተኞች መሪ የሆነው ሞሪስ ኩቭ ደሙርቪል ጨዋና አርቆ አስተዋይ ስለሆነ፣ ሊረዳን ይችላል በማለት፣ ተስፋ ማድረጋቸውን ገልጸው እንደነበረ ይታወሳል:: እንደዚህ ጨዋና አስተዋይ እያሉ የገነቡትና እምነት የጣሉበት ሰው፣ አቶ አክሊሉ እንደ አሰቡት ሆኖላቸው ይሆን ? የኤርትራን ታሪክ እየተከተልን ስንጓዝ ወደፊት እናየዋለን::

## የአምሳለ ገነት ጉባኤና ውሳኔ

ሐሙስ ሚያዝያ 7 ቀን 1949 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ዋና ኮሚሲዮን በታላቋ ብሪታንያ እና በኢትዮጵያ ዋና መልዕክተኛ መካከል ስለተደረገው የአስተያየት ልውውጥ፣ አቶ አክሊሉ ሀብተወልድ ለጃንሆይ የላኩት ራፖርና የእንግሊዙ አምባሳደር ለአቶ ተፈራወርቅ የሰጠው ማስታወሻ ረቡዕ ሚያዝያ 13 ቀን 1949 ዓ.ም ሁለቱም በአንድነት ለንጉሠ ነገሥቱ ቀረቡ::